# አዲስ ዘመን

እፕድ

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 088 ኅዳር 28 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# መንግሥት የፌዴራል ሥርዓቱን በትክክለኛ አቅጣጫ ለመምራት ጥረት እያደረገ ነው



ፎቶ - ገበበ ገብሬ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የክልል መንግሥታት ግንኙነት አዋጁን ተከትሎ እንዲፈጸም በማድረግና ለአዳዲስ ክልሎች ጥያቄ ምላሽ በመስጠት የፌዴራል ሥርዓቱ በትክክለኛ አቅጣጫ የመምራት ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ዶክተር ኃይለየሱስ ታዬ ገለጹ፡፡

የሕገ መንግሥትና የፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ኃይለየሱስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት የክልል መንግሥታት ግንኙነት አዋጅን በማውጣትና ግንኙነቶቹ አዋጅን ተከትሎ እንዲፈጸሙ የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን እና ለአዳዲስ ክልሎች የክልልነት ጥያቄ ምላሽ በመስጠት የፌደራል ሥርዓቱ በትክክለኛ አቅጣጫ ለመመራት የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።

የፌዴራል ሥርዓት ተግባራዊነት መገለጫው የመንግሥታት ግንኙነት ሆኖ እያለ፤ የመንግሥታት ግንኙነቱ ግልጽ፤ በሚታወቅ እና ተቋማዊ በሆነ ሥርዓት ሳይመራ ቆይቷል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የመንግሥታት ግንኙነቶች እና የአሠራር ሥርዓቶች ሲመሩ የነበሩት ግልጽ በሆነ እና በታወቀ የመንግሥታት ግንኙነት የአሠራር ሥርዓት ሳይሆን በፓርቲ ከፍተኛ አካላት ነበር ብለዋል፡፡

መንግሥት የፌዴራል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በኢኮኖሚ እድገቱ ውስጥ የኢንዱስትሪውንና የግብርናውን ድርሻ ለማሳደግ መሥራት ይገባል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- እንደ አገር እየተመዘገበ ባለው ኢኮኖሚያዊ እድገቱ ውስጥ የኢንዱስትሪውና ግብርናው ድርሻ እንዲያድግ መሥራት እንደሚገባ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር ከፍተኛ ተማራማሪው ዶክተር አረጋ ሹመቴ ገለጹ፡፡

ዶክተር አረጋ ሹመቴ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአንድ ሀገር ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የኢኮኖሚ እድገት ሊመዘገብ ይችላል፡፡ ወሳኙ ነገር ግን ምን አይነት የኢኮኖሚ እድገት ወይም በየትኛው ዘርፍ ተመዘገበ የሚለው ነው፡፡

በመሆኑም በኢትዮጵያ እየተመዘገበ ባለው ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ምርት አምርተው ለሌላው ክፍለ ኢኮኖሚ ግባት የሚሰጡት ግብርናውና ኢንዱስትሪው ድርሻ ከፍ እንዲል መሥራት ይገባል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እያስተናገደው ያለው የኢኮኖሚ እድገት ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ማለትም የአገልግሎት ዘርፉ የሚመራው የኢኮኖሚ እድገት ነው ያሉት ዶክተር አረጋ፤ በ2014 ዓ.ም የስድስት ነጥብ አራት በመቶ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ ውስጥ የአገልግሎት ዘርፉ ሰባት ነጥብ ስድስት በመቶ፣ ምርት አምርተው ለሌላው ክፍለ ኢኮኖሚ ግብዓት የሚሰጡት ግብርናውና ኢንዱስትሪው ግን በቅደም ተከተል የአራት ነጥብ ዘጠኝና የስድስት ነጥብ አንድ ዕድገት አስመዝግበዋል፡፡



ዶክተር አረጋ ሹመቴ

እንደ ዶክተር አረጋ ገለጻ፤ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እድገት በኢኮኖሚው ላይ ቀጣይነት ባለው መልኩ የዋጋ ግሽበት ሊያስከትል ይችላል፡፡ አገሪቱ ውስጥ ያለው ምርት የኢኮኖሚውን ፍላጎት ማሟላት የማይችል ከሆነ ደግሞ ምርት ከውጭ ማስመጣት ስለሚቀጥል አገሪቱን በውጭ ምርት ጥገኛ እንድትሆን ሊያደርጋት ይችላል፡፡

ብዙ ምርቶችን ከውጭ ማስመጣት ከቀጠልን የውጭ ምንዛሪውን ዋጋ ከፍ በማደረግ ምንዛሪውን ወደ ጥቁር ገበያው ያዘነበለ ግብይት እንዲኖር ያደርጋል ያሉት ተመራማሪው፤ ይህም ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ዋጋ ከፍ እንዲል በማድረግ አገር ውስጥ ያለውን የዋጋ ግሽበት ሊያባብሰው ይችላል፡፡

በመሆኑም መወሰድ የሚገባቸውን አስፈላጊ ርምጃዎች በመውሰድ የግብርናውና ኢንዱስትሪው

በኢኮኖሚ እድገቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የጸረ ሙስና ትግል ከንግግር ባለፈ ተግባራዊ ርምጃን ይሻል

አዲሱ ገረመው

ሱሉልታ፡- የጸረ ሙስና ትግሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከንግግር ባለፈ ተግባራዊ ርምጃን እንደሚሻ ተገለጸ። የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ የጸረ-ሙስና ቀንን አከብሯል።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በዓለም አቀፍ ለ19ኛ ጊዜ እና በሀገር አቀፍ ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ ሙስና ቀንን "ሙስናን መታገል በተግባር" በሚል መሪ ሀሳብ ትላንት በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሁነቶች አክብሯል። ሙስና የሀገርን ኢኮኖሚ የሚገታ እንደመሆኑ ትግሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከንግግር ባለፈ ተግባራዊ ርምጃን እንደሚሻ ተመላክቷል።

የአካዳሚው የሥነምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክተር ወይዘሮ አልማዝ መኮንን ባቀረቡት ጽሑፍ፣ በኢትዮጵያ ሙስናና ብልሹ አሠራር ስር እየሰደደ መምጣቱን ጠቅሰው፤ ይህ የሀገሪቱን የዕድገትና የብልጽግና ጉዞ የሚያደናቅፍ እንደሆነም አመላክተዋል።

በተገኘው መድረክ ሁሉ የሙስናን አስከፊነት፣ የሚያደርሰውን ጉዳት በመደስኮር ብቻ የመልካም አስተዳደር ችግር የሆነውን ሙስናን ማስወገድ እንደማይቻልም አስገንዝበዋል።

ከመቼውም ጊዜ በላይ የፀረ ሙስና ትግል ከንግግር ባለፈ ተግባራዊ ርምጃን ይሻል ያሉት ዳይሬክተሯ፣ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ባለ ድርሻ አካላት በሙሉ የበኩላቸውን

የጸረ ሙስና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል














## “መንግሥት በጦርነት ተጠምዷል በሚል የሀገር ሃብት በዘረፋ ሳይ የማያዳግም እርምጃ ይወስዳል”

- ዶክተር አበራ ብሩ
የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ገጽ 4






## ኢንተርፖል ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ኢትዮጵያ እያደረገች ያለውን ጥረት ይደግፋል

ገጽ 3




# ‹‹ዳዮኤ ቡሹ››

**ዘላለም ግዛው**


አቶ አበበ ማሪሞ


አቶ ታሪኩ ታመነ


ግሪጎሪ ሚሳይለዲስ

ሲዳማዎች የሚወዱትን ሰው ሲቀበሉ ‹‹ዳዮኤ ቡሹ›› ይላሉ፤ አፈር ይምጣብኝ ማለታቸው ነው። እጅ ሲነሱ፣ ከልብ የመነጨ ፍቅራቸውን ሲገልጹ ነው። ሰው ወዳድነታቸውን የሚያስመሰክሩበት እና ልዩ አቀባበል የሚያደርጉበት አባባላቸው ነው።

ሲዳማዎች ከሁሉም ክልሎች የተወከሉ ወንድምና እህቶቻቸውን ‹‹ዳዮኤ ቡሹ›› ለማለት ደፋ ቀና ማለት ከጀመሩ ሰነባብተዋል። የባህላዊ ጭፈራቸውን እና ምግባቸውን ሊጋብዙ ጓጉተዋል።

እንኳን ሰው እንስሳው በፍቅር የሚቀበልባት፣ ጽዱ ከተማዋ፣ አረንጓዴ ልማቷ፣ የፍቅር እና የመቻቻል ሀገሯ ሲዳማ ልምዷን ለማካፈል፣ በረከቷን ለማቋደስ ዝግጅት ላይ ትገኛለች።

ነዋሪዎቹ አካባቢውን በማስተካከል ሽር ጉድ ላይ ናቸው። ‹‹አቦ›› ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓታቸውን ተሞክሮ ሊያጋሩ የቀኑን መድረስ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። የየክልሉ ተወካዮችም የአካባቢውን ጸጋ ለማየት፣ በተፈጥሮ ፍል ውሃ ለመጠመቅ ጓጉተዋል።

የሚጎበኙ የቱሪስት መስህብ ታሪካዊ ቦታዎችን እያጸዱ፣ እያሰናዱ እና እያደሱ ይገኛሉ። እንግዶቻቸውን ጥቁር ሐይቅ ዳር ሊያዝናኑዋቸው፣ በጀልባ ሊያንሸራሽሯቸው፣ ታቦር ተራራን ሊያስጎበኙ በዋዜማው ሥራ በዝቶባቸዋል።

በፌዴሬሽን ምክር ቤት አስተባባሪነትና በሲዳማ ክልል አስተናጋጅነት የሚከበረው የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓልን "ኅብረብሔራዊ አንድነት ለዘላቂ ሰላም" በሚል መሪ ሃሳብ የማጠናቀቂያ በዓሉ ኅዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ለ17ኛ ጊዜ ለማክበር ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቅቋል።

የአባዬ ሎጅ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛው ግርማ፤ ሐዋሳ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ፣ በእንግዳ ተቀባይነቷ የምትታወቅ ከተማ መሆኗንም ይጠቁማሉ። መርሐ ግብሩ በተደጋጋሚ የተደረገ ቢሆንም የሐዋሳ ባለሃብቶች ከወትሮው በተለየ መልኩ ተዘጋጅተው እየጠበቁ እንደሚገኙም ይጠቁማሉ።

ሲዳማ የራሱን ክልል ካደራጀ በኋላ ከተማው ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከበር መሆኑ በዓሉን ከወትሮው ለየት ያደርገዋል የሚሉት አቶ ግዛው፤ ሲዳማ ብሔር ብሔረሰቦችን አቅፎ በመያዝ የሚታወቅ ነው። እንግዶቻችን በነጻነት ተደስተው ተዝናንተው እንዲመለሱ ተዘጋጅተን እየጠበቅን እንገኛለን ይላሉ።

በይርጋለም ከተማ አረጋሽ ሎጅ ባለቤት ግሪጎሪ ሚሳይለዲስ፤ በእናቴ ኢትዮጵያዊ በአባቴ ግሪካዊ ብሆንም በሲዳሞ ተወልጄ በማደጌ ብዙዎች እንደሚቆጥሩኝ የውጭ አገር ዜጋ ሳልሆን እግዚአብሔር የሰጠኝ ኢትዮጵያዊ የሲዳማ ተወላጅ ነኝ›› ይላሉ።

ተፈጥሮ ያደለው አካባቢ ውስጥ ነው የምኖረው፣ በሲዳሞ ቤት አሠራር በቀርከሃ ቤት አሠራር ለሙሚኔ በተባለው የጥበብ ቤት ውስጥ ነው የምኖረው። የሲዳሞ የቤት አሠራርን አስተዋውቄያለሁ ብለዋል።

ድሮም የማውቀው ሲዳሞ ክፍለ ግዛት ሲባል ነው። ፊደል ማንበብ የጀመርኩት ‹‹ሲዳማ›› በሚለው ነበር። ስለዚህ ሲዳማ አዕምሮዬ ውስጥ ተቀርጿል፣ ልቤ ውስጥም ተቀምጧል፣ ለእኔ ሲዳሞ ትልቅ ትርጉም አለው።

ዛሬ በክልልነት ተደራጅቶ ሳየው፣ ሕዝቡን ስመለከት በጣም ደስ ይለኛል። በአካባቢው ጫማ እና ደህና የለበሰ፣ የተማረም መመልከት ብርቅ ነበር፤ ዛሬ ሁሉም ጫማ ለብሶ መመልከት ለእኔ ኩራት ነው ሲልም ደስታውን ገልጿል።

ልዩነት አላውቅም። እኔ ያደግኩት በአንድ ኢትዮጵያዊነት፣ በፍቅር ነው። አሁንም አንድነትን ነው የምመኘው። አንድነቱ ሲመጣ ለእኔ ትልቅ ደስታ ነው። ለእኔ የሚገባኝ ኢትዮጵያዊነት አብሮ መኖር ማለት ነው።

እኛ ሁል ጊዜ ተዘጋጅተን ነው የምንጠብቀው። እንግዳ መቀበል ለእኛ አዲስ አይደለም። ከዓለም ዙሪያ እንግዶች መጥተው ያርፋሉ። እንደወትሮው እንግዶቻችንን ዳዮኤ ቡሹ ብለን በክብር ተቀብለን አስተናግደን ለመሸኘት ዝግጁ ነን።

በክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ምክትል ኃላፊና የቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊ አቶ አበበ ማሪሞ፤ ዘንድሮ በክልሉ በሚከበረው በዓል አንዱ የጉብኝት መስመር ይሆናል ተብሎ ከተዘጋጀው መካከል መዳረሻ ተብሎ ከሚጠበቀው መካከል ይርጋዓለም ከተማ አንዱ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ሲዳማ ክልል ዕድሜ ጠገብ ከሆኑ ከተሞች አንዱ ሲሆን፤ በደርግ ዘመን የሲዳማ አውራጃ የአካባቢው አስተዳደር ወደ ሐዋሳ ከተማ ከመዘዋወሩ አስቀድሞ ለረጅም ጊዜ የሲዳማ ጠቅላይ ግዛት የአካባቢው የአስተዳደር ማዕከል በመሆን ያገለገለች ከተማ መሆኗን ይጠቁማሉ።

በዚህ ምክንያት የተለያዩ ቅርሶች ያሏት ከተማ መሆኗን፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልጅ የራስ ደስታ ባለቤት የልዕልት ተናኜ ቤት፣ ዋሻዎች፣ ቤተ መንግሥቶች ያሉበት፣ በአካባቢው መጀመሪያ ትምህርት ቤት ያለበትና ጥንታዊ ከተማ መሆኗን ነው የሚናገሩት። የይርጋዓለምና አካባቢዋን የቱሪስት መዳረሻ በማድረግ እየተጎበኘ ይገኛል።

አረጋሽ ሎጅ ለቱሪስት መዳረሻ ትልቅ አገልግሎት በመስጠት ትልቅ ሚና የተጫወተ ማኅበረሰብ አቀፍ ቱሪዝምን ያስለመደ፣ ባህላዊውን የሲዳማን የደጋ መንደር የቀርከሃ ቤት አሠራር ጥበብን በመከተል የተገነባ ሰላማዊ ለውጭ ጎብኚዎች የሚመረጥ ቦታ መሆኑን ይናገራሉ። በቦታው ላይ ባህላዊ፣ ታሪካዊ እና ተፈጥሯዊ መስህቦች መሆኑንም ይገልጻሉ።

የሐዋሳ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ምክትል ኃላፊና የማስፈጸም አቅም ግንባታና የአካባቢ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ታሪኩ ታመነ እንደሚሉት፤ ከተማዋ የምትታወቅበትን የፍቅር ከተማነቷን፣ ጽዱ፣ ውብ፣ አረንጓዴና የቱሪስት ከተማነቷን ለእንግዶች ለማስተዋወቅ እየተሠራ ይገኛል።

በተለይ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የቱሪስት ቦታዎችን የማልማት ሥራ በትኩረት እየተሠራ ይገኛል። ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ ጀምሮ የመጨረስ ትግበራን እውን ለማድረግ የሥራ ባህልን በመቀየር እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት እየተሰራ ነው።

የታቦር ተራራን ኢኮ ቱሪዝም ስፍራን ለጎብኚዎች ዝግጁ ለማድረግ የግንባታ ሥራው እየተከናወነ ይገኛል። መግቢያው በእርግብ አምሳል የሚገነባው ይህ ስፍራ ከተማው የሰላም ከተማ መሆኗን የሚያሳይ መሆኑን ነው የሚጠቁሙት።

እዚሁ ስፍራ ሲዳማዎች አገጭ ለአገጭ ተገጫጭተው የሚታይበት ገጽታ የሲዳማ ባህላዊ ጭፈራን የሚንጸባርቅ ከመሆኑም ባሻገር ባህልን በማስተዋወቅ ረገድ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ነው የሚናገሩት።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ ለብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል እንግዶች በሰላም ገብተው በሰላም እንዲወጡ፣ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የእግረኛ መንገዶችን የማስተካል ሥራም እየተሠራ ይገኛል።

# ተፎካካሪ ፓርቲዎች

## አሸባሪው ሸኔ በወለጋ እያደረሰ ያለውን ግፍ አወገዙ

## በንፁሓን ላይ የሚደረግን ጥቃትም መንግሥት እንዲያስቆም ጠይቀዋል

አሸባሪው ሸኔ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ወለጋ ማንነትን መሠረት ባደረገ መልኩ በንጹሓን ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና ግድያ በማውገዝ መንግሥት በንጹሓን ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ግድያ እንዲያስቆም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጠየቁ።

አሸባሪው ሸኔ ከሰሞኑ በምሥራቅ ወለጋ በንጹሓን ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና ግድያ በማስመልከት የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ፤የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ፣ እናት ፓርቲ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ፓርቲ እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መግለጫ ሰጥተዋል።

ፓርቲዎቹ በመግለጫቸው ባለፉት ዓመታት በወለጋ ማንነትን መሠረት በማድረግ እየተፈፀመ ያለው ጥቃት መቆም እንዳለበት አስገንዝበዋል። ፓርቲዎቹ በሰጡት መግለጫ መንግሥት የንፁሓንን ጥቃት በአስቸኳይ እንዲያስቆምና በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሆነው አሸባሪ ቡድኑን በሚደግፉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላይ ርምጃ እንዲወስድ እንዲሁም መንግሥት መዋቅሩን እንዲያጠራና በጥፋተኞች ላይም ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ጠይቀዋል።

ፓርቲዎቹ በሰጡት መግለጫ መንግሥት በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ መስጠት እንዳለበትም ጠይቀዋል። ሚዲያዎችና የተለያዩ የሲቪክ ማኅበራት ጭፍጨፋው መቋጫ እንዲያገኝ የበኩላቸውን መወጣት አለባቸው ነው ያሉት።

በተለይም እናት ፓርቲ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ፓርቲ እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ባወጡት መግለጫ ባለፉት አራት ዓመታት የጥቃቱ ሰለባዎች በዋናነት የአማራ ተወላጆች ይሁኑ እንጂ ኦነግ ሸኔን የሚቃወሙ የኦሮሞ ተወላጆችም የችግሩ ሰለባ ሆነዋል ብለዋል። የኦሮሚያ ክልል መንግሥት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ነዋሪዎችን ሰላምና ደኅንነት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት ሲሉም አስታውቀዋል።

# ጃፓን ለኢትዮጵያ የአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር የሰብዓዊ ድጋፍ ልታደርግ ነው

## -የአፍሪካ ልማት ባንክ የ14 ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ተፈራርሟል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጃፓን በኢትዮጵያ በድርቅና ግጭት ለተጎዱ ወገኖች የአንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር የሰብዓዊ ድጋፍ ልታደርግ መሆኑን በኢትዮጵያ የጃፓን ኤምባሲ ገለጸ።

በኢትዮጵያ የጃፓን ኤምባሲ መረጃ እንዳመለከተው የጃፓን መንግሥት በኢትዮጵያ በድርቅና ግጭት ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ሰብዓዊ ድጋፍ ሊያደርግ ነው። ድጋፉም በአማራ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ትግራይ እና ሶማሌ ክልሎች በሚገኙ የጉዳቱ ተጋላጭ ወገኖች የሚሰጥ ነው።

ከጃፓን መንግሥት በሚገኘው ዕርዳታ፤ የምግብ ዋስትናና ደኅንነትን ለማረጋገጥ፣ እናቶችን እና ሴቶችን በሥርዓተ ፆታና ሥነ ተዋልዶ በኩል በመድረስ የጤና ክትትል እና ድጋፍ ለማድረስ ያለመ መሆኑን ተገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ ለሕፃናት አልሚ ምግብ ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም የእንስሳት ክሊኒኮችን በማቋቋም ክትባቶችን ተደራሽ ለማድረግ እንደሚሠራ ተመላክቷል።

በክልሎቹ በተከሰተው ግጭትና ድርቅ ምክንያት ለተፈናቀሉ እና ወደ ቀያቸው ለተመለሱ ወገኖች አስቸኳይ ድጋፉ ተደራሽ እንደሚሆን ተጠቁሟል።

ጃፓን ድጋፉን የምታቀርበው በምግብ ፕሮግራም፣ በምግብ እና እርሻ ድርጅት እንዲሁም በፍልሰተኞች ድርጅት አማካኝነት መሆኑን ያመላከተው መረጃው፤ በቀይ መስቀል ኮሚቴ እንዲሁም በተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ እና በዓለም አቀፉ የሕጻናት አድን ድርጅትም ሰብዓዊ ዕርዳታው እንዲዳረስ እንደሚሠራ መረጃው አትቷል። በተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ ድጋፍ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ እንዲሁም በሌሎችም ዓለም አቀፍ ግብረ ሠናይ ድርጅቶች በኩል መሆኑን አስታውቃለች።



በተያያዘ በኦሮሚያ ክልል ቆላማ አካባቢዎች ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የ14 ሚሊዮን ዶላር የዕርዳታ ስምምነት መፈረሙን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታውቋል።

በኦሮሚያ ክልል ቆላማ አካባቢዎች ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የ14 ሚሊዮን ዶላር የዕርዳታ ስምምነት የተፈረመው በገንዘብ ሚኒስቴርና በአፍሪካ ልማት ባንክ መካከል ነው። ገንዘቡ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአካባቢ ልማት፣ ሥርዓተ ፆታን ያገናዘበ የተቀናጀ ዘላቂ የውሃ ልማት፣ የአካባቢ እና የግል ንጽሕና አገልግሎትን ለማስፋፋት እንደሚውል ተነግሯል።

በተጨማሪም በውሃ አጠር አከባቢዎች ለሚኖሩ አርብቶ አደሮች የከርሰ ምድር ውሃ ተደራሽ የሚሆንበት ፕሮጀክት እንደሚተገበር እና የገንዘብ ድጋፉ በጤና፣ በማኅበራዊ ኑሮ፣ በሥነ-ምግብ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመደገፍ እንደሚውል ተገልጿል።

የዕርዳታ ስምምነቱን የፈረሙት የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰመሪታ ሰዋሰው እና የአፍሪካ ልማት ባንክ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጠና ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱል ካማራ መሆናቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል።

# ክልሉ በበጀት ዓመቱ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች ሥራ ለመፍጠር አቅዷል

## - ንብ ማነብ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጓል

**ስምስም መንግሥቱ**

ባህርዳር፡- በአማራ ክልል የሥራ ዕድል ፈጠራ በወሳኝ ተልዕኮ እየተሠራ መሆኑንና በበጀት ዓመቱም ለአንድ ሚሊዮን 203 ሺ180 ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ። ከተለዩት የሥራ ዘርፎች የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝና በዚህም ወደ 529 ሺ. ወጣቶችን ለማሠማራት መታቀዱ ተጠቁሟል።

የአማራ ክልል የሥራና ሥልጠና ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አወቀ ዘመነ በክልሉ የተለያዩ ዞኖች በማኅበር ተደራጅተው በንብ ማነብ ላይ የተሠማሩ ወጣቶች ያመረቱትን የማርና ማር ውጤቶችን የማስተዋወቅና የማነቃቃት መርሐግብር ሰሞኑን በባህርዳር ከተማ በተካሄደበት ወቅት ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ለአንድ ሚሊዮን 203 ሺ180 ወጣቶች ሥራ ለመፍጠር መታቀዱንና የሥራ ዕድል ለመፍጠርም የግብርናው ዘርፍ በተለይም ንብ ማነብና የእንስሳት ሀብት ልማት ትልቅ አቅም ያለው ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁ መሠረትም የሥራ ዕድሉ ከሚፈጠርላቸው አንድ ሚሊዮን 203 ሺ180 ወጣቶች መካከል 529 ሺ. ወጣቶች በግብርናው ዘርፍ የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ናቸው።

እንደ አቶ አወቀ ማብራሪያ በግብርናው ዘርፍ በተለያየ መንገድ ወጣቶችን በማገዝ ውጤታማ ለማድረግ 25 የሚሆኑ ግብረሰናይ ድርጅቶች ይገኛሉ። የተቋማቱን አቅም የበለጠ ለመጠቀም የሥራና ሥልጠና ቢሮ ጥረት እያደረገ ነው።

ተሞክሯቸውን ለማስፋት፣ የአሠራር ድግግሞሽ እንዳይኖርና የሀብት ብክነት ሳይኖር አቅማቸውን አሟጠው ከመንግሥት አቅም ጋር የተቀናጀ ሥራ እንዲሠሩ ግብረሰናይ ድርጅቶቹ የጋራ የሆነ ፎረም ኖሯቸው ለመንቀሳቀስ የሚችሉበትን መንገድ እንዲያመቻቹ ቢሮው ከግብረሰናይ ድርጅቶቹ ጋር በመነጋገር የተጠናከረ ሥራ ለመሥራት ጥረት እያደረገ እንደሆነም ተጠቁሟል።

ቀድመው ሥራ የጀመሩ ውጤታማነታቸው እየታየ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ አወቀ፤ በተለይም በንብ ማነብ የክህሎት ሥልጠና ከመስጠት ጀምሮ ምርት ተመርቶ ለገበያ እስኪደርስ ድረስ ባለው ሂደት ወጣቶችን በማብቃት፣ለንብ ማነብ አስፈላጊ የሆነ ቁሳቁስ በማሟላትና በተለያየ መንገድ በመደገፍ በክልሉ አዊ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ጎንደር፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ወሎ፣ዋግ ኽምራና ደቡብ ጎንደር ዞኖች በተለያዩ



በወጣቶች የተመረተው ማር ልማት ሲጎበኝ፡

ወረዳዎች ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ዓለምአቀፍ ሥነ ነፍሳትና ሳይንስ ሥነምህዳር ማዕከል (አይ.ሲ.አይ.ፒ ኢ) የሞይሽ ፕሮግራም በውጤታማነት እንደሚጠቀስ አመልክተዋል።

በፕሮግራሙ እየታገዙ ወጣቶችም ከባዕድ ነገር ነፃ የሆነ (ኦርጋኒክ) ማርና ሰም አምርተው ለገበያ በማቅረብ ኮለን ወይንም ንብ አባዝተው ለንብ አናቢዎች በመሸጥ በገቢ ተጠቃሚ ከመሆናቸው በተጨማሪ ክልሉንም በማር ልማት እንዲታወቅ በማድረግ ውጤታማነታቸው እየታየ መሆኑን አስረድተዋል። አሳሳቢ የሆነውን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ በክልሉ እየተደረገ ያለውን ጥረት የሚያግዝ ፕሮግራም እንደሆነም ጠቁመዋል።

በበጀት ዓመቱ ሩብ ዓመት ከአጠቃላይ እቅዱ 15 በመቶ ለመፈጸም ወይንም ለ180 ሺ. ወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር እንደሆነ የገለጹት አቶ አወቀ፤ በሩብ ዓመት ለ129 ሺ. ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን አስታውቀዋል። በክልሉ የሥራ ፈላጊው ቁጥር እየጨመረ መሆኑን ጠቅሰው፣53ሺ. የዩኒቨርስቲና 81ሺ151 የኮሌጅ ተመራቂዎች፣ በድምሩ ወደ 912 ሺ. ሥራ ፈላጊዎች መመዝገባቸውን አመልክተዋል። ለሥራ ፈላጊው ቋሚ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት፣በርብርብ ለመሥራት ከታች እስከ ላይ ያለው አመራር በጋራ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልጸዋል። ጦርነት ቆሞ ሰላም እየተፈጠረ ባለበት በዚህ ወቅት በጦርነቱ የተጎዳው የማኅበረሰብ ክፍል ሥራ ፈላጊ በመሆኑ የሥራ ዕድል መፍጠሩ ተግባር ለነገ የሚባል እንዳልሆነ አስምረውበታል።

ዓለም አቀፍ ሥነ ነፍሳትና ሳይንስ ሥነ ምህዳር ማዕከል (አይ.ሲ.አይ.ፒ ኢ) የሞይሽ ፕሮግራም አስተባባሪ ዶክተር ወርቅነህ አያሌው በበኩላቸው፤ በሞይሽ ፕሮግራም ወደ 10ሺ. የሚሆኑ ወጣቶች ተሳታፊ መሆናቸውንና ፕሮግራሙም ተገምግሞ ጥሩ ውጤት በማስገኘቱ ሞይሽ የሚለው ሁለተኛው ፕሮግራም መጀመሩን ገልጸዋል። በሞይሽ ፕሮግራም በአማራ ክልል ወደ 19ሺ. ወጣቶች መካተታቸውንና በአጠቃላይ በክልሉ ወደ 30ሺ. ወጣቶች በንብ ማነብ መሠማራታቸውን ገልጸዋል።

በክልሉ በጦርነት ቀጣና ውስጥ በነበሩ ጥቂት አካባቢዎች ወደኃላ ቢቀሩም በንብ ማነብ የተፈጠረው የሥራ ዕድል መልካም ውጤት እያስገኘ መሆኑን አስረድተዋል። ዋና መሥሪያ ቤቱን ካናዳ ባደረገው ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ዓለም አቀፍ ሥነ ነፍሳትና ሳይንስ ሥነምህዳር ማዕከል (አይ.ሲ.አይ.ፒ ኢ) በእስካሁን እንቅስቃሴው በአማራ፣በኦሮሚያ፣በደቡብና በትግራይ ክልሎች 70ሺ. ወጣቶችን በንብ ማነብ በማሰልጠን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል። በአምስት ዓመት ጊዜ 100ሺ. ወጣቶችን በልማቱ ውስጥ ለማስገባትና እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።



ዳንኤል ዳምጃኖቪክ

# ኢንተርፖል

## ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ኢትዮጵያ እያደረገች ያለውን ጥረት ይደግፋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፉ የፖሊስ ድርጅት /ኢንተርፖል/በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ኢትዮጵያ እያደረገች ያለውን ጥረት እንደሚደግፍ አስታወቀ።

በዓለም አቀፉ የፖሊስ ድርጅት /ኢንተርፖል/ የፀረ ሽብር ማዕከል የአፍሪካና የአውሮፓ ማዕከል ኃላፊ ዳንኤል ዳምጃኖቪክ በአዲስ አበባ ከትናንት ጀምሮ እየተካሄደ ባለው በ24ኛው የምሥራቅ አፍሪካ ፖሊስ አዛዦች ኅብረት ጠቅላላ ስብሰባ በመካፈል ላይ ይገኛሉ። ኃላፊው እንደገለጹት፤ድንበር ዘለል ሽብርተኞችን መከላከል የኢንተርፖል ዋነኛ ተልዕኮው ነው። በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ስጋት የሆነውን ሽብርተኝነት በመዋጋት የኢትዮጵያን የላቀ ሚና የሚደነቅ ነው። ዓለም አቀፉ የፖሊስ ድርጅት (ኢንተርፖል) ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ኢትዮጵያ እያደረገች ያለውን ጥረት ይደግፋል።

በዓለም 195 አገራትን በአባልነት ያቀፈው ኢንተርፖል በየአህጉራቱ ከሚገኙ የፀረ ሽብር የቀጣና ማዕከላት መካከል አንዱ በኬንያ ናይሮቢ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል። በተለይም የሽብርተኝነት ስጋት ባለበት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ከሚመለከታቸው የሀገራቱ የጉምሩክ፣ ኢሚግሬሽን፣ የፖሊስና ሌሎችም ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለው የምስራቅ አፍሪካ ፖሊስ አዛዦች ኅብረት ስብሰባም በርካታ ባለድርሻ ተቋማት ጋር ለመምከር ዕድል የፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል።ላለፉት አምስት ዓመታት ከየሀገራቱ የጉምሩክ፣ ኢሚግሬሽን፣ ከፖሊስና ሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሽብርተኞችን ለመከላከል በርካታ ርምጃዎችን ወስደናል ብለዋል።

በስብሰባው የቀጣናው ሀገራት የጸረ ሽብር ትግል ተሞክሯቸውን ያጋሩ መሆኑን ጠቅሰው የኢትዮጵያ ልምድ የሚደነቅ መሆኑን ገልጸዋል። በመሆኑም ኢንተርፖል በፀረ ሽብር ግዳጅ አፈጻጸም ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎችም ሀገራት የሚያደርጉትን ጥረት እንዲሁም ተሞክሮ እንዲለዋወጡና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርገውን ድጋፍና ትብብር ያጠናክራል ብለዋል።

በጸረ ሽብር የትግል እንቅስቃሴ ኢንተርፖል ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው በቀጣይም አጠናክሮ እንደሚቀጥል አመልክተዋል።ኢትዮጵያ በቀጣናው የሽብር ተጋላጭነት ስጋት ካለባቸው አገሮች መካከል መሆኗን ጠቅሰው የመከላከል ሥራው በተጠናከረ መልኩ ሊቀጥል ይገባዋል ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# "ሙስና የሀገር እድገት ፀር በመሆኑ አምርረን መታገል አለብን"

## - ብርጋዴር ጄኔራል ይልማ መኳንንቴ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ሙስና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲዛባ፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር፣ የሥራ አጥ ቁጥጥርና ድህነት እንዲጨምር የሚያደርግ በመሆኑ አምርረን መታገል አለብን ሲሉ የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ገለጹ። የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት አመራርና አባላት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ-ሙስና ቀን "ሙስናን መታገል በተግባር ነው!" በሚል መሪ ቃል አከብረዋል።

የመከላከያ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ብርጋዴር ጄኔራል ይልማ መኳንንቴ የፀረ-ሙስና ቀን በማጠቃለያ መድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ ሙስና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲዛባ፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር፣ የሥራ አጥ ቁጥርና ድህነት እንዲጨምር ያደርጋል። እንዲሁም የጤናና የትምህርት ተቋማት እንዲዳከሙ፤ የዲሞክራሲ መርሆች እንዲጣሱ እና ግልጽና አሳታፊ የመንግሥት አሠራር እንዳይኖር የሚያደርግ ነው። ሙስና የአገር እድገት ፀር በመሆኑ አምርረን መታገል አለብን ብለዋል።

ሙስናን ለመከላከልም እንደተቋም አደረጃጀትና አሠራር ማጠናከር፤ የሥነ ምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታ፤ የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ማጠናከር አስፈላጊና ወሳኝ ነው ያሉት ብርጋዴር ጄኔራል ይልማ፤ ሙስና በአገራችን እያደረሰ ያለው ሁሉ አቀፍ ጉዳትና የስነ-ምግባር ብልሹነት ትውልዱ ላይ የሚያስከትለው



የሞራል ውድቀት ለሀገር እድገት ፀር መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ተቋም ዓለም አቀፍ የጸረ ሙስና ቀንን ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ሁነቶች ሲከበር መቆየቱን አውስተው፤ አምና በ2014 ዓ.ም ከነበረው የሕግ ማስከበር ዘመቻ ጎን ለጎን በመምሪያዎችና በክፍሎች እለቱ መከበሩን አስታውሰዋል። በበጀት ዓመቱ በስነ ምግባርና ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ በርካታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መሰጠታቸውንም ተናግረዋል።

ሙስናና ብልሹ አሠራርን ትርጉም ባለው ሁኔታ ለመከላከል ዜጎች በፀረ-ሙስና ትግሉ ሊሳተፉ እንደሚገባ የገለጹት የመከላከያ ስነ ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኮሎኔል አስፋ ደበሌ ፤ የትውልድ የስነ-ምግባር ግንባታ በጠንካራ ስነ ምግባር በመምራት ሌብነትንና ብልሹ አሠራርን በመታገል የሀገር እድገትን እናፋጥናለን ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ኮሎኔል አስፋ ገለፃ፤ ሙስናና ብልሹ አሠራር ጥቂቶችን በጊዜያዊነት በመጥቀም ብዙኃኑን ለድህነት የሚዳርግ ነው። የኅብረተሰቡን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት በማደናቀፍ አድሎና ብልሹ አሠራርን በማስፋፋት በሐዝብ መካከል አለመተማመንን ይፈጥራል።

የሙስና ቀንን ስናከብር ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመታገል ከብልሹና ሌብነት የፀዳ በሕግ የተመራ አሠራር መከተል እንደሚገባና ባለሙያዎችም ያለ ምንም እጅ መንሻ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው መፈተሽ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ የሠራዊቱ አመራሮች፣ አባላት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተገኙ ሲሆን ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጽሑፎችም በውይይቱ ቀርቧል።

# ለአካል ጉዳተኞች የአካል ድጋፍና የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደረገ

ቤዛ እሸቱ

አዲስ አበባ፡- በድሬዳዋና አካባቢዋ ለሚገኙ አካል ጉዳተኞች የሚውል ከሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የአካል ድጋፍና የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደረገ።

በድሬዳዋ ከተማ ሐምሌ 24 የተከበረውን የአካል ጉዳተኞች ቀንን አስመልክቶ የተሰጠው ድጋፍ ዊልቸር፣ ክራንች፣ አጋዥ የድምጽ መሣሪያና የአይነስውራን በትር መሆኑን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ኤርጎጌ ገለጻ በኢትዮጵያ ወደ 20 ሚሊዮን የሚጠጉ የአካል ጉዳተኞች ሲኖሩ ለዘመናት ከተሳትፎና ተጠቃሚነት ተገፍተው ቆይተዋል። ይሄንን ለመቅረፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እየሠራ መሆኑንና የአካል ጉዳት በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ላይ ሊከሰት የሚችል የሕይወት አጋጣሚ መሆኑን መረዳት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሚኒስትሯ ለአገር ሕልውና ዋጋ የከፈሉ ጀግኖች ተገቢውን ክብርና እንክብካቤ እንዲያገኙ የሚያስችል የኢትዮጵያ ጀግኖች የጦር አካል ጉዳተኞች የተሐድሶና ስልጠና ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ተጠናቆ ለመንግሥት መቅረቡንም ተናግረዋል።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው በኢትዮጵያ አካል ጉዳተኝነትን ከሚያስከትሉ በሽታዎች እና ሁኔታዎች አብዛኞቹ በቀላሉ መከላከል ይቻላል ብለዋል። ሁለንተናዊ የሕክምና ተቋማትን አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች አካታች ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ሊያ ገለጻ በቅርቡ በጤና ትምህርት ዘርፍ የተከሰተው በትምህርትና ሥልጠና አካታችነት ላይ ውስንነት መኖሩን ያሳየ ነው። በቀጣይ ሙያው የሚፈልገው ክህሎት እንዲኖር መሠረታዊ ጉዳዮችን ባሟላ መልኩ የአካል ጉዳተኞች በጤና ሙያ ስልጠና ውስጥ የሚካተቱበት አግባብ መስፋት እንዳለበት ያሳየ መሆኑንና ለዚህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር ስለ አካል ጉዳት ሲታሰብ የችሮታ ጉዳይ መሆን እንደሌለበት ገልጸዋል። የከተማ አስተዳደሩ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ቃል ገብተዋል።

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ወይንሸት ሙሉሰው የአካል ጉዳተኞች ችግር የሚፈታው ሁሉም በትብብር ሲሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ከጥቂት ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ በጥቂት ሰዎች ሲከበር የነበረው በዓል በአመራሩ ዘንድ የተሻለ ግንዛቤ በመፈጠሩ በክልሎች ተሳትፎ በየክልሉ በዙር እየተከበረ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኅብረተሰቡና የመንግሥት አካላት በተለይ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው፣ መስማትና ማየት የተሳናቸውና የአዕምሮ መታወክ ያጋጠማቸው ወገኖችን እንዲያግዙ ጥሪ አቅርበዋል።

በመድረኩ ላይ የአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ያሉ ችግሮች እንዲፈቱና መብት እንዲከበር የሠሩ የክልል ቢሮዎች፣ ኤምባሲዎች ዓለም አቀፍና ሀገር በቀል የግብረሰናይ ድርጅቶች የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት የእውቅና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። የ2016 ዓመት የአካል ጉዳተኞች ቀን በሀገር አቀፍ ደረጃ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚከበር ይሆናል።

# “መንግሥት በጦርነት ተጠምዷል በሚል የሀገር ሃብት በዘረፉ ላይ የማያዳግም እርምጃ ይወስዳል”

- ዶክተር አበራ ብሩ

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በጦርነት ተጠምዷል በሚል የሀገር ሃብት ዘረፉ ላይ በተሠማሩ አካላት ላይ የማያዳግም እርምጃ እንደሚወሰድ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር አበራ ብሩ ገለጹ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ19ኛ ጊዜ በሀገር ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ ሙስና ቀን አስመልክቶ በአቃቂ ክፍለ ከተማ በሚገኙ 12 ወረዳዎች ሲካሄድ የቆየው የፀረ ሙስና ትግል ንቅናቄ ማጠቃለያ በክፍለ ከተማ ደረጃ ባለፈው ሳምንት ተካሂዷል።

በመድረኩ ላይ ውይይት የመሩት የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር አበራ ብሩ እንደገለጹት፤ መንግሥት በጦርነት ተጠምዷል በሚል የሀገር ሃብት ሲዘርፉ የነበሩ ሰዎች ተለይተዋል። መንግሥት በነዚህ ከፍተኛ ሙስና በሠሩ አካላት ላይ የማያዳግም ርምጃ ይወስዳል።

ከዚህ በፊት የሙስና መከላከል ቀን ቢከበርም ሙስና እንደ አንድ የሥርዓቱ አካል ተዘርግቶ ስለነበር ከወረቀት ያለፈ ሥራ መሥራት ሳይቻል መቆየቱን ያነሱት ዶክተር አበራ፤ አሁን የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ ሙስናን በመከላከል ረገድ ወደ ተግባር መግባት ነው ብለዋል።

የሙስና ተግባርን በመረጃ ለማስደገፍ እጅግ ከባድ እና ውስብስብ መሆኑን ጠቁመው፤ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ በዚህ ጉዳይ ላይ የማይተካ ሚና ስላለው እና ከኅብረተሰቡ ተደብቆ የሚቀር ስለሌለ ማኅበረሰቡ በነቃ ተሳትፎ ሌቦችን ማጋለጥ አለበት ብለዋል።

መንግሥት ከባድ ትግል ውስጥ እንዳለ በመገንዘብ ኅብረተሰቡ በሙስና ጥቆማ ተሳትፎ ላይ ንቁ መሆን አለበት ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ በሙስና ላይ የሚደረግ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ መንግሥት ለሚወስደው እርምጃ ደጋፊ ስለሚሆን ችላ ማለት እንደማይገባ ጠቁመዋል።

በመድረኩ ላይ ሙስናን መታገል በተግባር በሚል ዙሪያ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሰነድ ያቀረቡት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በአቅም ግንባታና ሁኔታ ግምገማ ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ዘነበ ወይሳ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በሙሰኝነት ሚዛን ከዓለም ሀገራት አንፃር ያለችበትን ደረጃ ማሻሻል የሚቻለው የኅብረተሰቡ ተሳትፎ ሲያድግና ሙስናን ተመልክቶ አያገባኝም ብሎ የማያልፍ ትውልድ መፍጠር ሲቻል ነው ብለዋል።

ሙስና ነውር እንዲሆን ባለመሠራቱ እና በአኗኗር ዘይቤያችንና ሥነ ቃሎቻችን ሙስናን አሸሞንሙነን ስለያዝነው ኢትዮጵያ ታማለች ያሉት ኃላፊው፤ ሙስናን በቃል ሳናሸሞነሙን ሌብነትም ወንጀልም መሆኑን በማመን ሀገራችንን ልናክም ይገባል ብለዋል።

ከአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ከተለያዩ ወረዳዎች የተውጣጡ ነዋሪዎች ሙስናን የመከላከል መድረክ መዘጋጀቱን አመስግነዋል።

ሆኖም በሙስና ጥቆማ ላይ ሲሳተፉ ከዛቻ ጀምሮ እስከ ድብደባ እንደሚደርስባቸው ገልፀው ይህ ሁኔታ ሙስናው በመንግሥት መዋቅር ውስጥ እንዳለ እንዲጠራጠሩ እንዳረጋቸው ገልፀዋል።

በተጨማሪም ጥቆማ የተደረገባቸው የወረዳና ክፍለ ከተማ አመራሮች ላይ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ያሉበትን ቦታ ሲዘዋወሩ እንጂ እርምጃ ሲወሰድባቸው ባለማየታቸው ቅሬታ እንዳሳደረባቸው አንስተዋል።

በተለይ የመሬት አስተዳደር እና የክፍለ ከተማ የፍትሕ ተቋማት ላይ ፍተሻ እንዲያደርግ የክፍለ ከተማውን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጠይቀዋል። አመራሩ በቁርጠኝነት ለመታገል ከተነሳ ከጎናችሁ ነን ሲሉም የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች ተናግረዋል።

# መንግሥት የፌዴራል ሥርዓቱን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዚህ አካሄድም ፓርቲው በማዕከላዊ ኮሚቴ ተሰብስቦ የወሰነውን ለክልሎች ያስተላልፍ ስለነበር የቀደመው ሥርዓት የነበረው አካሄድ የፓርቲ ጉዳይ እንጂ የሕገ መንግሥት ጉዳይ እንዳልነበር ገልጸው፤ የማንነት እና የክልልነት ጥያቄዎች ላይም የተሰጡ ምላሾች የፌዴራል ሥርዓቱን ተግባራዊነት የሚያረጋግጡ አልነበሩም ሲሉ አብራርተዋል።

በመሆኑም በዚህ ዙሪያ ቀድሞ የነበሩ ስህተቶችን ለማረም በሚረዳ መልኩ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ያነሱት ዶክተር ኃይለየሱስ የለውጡ መንግሥት የመንግሥታት ግንኙነት አዋጅ በማውጣት እና ወደ ትግበራ በመግባት፤ለአደረጃጀት ጥያቄዎች በየደረጃው ምላሽ በመስጠት የፌዴራል ሥርዓቱ በትክክለኛ አቅጣጫ ለማስኬድ የሚያስችሉ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛል ነው ያሉት።

በተወሰደው ርምጃም የመንግሥት ግንኙነት የታወቀ እና ተቋማዊ ከማድረግ እስከ አዳዲስ ክልሎች ምሥረታ ድረስ የዘለቀ የፌዴራል ሥርዓት መሠረት መሬት ላይ ወርዶ ሊተገበር እንደቻለ አንስተዋል።

ከጣልቃ ገብነት በተላቀቀ መልኩ ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱ ክልሎች መኖራቸው፤ የክልሎችን ግንኙነት በታወቀ መንገድ ለማድረግ እና የመንግሥታቱን ግንኙነት ለመወሰን አዋጅ ወጥቶ የክልል መንግሥታት እየተገናኙ ችግሮችን ተመካክሮ ለመፍታት እንቅስቃሴዎች ላይ ያሉ መሆናቸው ተጠናክሮ ቢቀጥል ብዙቹ ጉዳዮች መፍትሔ እያገኙ መሄድ እንደሚችሉ ብዙ ማሳያዎች መሆናቸውን በማንሳት አስረድተዋል።

በአንፃሩ የፌዴራል ሥርዓት መነሻው የአብሮነት እሳቤ ሆኖ እያለ በነበሩ ሚዛን ያልጠበቁ የራስ አስተዳደርን የብቻ አስተዳደር አድርጎ የሚያዩና የእኔን ብቻ የሚያቀነቅኑ የእኛን የረሱ እሳቤዎች የፌዴራሊዝም ጽንሰ ሃሳብ ላይ የተዛባ ግንዛቤ እንዲኖር ተደርጓል ያሉት ዶክተር ኃይለየሱስ፤ በአጠቃላይም የፌደራል ሥርዓቱ በተለያዩ መመዘኛዎች ሲታይ በትክክል መሬት ወርዷል ማለት የማያስችሉ በርካታ ነጥቦች እንዳሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪም የፌዴራል ሥርዓትን በአግባቡ ለመተግበር የክልል መንግሥታት የሚያወጡት የክልል ስትራቴጂ እና የፌዴራል መንግሥት የሚያወጣው ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ በአንድ ሃገር ውስጥ እና ለአንድ ሕዝብ በተለያዩ አግባቦች የሚተገበር በመሆኑ የተቀናጀና የተናበበ ሊሆን ይገባዋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህም ሊመራ የሚገባው በሚታወቅ ሥርዓት መሆን እንደሚኖርበት እና በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ያለ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ የፌዴራል ሥርዓት በአንዴ ተገንብቶ የሚያልቅ ሥርዓት ሳይሆን ሂደት ነው። ሆኖም ሁሉም ሰው ሃገሪቱ ሕብረ ብሔራዊት ሀገር የመሆኗን እውነታ በመቀበል ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ለማጠናከር የበኩሉን አስተዋፅዖ ሊወጣ ይገባል። ይህን ነባራዊ እውነታ የአንዱን ማንነት በማጥፋት፣ አንደኛው ሌላውን እንዲውጥ በማድረግም ሆነ በሌሎች መንዶች ሊሻር የማይችል ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ይህ ሊሆን ስለማይችል ልዩነትን በማቻቻል የጋራ ዕድገት የሚመጣበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል።

# በኢኮኖሚ እድገቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ክፍለ ኢኮኖሚ በተሻለ ፍጥነት እንዲያድግና ከአጠቃላይ እድገቱ ያለው ድርሻ ከፍ እንዲል መሥራት ይገባል ብለዋል።

በ2015 ዓ.ም የሰባት ነጥብ አምስት በመቶ እድገት ለማስመዝገብ መታቀዱን አስታውሰው፤ ይህም አገሪቱ ሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚኖራት ከሆነ ሊሳካ የሚችል ነው ብለዋል።

እቅዱ ሀገሪቱ በጦርነት ውስጥ ሆና ካሳካቸው ያለፈው ዓመት እቅድ ጋር ብዙ ያልተራራቀ መሆኑን አስገንዝበው፤ በየቦታው የሚስተዋሉ ግጭቶችን በማስቆም ሰላም ማስፈን ከተቻለ፣ የግብይት ሥርዓቱ ከተስተካከለና የሕግ የበላይነት ተከብሮ ምርት በአግባቡ ከተመረተ የሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከታቀደው ከፍ ብሎ በሁለት አኃዝ የሚቆጠር ኢኮኖሚያዊ እድገት ልታስመዘግብ የምትችልበት ዕድል መኖሩንም ዶክተር አረጋ ጨምረው ገልጸዋል።



ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

# የጸረ ሙስና ትግል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኃላፊነት ሊወጡ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ዳይሬክተሯ ከንግግር ተሻግሮ መረጃና እውቀት ላይ የተመሠረተ ተግባር ማሳየት ይገባል በማለት፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን መለየት፣ ማጋለጥና ማረም፣ እንዲሁም የሥነ ምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታን በማጠናከር የልማትና የመልካም አስተዳደር ነቀርሳ የሆነውን ሙስና ከስር መሠረቱ ለመንቀል ሁሉም እንደየሚናው ቁርጠኛ መሆን ይገባል ሲሉ መክረዋል።

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፣ ሙስናን ለመግታት ጅምር እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም ከተሠራው ይልቅ ያልተሠራው ያመዝናል። በቀጣይ ከፍተኛ ጥረትና የተቀናጀ ርብርብ ካልተደረገ የሙስና ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ ዕድል ይፈጥራል።

የተቋማት የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራር ሥርዓት ዝርጋታ ክፍተት መኖር፣ ሕዝቡ በጸረ ሙስና ትግሉ በበቂ ሁኔታ አለመሳተፍ፣ የባለድርሻ ተቋማት የተቀናጀና የተደራጀ የጸረ ሙስና እርምጃ አለመውሰድና የሙሰኞችን የሥነ ምግባርና የሞራል መዛነፎች በበቂ ደረጃ አለማረም የጸረ ሙስና ትግል የሚፈለገውን ያህል ውጤት እንዳያስመዘግብ ያደረጉ ምክንያቶች እንደሆኑ ዳይሬክተሯ ገልጸዋል።

ተቋማዊ አደረጃጀትና አሠራር ማጠናከር፣ የሥነ ምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታና የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል አሠራርን ማጠናከር የጸረ ሙስና ትግል ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆን እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ለዚህም የመንግሥት ተቋማት አመራሮች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የመገናኛ ብዙኃን፣ ቤተሰብ፣ የትምህርት ተቋማትና ማኅበራዊ ተቋማት የተጠናከረ የጸረ ሙስና ትግል በኢትዮጵያ እንዲቀጣጠል የበኩላቸውን ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

ምክትል ርዕሰ አካዳሚው ዶክተር ወንድዬ ለገሰ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር፣ ሙስና የሀገር ነቀርሳ መሆኑን በመጥቀስ መንግሥት ይህንን ትኩረት አድርጎ እየወሰደ ያለው እርምጃ የሚያበረታታ ነው ብለዋል።

ዶክተር ወንድዬ ሙስናን ማጥፋት የውሳኔ ጉዳይ እንደሆነ በመጥቀስ መንግሥት ይህንን ትኩረት አድርጎ እየወሰደ ያለውን ርምጃ ሁሉም ሊደግፈውና ለተግባራዊነቱም ተባባሪ መሆን እንዳለበት አስታውቀዋል። አካዳሚው ግንዛቤ በመፍጠር የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣም ገልጸዋል።

በተጠናከረ ቅንጅታዊ አሠራር ሌብነትን እና ብልሹ አሠራርን መታገል እንደሚገባም የሁነቱ ታዳሚያን ተናግረዋል።

አካዳሚው ከጸረ-ሙስና ቀን በተጨማሪ የጸረ-ጾታዊ ጥቃትና የኤች አይቪ /ኤድስ ቀንን በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሁነቶች አክብሯል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ምሁራን ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ዘላቂ ሰላም ተገቢውን ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል!

ያለፉት አራት ዓመታት ለኢትዮጵያ ተስፋም ስጋትም ይዘው የመጡ ጊዜያት ናቸው። ከበጎ ጎኑ ብንነሳ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ያበበበት፤ ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ በነጻነት እንዲሳተፉ መድረኩ የተከፈተባቸው ወቅቶች ናቸው። በዚህም የኢትዮጵያ አንድነት መሰረት የተጣለበት ፤ በሀገሪቱ ታሪክ ነጻ ምርጫ የተካሄደበት፤ ምርትና ምርታማነት ያደገበት፤ የተጓተቱ ፕሮጀክቶች እንደገና ተነቃቅተው ለውጤት የበቁበት፤ ስንዴ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ኤክስፖርት እስከ ማድረግ የተደረሰበትና የህዳሴ ግድብ ብርሃን ያመነጨበት ተስፋ ሰጪ ዓመታቶች ነበሩ።

በሌላ በኩል ደግሞ እያንሰራራ የነበረው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከኮሮና መከሰት ጋር በተያያዘ ፈተና ውስጥ የወደቀበት፤ የፋብሪካዎች ምርታማነት ያሽቆለቆለበት፤ ሃገር በስጋት የተሸበበችበትና በዚህም በርካቶች የመንግስት እጅ ጠባቂ የሆኑበት ጊዜ ነበር። ኢትዮጵያ ይህንን ፈተና በቅጡ ሳትሻገር ከ40 አመታት ወዲህ የከፋ የተባለ ድርቅ ያጋጠመበት፤ የዩክሬንና የሩሲያም ጦርነት በርካታ የግብርና ፋብሪካና ፍጆታ ዕቃዎችን ከውጭ ለምታስገባው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ፈተና የሆነበትም ጊዜ ነው።

የኢትዮጵያ ፈተና በእነዚህ ብቻ አልተገታም። በፈተና ውስጥም ሆና ኢትዮጵያ እያስመዘገበችው ያለው የልማትና ዴሞክራሲ ጎዳና ያልተዋጠላቸው ወገኖች ሀገሪቱ በግጭትና በጦርነት አዙሪት ውስጥ እንድትቆይና በሂደትም እንድትፈራርስ ያለመታከት የሰሩባቸው ዓመታት ነበሩ። የኢትዮጵያን ውድቀት የሚመኙ አካላት በአራቱም የሀገሪቱ ማዕዘናት ግጭት፤ ሁከት፤ ብጥብጥና ብሎም ጦርነት እንዲነግስ አቅደው ሰርተዋል። በዚህም በተለያዩ አካባቢዎች መፈናቀል፣ስደትና ሞት ነግሶ ቆይቷል።

ጥቅምት 24 ቀን 2013 በሰሜን ዕዝ ላይ በተፈጸመው ክህደትም ኢትዮጵያ ህልውናዋን ለማስከበር ወደ ለየለት ጦርነት ገብታለች። ከጥቅምት 24 ቀን 2013 ጀምሮ በተካሄዱ ሶስት ዙር ተከታታይ ጦርነቶችም በርካቶች የጦርነቱ ሰለባ ከመሆናቸውም ባሻገር የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ክፉኛ ተጎድቷል። መሰረተ ልማቶች ወድመዋል፤ምርትና የእርሻ ስራዎች ተስተጓጉለዋል። በርካቶችም ቀያቸውን ለቀው ተሰደዋል። የተባበሩት መንግስታት በቅርቡ ይፋ ባደረገው መረጃም ከጦርነቱ ጋር በተያያዘም 26 ሚሊዮን ዜጎች የሰብአዊ ርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስትና ሕወሓት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ ባደረጉት የሰላም ስምምነት ሀገሪቱ ወደ ሰላም የተመለሰች ቢሆንም በጦርነት የላሸቀው ኢኮኖሚ ለማንሰራራት ዓመታት እንደሚወስድ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ እየገለጹ ነው። ሆኖም ይህንን እውነታ ባለመረዳት ወይንም በአንዳንድ ወገኖች በኩል ፖለቲካዊ ጫና ለማሳደር በሚመስል መልኩ ሴራ ሲደገስና ሕዝብና ሀገር ለማበጣበጥ ጥረት ሲደረግ ይስተዋላል።

ከዚህ በተቃራኒውም ምሁራን በአንድ መድረክ ተሰባስበው በፈተና ውስጥ ሆና ተስፋዋ የጎላውን ኢትዮጵያ እንዴት እናግዛት ብለው ሲመክሩም ተስተውሏል። ምሁራኑ በምክክራቸው የተለያዩ ልምዶችን በማንሳትና ተሞክሮዎችን በመቃኘት በሌሎች ሀገራት ያሉ ምሁራን ለሀገራቸው ዕድገትና ብሄራዊ ጥቅም ምን ሰሩ እኛስ ምን ይቀረናል? በሚለው ላይ ሃሳብ ተለዋውጠዋል። ይህንንም መነሻ በማድረግ ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸርና ምሁራኑ ለሀገራቸው ለማበርከት ከሚችሉት አስተዋጽኦ አንጻር የምሁራኑ የእስካሁኑ ክንውን በቂ አለመሆኑ በጥናትም ጭምር ተመላክቷል።

ምሁራን በዕለት ተዕለት ስራቸው ተማሪዎችን ከማነጽ ባሻገር ሀገር የተጋረጠባትን ችግር እንድትሻገር መፍትሄ በማመላከት ጭምር የማይተካ ሚና አላቸው።ኢትዮጵያ ደግሞ በዚህ ወቅት በተፈራረቁባት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ትከሻዋ የዛለ፤ ወገቧ የጎበጠ በመሆኑ አለሁልሽ የሚሏት የተማሩ ከልጆቿ የምትሻበት ወቅት ላይ ትገኛለች።ኢትዮጵያ የተጋረጠባት ችግር ከኢኮኖሚ አልፎ የሉአላዊነት ተግዳሮት መሆኑንም መረዳት ከምሁራን የተሰወረ አይደለም።

ስለሆነም ምሁራን ለሀገር ዕድገት፣ ሉዓላዊነት እና ሰላም መረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ የሚያበረክቱበት ወቅት ላይ ይገኛሉ። ብዙሃኑ ዜጋም ኢትዮጵያ ከህመሟ እንድትፈወስና ወደ ቀድሞ ዝናና ክብሯ እንድትመለስ የምሁራኑን በዕውቀትና በጥበብ የታጀበ መፍትሄ በጉጉት እየጠበቀ ነው።የኢትዮጵያ ምሁራን ደግሞ ይህንን የማድረግ አቅም አላቸው፤ እንደሚያደርጉትም አይጠረጠርም!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ሌብነትን የሚጠየፍ ትውልድ ለማፍራት

ሙሉቀን ታደገ

ባለፉት ጊዜያት በሀገራችን ሰላምና መረጋጋት ጠፍቶ ፈተናዎቿ አይለው በውስጥ ሆነ በውጭ ኃይሎች ሲደርስባት የነበረው ጫና በርትቶ ቆይቷል። አሁን ላይ ሰላምን ለማስፈን እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ተስፋ የሚፈነጥቁ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የሀገር እድገት የሚገታው ሌብነት እየተስፋፋ ነው።

በሀገራችን ማህበረሰብ ዘንድ ሌብነት ነውርና ጸያፍ ተግባር መሆኑ ሲነገር ኖሯል፤ ሌባ የተባለ ወይም ሲሰርቅ የተገኘ ሰው በህብረተሰቡ ዘንድም የሚወገዝና የተገለለም ነበር። ይህም ሆኖ በመንግሥት ስልጣን ሲሆን ግን « ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» በሚል ብሂል ሌብነት ሲበረታታ ይታያል። ህብረተሰቡ ሌባውን እያበረታታ ይብስ ብሎ ሌብነት የሚጠየፈውን የሚኮንንበት አጋጣሚዎችም አይጠፉም። እገሌ እኮ ባለስልጣን ሆነ ሲባል ብዙ ነገሮችን ከእሱ ይጠብቃል።

ሰውየው በባህሪው ሌብነትን የሚጠየፍ ቢሆን እንኳን ከራሱ ሰዎች ማለትም ከሚስቱ ጀምሮ ከቅርብ ሰዎቹ ሳይቀር ወደ ሌብነት የሚገፋፋው አካል አይጠፋም። ሁሉ በእጅህ ሁሉ በደጅህ ሆኖ ማድረግ እየቻልክ ለምን አታደርግም ። እገሌን አታየውም እንዴ በስልጣኑ ተጠቅሞ ከራሱ አልፎ ለዘመዶች ሳይቀር ያንበሸበሸውን ሀብትና ንብረት ተመልከት፤ ይልቅ ጊዜህን ተጠቀምበት የሚሉ ጎትጓቾች በዙሪያ አይጠፉም። በዚህ አጥፊ ምክርም በተፅዕኖ ውስጥ የሚወድቁ ሰዎች ይታጣሉ ማለት አይቻልም።

ስልጣን ላይ ያለው አካልም ስልጣን አግኝቶ በስልጣኑ ሳይጠቀም ቢወርድ ነገ እውን ሊቆጨው እንደሚችል በመገንዘብ መመዝበሩን ይያያዘዋል። ሰውየው በስልጣን ላይ እያለ ከተጋለጠና በህግ ጥላ ሥር ሆኖ ወደ ወህኒ ከወረድ በኋላ ደግሞ ሙስና በልቶ ነው በማለት ቀለል ሲያደርገው ይታያል። ይህ የሚፈጸመው ደግሞ ሌብነትን በጽኑ ይጠየፋል ከሚባለው ማህበረሰብ ውስጥ መሆኑ ለምን የሚለውን እንድንጠይቅና ያለፍንባቸውን ሥርዓቶች እንድንመለከት ያስገድደናል።

ባለፉት ሦስት አስርት ዓመታት በሀገራችን የታየው ሌብነት እንኳን ብንመለከት በቂ ነው። በወቅቱ የነበረው መንግሥትም የሰረቁ ባለስልጣናት ላይ ህብረተሰብ ጥቆማ ሲሰጥ ለሌባው አካል ሽፋን እየሰጠ ከነበሩበት ስልጣን ላይ በማንሳት ከፍ ባለ የተሻለ የሚበዘብዙበት ስልጣን ሲሰጥ ይስተዋል ነበር። ይህ የሚያሳየን የመንግሥት መዋቅራዊ አሠራር ጭምር ለሌብነትና ለብልሹ አሠራር የተጋለጠ እንደነበር ነው።

ስርአቱ ለሌብነት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ በርካቶች ሌብነትን ለመከላከል የተበጁ ስርአቶችን ሳይቀር ሆነ ብለው በማፍረስ የህዝብን ንብረት ለራሳቸው ጥቅም ሲያውሉ በስፋት ተስተውሏል። ለዚህም ሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ ባለቤት አልባ ህንጻዎች መገኘታቸው ሌብነቱ ምን ያህል ስር የሰደደ መሆኑን እና እንደ ህብረተሰብ ሌብነትን እየተለማመድን መምጣታችን ማሳያ ነው።

ከለውጡም በኋላ ቢሆን እየታየ ያለው ሌብነት ምንም አይነት መሻሻል የማይታየበት እንዲያው ከድጡ ወደ ማጡ የሚያስብል እየሆነ ነው። በተለይ ለህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት መንግሥት ደመወዝ እየከፈላቸው ለህብረተሰብ በነጻ አገልግሎት መስጠት እየተጠበቀባቸው ህብረተሰብን በማጉላላትና ለእንግልት በመዳረጋቸው ሳያንስ በግልጽ ጉቦን የሚጠይቁ አካላት ተበራክተዋል። ይህም የህብረተሰቡ የቀን ከቀን እሮሮ እየሆነ መጥቷል።

ሀገርን ከገባችበት ፈተና ለመታደግ ያላትን የሌላትን አቅም አጠራቅማ ደፋ ቀና በምትልበት በዚህ ወቅት የሀገርን ፈተና እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም መንግሥት አንዱን ቀዳዳ ሲደፍን ሌላ ቀዳዳ እያበጁ ለሌብነት እራሳቸውን እያዘጋጁ ያሉ ኃይሎች እየተበራከቱ ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ስብሰባ በተካሄደበት ወቅት ለምክር ቤት አባላት በሰጡት ምላሽ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የሰፈነው ሌብነት በጣም አታካች ሁኔታ ላይ ደርሷል። በተለይ ሀገር የገጠማትን ፈተና እንደ እድል የወሰዱ ሰዎች ቀይ መስመር የተባለውን የሌብነት ቀይ ምንጣፍ አድርገው በነጻነት እየተንሸራሸሩበት ነው። ይህም በሀገር የኢኮኖሚ ላይ እያስከተለ ያለው ጫና ቀላል አይደለም።

ህብረተሰቡ አገልግሎት ፈልጎ ጎራ የሚልባቸው የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት ከማፈጠን ይልቅ ግልጽነት የሌለው ብልሹ አሠራር በመከተል ለሚሰጡት የተንዛዛ አገልግሎት ጉቦ በመጠየቅ የማይገባቸውን ጥቅም ለማጋበስ ሲጣጥሩ መታየታቸው የተዘረጋው አሠራር ተጠያቂነትን ያላሰፈነ እንደሆነ አመላካች ነው።

የሌብነት ድርጊቱ የሚፈጸመው በተወሳሰበ ሰንሰለት በጥቅም በተሳሰሩ አካላት መሆኑን ህብረተሰቡ ይናገራል። ከፈጻሚ አካል ጀምሮ እላይ እስከተቀመጠ አመራር ድረስ ለሌብነትና ለብልሹ አሠራር የተጋለጡ መሆናቸውን የሚናገሩትም ብዙዎች ናቸው። ለእነዚህ አካላት ባልተገባ ድርጊታቸው የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲኖር በማድረግ በመንግሥትና በህብረተሰቡ መካከል ቅሬታ በመፍጠር ህዝቡን ለምሬት የሚዳርጉ ናቸው።

ሌላው ቀርቶ በመንግሥት አፍንጫ ሥር ቁጭ ብለው ሌብነት የሚፈጸሙ አካላት ሳይቀር ቶሎ ሳይደረስባቸው በመቅረቱ መንግሥትን ሳይቀር እያሳሳቱ የመንግሥትን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እየከተቱ ይገኛሉ። ለአብነት በአዲስ አበባ የኮንደሚንየም ቤት እጣ አወጣጥ የተከሰተው ድርጊትን ማንሳት ይቻላል።

በመሬት ጉዳይ የሚነሱ ቅሬታዎችንም ብንመለከት በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ከመሬት ዝርፊያ ጋር በተያያዘ የወረዳ ዋና ስራ አስፈፃሚን ጨምሮ በመሬት ጉዳይ ይወስኑ የነበሩ አመራሮች፣ባለሙያዎች፣ ደላሎችና በዚህ ድርጊት የተሳተፉትን በመለየት ለህግ እንዲቀርቡ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ ከ37 ተጠርጣሪዎች ውስጥ እስካሁን ድረስ 12 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ መደረጉ ከተማ አስተዳደሩ ሌብነቱ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተሰግስገው ባሉ አካላት ጭምር እንደሆነ አንዱ ማሳያ ነው ።

እንዲህ አይነት ሌቦች በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ተሰግስገው መገኘታቸው ሌብነትን ከሥር መሰረቱ ለመንቀል የሚደረገው ሂደት ላይ እንቅፋት ሆኗል። አሁን ላይ መንግሥትም ሌብነትን ለመከላከል ሀገራዊ ኮሚቴ በማቋቋም እያሳየ ያለው ቁርጠኝነት የሚበረታታ ቢሆንም ግልጽኝነት የሰፈነበት እና ተጠያቂነት ያለበት አሠራር መዘርጋት ደግሞ ከራሱ ከመንግሥት የሚጠበቅ ይሆናል።

ህብረተሰቡም በሌብነት ውስጥ ተቀባዩን አካል ብቻ ሳይሆን ሰጪውንም አካል ተጠያቂ የሚያደርግ በመገንዘብ ጉቦ ባለመስጠት፣ ሌብነትን የሚያስፋፉ ተግባራት ሲመለከት በመጠቆም የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት። ሌብነት የሚጎዳው ሀገርን ብሎም ህዝብን በመሆኑ ሁላችንም የድርሻችንን በመወጣት ሌብነትን የሚጠየፍ ተጠያቂ ዜጋን ማፍራት ይጠበቅብናል።

## ተጠየቅ

# “ብልሹ አሰራርን ለማስቆም በተሰራው ስራ አመራርና ሰራተኞች ተጠያቂ ተደርገዋል”

- ኢንጂነር ስጦታው አካለ
የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

አስመረት ብስራት

**በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገነቡ ህንፃዎች ጥራትና ደህንነታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ምን እየተሰራ ነው? ግንባታቸውስ በምን መልኩ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል? ህንፃው ተጠናቆ የአገልግሎት ፈቃድን ካገኘ በኋላስ ለተገቢው ግልጋሎት እየዋለ ነወይ? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ይዘን የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ስጦታው አካለ ጋር ቆይታ አድርገናል።**

**አዲስ ዘመን፦ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነቱ ምንድነው ?**

**ኢንጂነር ስጦታው፦** የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በከተማዋ ውስጥ እንደማንኛውም አስፈፃሚ ተቋም ግንባታና ግንባታ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን እንዲሁም በከተማዋ ውስጥ የሚሰሩ አጠቃላይ መሰረተ ልማቶችን የሚያቀናጅ የሚቆጣጠር እና ከግንባታ ፈቃድ ጋር የሚገናኙ አምስት ዋና ዋና እና 29 ዝርዝር አገልግሎቶችን የሚሰጥ ተቋም ነው።

ተቋሙ በየጊዜው በአዳዲስ አደረጃጀትና መዋቅር እየተሻሻለ እየሰፋ የመጣ ነው። በ2014 በጀት አመት በአዋጅ 74/2014 ተግባርና ኃላፊነቱ ተሻሽሎ ለበርካታ ተገልጋዮች አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ተቋሙ በከተማዋ የሚገነቡ ህንፃዎችን ፈቃድ የሚሰጥ እንደመሆኑ የፍቃድ አሰጣጥ ሂደቱ ምን ይመስላል የሚለውን ቢያብራሩልን?**

**ኢንጂነር ስጦታው፦** የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። የግንባታ ፈቃድ የሚፈልግ አንድ ተገልጋይ ከመሬት ተቋም የተሰጠው ህጋዊ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዞ ይመጣል ። በተጨማሪም ሌሎች የእዳና እገዳ ሰርተፍኬት ከዛው ተቋም ያቀርባል። እነዚህ ከተሟሉና የተገልጋዩ ማመልከቻ አስካለ ድረስ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል። ፍቃዱ ከተጠየቀ በኋላ በቅድሚያ የማጣራት ስራ ይሰራል። ይህ ሲባል ቦታው ለምን አገልግሎት እንደተፈቀደ፤ የአካባቢው ፕላን ምን እንደሚመስል፤ የህንፃው ከፍታ እና ሌሎች ዲዛይንና ፕላንን በሚያጣጥም መልኩ ታይቶ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል።

ፍቃድ ከተሰጠ በኋላ የተሰጠውን ጊዜ እንዲያጠናቅቅ የጊዜ ገደብ ይቀመጣል። የጊዜ ገደቡ እንደየ ግንባታው አይነት ሊረዝምና ሊያጥር ይችላል። በተሰጠው የጊዜ ገደብ ግንባታው መከናወኑ የግንባታ ክትትል ይደረጋል። ክትትሉ ግንባታው በጥራት እየተካሄደ መሆኑን፤ በምህንድስናው ዘርፍ ባሉ ባለሙያዎች ሙያዊ ምዘና እየተደረገ በየደረጃው ይከናወናል።

የሲሚንቶ ሬሾ፤ የብሎኬት ጥራት፤ የስራ አካሄድ ሂደት፤ የባለሙያዎች ብቃትን በተቀመጠበት ቀን ልክ በፍጥነት እየሰራ መሆኑን በመከታተል ግንባታው እስኪያልቅ ይሰራል። በዚህ የክትትል ሂደት ውስጥ በተለይም የጥራት ችግር ሲያጋጥም ስራውን በማስቆም እርማት እንዲወሰድ ይደረጋል። ከዚህም ባለፈ ቅጣት የሚጣልበት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ እገዳ ይደረጋል። በስህተት ጥራቱን ሳይጠብቅ ሾልኮ የተሰራ ግንባታ ከተገኘ በተለያዩ የላብራቶሪ ምርመራዎች ታይቶ ህንፃው እንዲፈርስ ይደረጋል።

መፍረስ ላይ ከመድረሱ በፊት የቅደመ ክትትል ስራ ይሰራል። አንድ መሀንዲስ ክትትል ሲያደርግ እለት እለት የሚሰራውን የግንባታ ደረጃ በማዘዝ ክትትል ስለሚያደርግ የግድ ካልሆነ በቀር የማስፈረስ ስራ አይሰራም። ከዚህ በተጨማሪ በከተማዋ ውስጥ ያሉ ያረጁ አደጋ ያስከትላሉ ተብለው የሚታሰቡ ህንፃዎች የማፍረስ ስራ ይሰራሉ። በዚህ መልኩ ነው እንደዚህ የግንባታ ቁጥጥርና ፍቃድ ተቀናጅተው የሚሰሩት።

**አዲስ ዘመን ፦ ተቋሙ ይሄን ያህል የቁጥጥር ስራ ላይ ትኩረት አድርጎ በኃላፊነት ስሜት የሚሰራ ከሆነ በተለያዩ ጊዜ ፈረሱ፤ ተናዱ ጉዳት አስከተሉ ሲባል የምንሰማቸው ህንፃዎች በምን**



**ምክንያት ነው?**

**ኢንጂነር ስጦታው፦** የትኞቹ ህንፃዎች ናቸው የተናዱት? መረጃው አለሽ? እኔ አንድ ያረጀ ህንፃ በመርካቶ ከመናዱ በስተቀር የማውቃቸው ቦታዎች የሉም። የመርካቶውም ቅርስ ነው ተብሎ እየተጠበቀ የቆየ ሲሆን ሌሎቹም ህንፃዎች በተገቢው መልኩ ካልተያዙ አደጋው የከፋ ሊሆን እንደሚችል ያስጠነቀቀ ነው። ይህ ህንፃ በተገቢው ላለመታየቱ የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ሊመለከተው ይገባ ነበር። ከእኛ ጋር የተያያዘ ግን የማውቀው የፈረሰ ህንፃ የለም።

**አዲስ ዘመን፦ ይህ ህንፃ ፈርሷል አልፈረሰም በማለት ስመከራከር ሳይሆን ውዱን የሰው ህይወት የሚያስከፍለን አደጋ እንዳይከሰት በተባለው ልክ ትኩረት ስለመሰጠቱ እንዲያረጋግጡልን ጭምር ነው ይሄን ጉዳይ ያነሳሁት፤ ምናልባትም ህንፃውን በሚከታተሉት ባለሙያዎችና ሌሎች ላይ የሚታይ የስነምግባር ጉድለት ሲኖር ቢችልስ?**

**ኢንጂነር ስጦታው፤** የስነምግባር ጉዳይ ተቋሙም ትኩረት አድርጎ የሚሰራበት ጉዳይ ነው። ከአመራር እስከታች ሰራተኛ የሆነ ሰው ስለ ህንፃው ደህንነት የማይጨነቅ ሰራተኛ፤ ስለ ግንባታ የኮንክሪት ሬሾ የኮንክሪት ጥንካሬ የማይጨነቅ ከሆነ ህንፃው አደጋ ላይ ነው የሚሆነው። በተለይ ደግሞ ግንባታውን የሚያከናውነው ኮንትራክተርና አማካሪ ስለሚሆን ባለቤት ስለማይሆን እንደ ባለቤት ያለመጨነቅ ሁኔታ አለ። ይህንን እንደባለቤት የማይጨነቅ ኮንትራክተርና አማካሪ ተቋሙ ጠበቅ ብሎ በንፅህና ተከታትሎ አስፈላጊውን እርማት ካልሰጠ ለህንፃው አደገኛ ነው የሚሆነው። ስለዚህ የቁጥጥር ጉዳይ ምንም ድርድር ውስጥ አይገባም።

ይህ ሲባል ግን የስነምግባር ጉድለት የለም ማለት አይደለም። አልፎ አልፎ ይታያል። ይህ ግን በተደረሰበት ልክ እርምጃ የሚወሰድበት አካሄድ እየተሰራ ነው። አመራርም ቢሆን፣ ባለሙያም ቢሆን ይጠይቃል። በበጀት አመቱ ሩብ አመት ማለትም ባለፈው ሶስት ወር ከስራ የታገዱ የታሰሩ የተለያዩ የቅጣት እርምጃዎች የተወሰደባቸው አሉ።

በአዲሱ አዋጅ ላይ ክትትሉንም ቅጣቱንም ጠበቅ ያደረገ መመሪያ በመኖሩ ለብልሹ አሰራር የሚጋለጥበት እድል እየጠበበ ነው። ይህ ቢሆንም ግን ሾልኮ የተገኘ ጥፋት ተቆጣጣሪ ባለሙያው ላይ ብቻ ሳይሆን ኮንትራክተሩም ፍቃዱን እስከመንጠቅ የሚደርስ ቅጣት እየተወሰደ ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ከስራው ስፋትና ስራውም ከሚያስከተለው የከፋ ጉዳት አንፃር ክትትሉ በቂ ነው ብለው ያምናሉ? ለቀጣይስ ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት ምን ምን ተግባሮች መከናወን አለባቸው?**

**ኢንጂነር ስጦታው፦** ከላይ በበጀት ዓመቱ ሩብ አመት እርምጃ ተወሰደባቸው ያልናቸው ሰራተኞችና አመራሮች 39 ናቸው። እነዚህም ይህን የስነ ምግባር ጥሰት ሲፈፅሙ የተደረሰባቸው ናቸው። በሶስት ወራት ውስጥ ይሄን ያህል ቁጥር ያለው ሰው ካገኘን የሚቀጥለው ሩብ አመት ቁጥሩ ሊጨምርም ሊቀንስም ይችላል። ሰው እንዲጠየቅ ዋና አላማ አድርጎ ከመስራት ይልቅ ችግሩ እንዳይፈፀም በተለያዩ አይነት መንገዶች በመጠቀም ለመከላከል ጥረት ይደረጋል።

የተያዙት ግን ባልተገባ መንገድ ሌሎችን ለመጥቀም የሞከሩ ናቸው። ይሄ እንዳይኖር ብዙ የህግ ማእቀፎችን አሻሽለናል። ብዙ የሙስና ምንጮችን አድርቀናል። ብዙ ለብልሹ አሰራር የሚያጋለጡ አሰራሮችን ፈትናል፤ ደንብ አፅድቀናል። አዋጅ ተስተካክሏል። የተለያዩ የህንፃ እስታንዳርድ፣ የውጭ ማስታወቂያ እስታንዳርድ የህንፃ ቀለም እስታንዳርድ አዘጋጅተናል።

አዲሱ የህንፃ ወይም የግንባታ መመሪያን አስተካክለነዋል ፤አሻሽለናል። እነዚህ ሁሉ ለሙስና ምንጭ ነበሩ። አብዛኛው ሰው ይቸገር ነበር።አሁን ቀለል ተደርገዋል፤ ተገልጋይ በቀላሉ ገንዘብ ሳልሰጥ መስተናገድ አልችልም እንዳይል አድርገነዋል፤ አሁን ተገልጋይ ለሙስና ለመክፈል አይገደድም። ሲስተሙ አሁን ቀሏል ፤አብዛኛው ነገር በኦላይን ነው የሚስተናገደው፤ እዚህ ቢሮ ውስጥ ያለ አገልጋይ ከማንም ባለጉዳይ ጋር ሳይገናኝ ብቻውን ስራውን ሰርቶ መጨረስ ይችላል። ከዚህ ውጪ ኦላይን ሲስተም መጠቀም የማይችሉ ሰዎች አሉ፤ እንደገና ደግሞ ያልተገባ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ በዚህ መንገድ የተገኘ ግድፈት ሊሆን ስለሚችል ቁጥሩ ያነሰ መስሏል።

እነዚህን የህግ ማእቀፎች ከማዘጋጀታችን በፊት ከላይ ተቀጡ ያልናቸው ሙያተኞች በቀን ውስጥ ሊያዙ የሚችሉ ሊሆን ይችል ነበር። አሁን ግን ሰፊ ርብርብ በማድረግ አሰራሩን በዘመናዊ መልኩ ለመቀየር በመቻሉ መሻሻሎች ታይተዋል።

አንቺ ከመምጣትሽ በፊት የገባው ባለጉዳይ ይዟቸው ከመጣቸው ማስረጃዎች መካከል አንድ ፎርጅድ ሰነድ በማቅረቡ እጅ ከፍንጅ ተይዞ ፖሊስ ይዞት ሲሄድ ተመልከተሻል። ምንም አይነት ስህተት የማይሰራበት መንገድ ተፈጥሯል።

**አዲስ ዘመን፦ተቋሙ ግንባታዎች ሲከናወኑ ምን ያህል ደህንነቱን የጠበቀ የግንባታ ሂደት እየተከናወነ ስለመሆኑስ ይከታተላል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፦** የእኛ ተቋም የግንባታ ፈቃድ ሲፈልግ የሚረጋገጠውን አረጋግጦ ፍቃድ መስጠት፤ ግንባታ ከተጀመረ በኋላ ደግሞ ሄዶ የግንባታ ጥራት፤ ማለትም በዲዛይኑ መሰረት እየተሰራ መሆኑ የቴክኒክ ስህተት እንዳይኖርበት እስከመጨረሻው ድረስ በመከታተል ህንፃው ሲጠናቀቅ አገልግሎት ለመስጠት ተዘጋጅቷል በማለት የመጨረሻውን የመጠቀሚያ ፍቃድ የመስጠት ኃላፊነት ነው ያለው።

ከዛ ውጭ ያሉ ደንብ መተላለፎች ሲኖሩ አይመለከትንም በማለት ከመተው ይልቅ ከደንብ ማስከበሮች ጋር በመሆን እርምጃ የሚወሰድበትን መንገድ እንፈልጋለን። እኛ ፍቃድ የሰጠነው ገንቢ መንገድ ላይ የግንባታ እቃውን አስቀምጦ የመንገድ ደህንነት ሰርአቱን ካስተጓጎለ ሊቀጣ ይገባል። ከደንብ ማስከበር ከአቅም በላይ ከሆነ የግንባታ ማስቆሚያ ይሰጠዋል፤ ስለዚህ ይህንን ለማድረግ የሚሞክሩ አይመስለኝም ግን ከአጠፉ ግንባታ እስከ ማስቆም እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

ሌላው የግንባታ ደህንነት ጋር የተነሳው ለመመለስ ይህ የህንፃ ላይ ደህንነት በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ወደኛ ሀገር ስንመጣ አለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በሙሉ ለመጠቀም ሙከራ ይደረጋል። ክሬንና ሊፍትን ጨምሮ የተለያዩ ለደህንነት የሚጠቅሙ ቁሶችን መጠቀም ይችላሉ።

ይህ ቢሆንም ግን አደጋ አይከሰትም ማለት አይቻልም። አንዳንዴ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ሌላ ጊዜ ደግሞ በቸልተኝነትም ሊመጣ ይችላል። በኛ በኩል ግን የደህንነት መጠበቂያ ቁሶች ላይ ምንም አይነት ክፍተት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ይደረጋል። ለምሳሌ ማንኛውም ሰው ሄልሜት ሳያደርግ፤ ሴፍቲ ሹዝና አንፀባራቂ ልብስ ሳያደርግ ወደ ግንባታው ቦታ እንዳይገባ ይደረጋል። ይህም አደጋ ቢደርስ የአደጋውን መጠን ለመቀነስ ይረዳል።

የህንፃ ደህንነት ግንባታው ውስጥ በሚሰሩ ሰራተኞች ብቻ ሳይሆን ግንባታው ያለበት አካባቢ ያሉ ቤቶች ላይ አደጋ እንዳያደርስ መከለያ የሚባል ግንባታው በመከለያ ተሸፍኖ እንዲሰራ ይደረጋል። ብዙ ጊዜ ብሎኬትና ሌሎች የግንባታ ቁሶች ወድቀው ሰው ላይና ንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የሚደረግ ሲሆን ይህንን ሳያደርጉ የሚገነቡ አካላት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፦ ግንባታቸው የተጠናቀቀ ህንፃዎች ላይ እንደምንመለከተው ለአካል ጉዳተኞች መወጣጫ ተብለው የሚሰሩ የዊልቸር መውጫዎች ተደርጓል ለማለት በሚመስል መልኩ ዲግሪያቸው ከፍ ያሉ ይሆናሉ፤ ሊፍቶችም ቢሆኑ አይነስውራን ሲጠቀሙባቸው የሚችሏቸው አይነት ድምፅ ያላቸው ሲሆኑ አይታይም፤ የህብረተሰቡ**

# ተጠየቅ



**ግማሽ ክፍል የሆኑ አካል ጉዳተኞችን ያማከለ ህንፃ ከማስገንባት አንፃርስ ተቋሙ ምን ይሰራል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** ህንፃዎች የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጣቸው አንዱ ባፀደቀው ፕላን መሰረት ተጠናቀቀ ወይ? የሚለው ነው የሚታየው። የቀረበው ዲዛይንና ፕላን የሚፀድቀው ደግሞ አካል ጉዳተኛን ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ እናረጋግጣለን። ለዚህም አንዱ ሊፍት ነው፤ ሁለተኛው የውልቸር መውጫ ከሊፍት ውጭ ያለ ደረጃ ነው። የዚህ ድግሪ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ በምን ያህል ድግሪ መሰራት አለበት የሚለው ተቀምጧል። የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃዱ የሚሰጠውም ይሄው ተረጋገጦ ነው።

ሁለተኛው ከባለአራት ፎቅ በላይ ለሆኑ ህንፃዎች ጠቅላላ ሊፍት እንዲኖራቸው እናስገድዳለን። ሊፍት ሳይኖረውም የመጠቀሚያ ፈቃድ አይሰጠውም ማለት ነው። ሊፍቶቹ በህንፃው ስፋት መሰረት የሊፍት እስታንዳርድ ወጥቶለት ይሰራል። አካል ጉዳተኞችን ያማከለ ህንፃ እንዳይኖር ለማድረግ መመሪያው ላይ በጉልህ ተቀምጧል። አዲሱ መመሪያም ከዚህ በፊት የነበሩ አይነት ችግሮች እንዳይከሰት ምንም ክፍተት የሌለባቸው እንዲሆኑ እየሰራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ካስፈለገ የውልቸር መወጣጫዎቹ የቆሙ ተራሮች የሚመስሉበት ህንፃዎችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፤ እነዚህ ያልናቸው ህንፃዎችስ በምን መስፈርት ነው ታዲያ የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸው?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** እንደዚህ አይነት ህንፃዎች አሉ ከተባለ ያንን ህንፃ ሲቆጣጠር የነበረ ባለሞያ ፍቃድ የሰጠበት የራሱ ምክንያት ይኖረዋል። ወይ ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ውስጥ ያለበት ይሆናል፤ ወይ ሌላ አማራጭ አስቀምጧል፤ ይህ ሲባል ምናልባትም በቤዝመንቱ በኩል ሊፍት ለአካል ጉዳተኛው ተዘጋጅቶ ሊሆን ይችላል፤ ምናልባትም አንቺ ያየሽው ለእቃ ማጓጓዣ የተሰራ ይሆናል። ለአካሉ ጉዳተኛ የሚሆን የውልቸር መወጣጫ ካልሆነም ፍቃድ አይሰጥም።

ይህን የምለው ሙሉ ለሙሉ ከችግር የፀዱ ህንፃዎች አሉ ላይባል ቢችልም ይህ ህንፃ በተገቢው መልኩ ሁሉንም ማህበረሰብ ያማከለ አገልግሎት ሳይሰጥ ለአገልግሎት ክፍት ያደረገው ባለሞያ መቼም ቢሆን ከተጠያቂነት አያመለጥም። ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅ ህንፃው ሳይገባው ከተፈቀደለት ከሀያና ሰላሳ አመታት በኋላም ሊጠየቅ ይችላል። የተባለው ሆኖ ቢገኝ ህንፃው ባለቤት አፍርሶ እንዲያያስተካክል ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፤ አንድ ህንፃ የአገልግሎት ፍቃድ ካገኘ በኋላ በትክክል ህንፃውን ስተፈለገው አገልግሎት እያዋለ ነው የሚለውን ትቆጣጠራላችሁ? ይህ ሲባል የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች አንዳንዴ ሳልተሰሩበት አላማ ሲውሉ ይታያሉና ቁጥጥሩ እስከምን ድረስ ነው?**

**ኢንጂነር ስጦታው፤** ህንፃዎች ለተሰሩበት አገልግሎት ብቻ እንዲውሉ የመቆጣጠር ሀላፊነት የተሰጠው ለተቋሙ ነው። አንዱና ከሁሉ በላይ ትኩረት የሚሻው የህንፃ ቤዝመንቶች ለተፈቀደላቸው ለፓርኪንግ አገልግሎት ብቻ እንዲውሉ የማድረግ ቁጥጥር ይደረጋል። ነገር ግን የህንፃ መጠቀሚያ ፍቃድን ካገኙ በኋላ የተፈቀደለትን አገልግሎት በመተው ለጭፈራ ቤቶች፤ ለመጋዘኖች ሊውል ይችላል።

ህንፃዎች ሲለሙ ህንፃው ውስጥ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ተገልጋዮች መኪናቸውን መንገድ ዳር በማቆም ከተማይቱን ማጨናነቅ እንዳይኖር ያደርጋል። ፍቃዱም የፓርኪንግ መሰረተ ልማትን ላሟላ ህንፃ የሚሰጥ ነው። ፍቃዱን ከወሰደ በኋላ ግን መቀየር እንዳይችል በየስድስት ወሩ ህንፃው ኦዲት ይደረጋል። የቀየረ ካለ አጠቃላይ የህንፃው ባለቤት የንግድ ፍቃዱ ተነጥቆ ህንፃው ይታሸጋል።

ይህ ደግሞ ለንግድ ቢሮም በሚላክ ደብዳቤ የንግድ ፍቃዱም እንዲሰረዝ ይደረጋል። አሁን በተሻሻለው መመሪያ መሰረት ቅጣቱ ከፍ ተደርጓል። ከዚህ ቀደም የነበሩ ችግሮች እንዳይደገሙ ቅጣትና ቁጥጥር እየተደረገ ነው ያለው።

**አዲስ ዘመን፡- ፍቃድ አሰጣጡም ሳይ ቀጣይ ቁጥጥሩም ሳይ በብልሹ አሰራር የተነሳም የህንፃ ፓርኪንጎች ሳልተገባ አገልግሎት ሲውሉ ይችላሉ። ከላይ እርምጃ እንደተወሰደ ቢነገርም አሁንም የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ከመኪና ማቆሚያነት ውጪ ስሆነ አገልግሎት የሚውልበት ሁኔታ ይታያል፤ ስለዚህስ ጉዳይ ምን ይላሉ?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** የብልሹ አሰራር ጉዳይ በአንድ ጊዜ ይስተካከላል ፤ይጸዳል የሚባል ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን አሁን በሰራናቸው ሪፎርሞች ያሉ ችግሮችን ቀንሰናል፤ በዚህኛው አመትም ዜሮ ለማድረግ እየሰራን እንገኛለን። በዚህ ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙት የማያዳግም እርምጃ ይወሰድባቸዋል። የአሰራር ክፍተት ያለባቸውን የአሰራር ማሻሻያዎች እያደረግን እናስተካክለዋለን። ከአሁን በፊት የነበረው ፍቃድ አሰጣጥ ህግ ራሱ ለሌባ ምቹ ነበር። አሁን ያለው ግን ለባለሙያውም ጥሩ ነው።

በህገ ወጥ መንገድ ለሚሰሩት ምቹ የነበረበት ጊዜ አሁን ቀሎ ተገልጋዩ ቀላሉን መንገድ እንደጠቀም መብቱን እንዲያስከብር ህጉን እንዲያውቅ ይሰራል። ከዚህ ያለፈው ቅጣት ይጣላል። አሁን የአሰራር ስርአቱን በማዘመን ባለጉዳይና አገልጋይ ሳይገናኙ አገልግሎቶች የሚያገኙበት መንገድ እየተመቻቸ ነው።

ይህ ሲደረግ ባለጉዳይ መንገድ ላይ የሚያጠፋውን ጊዜ ይቀንሳል። ተሽከርካሪውን ይዞ መንገድ ሲያጨናንቅ አይታይም። ባለሙያ ጋር መጥቶ ደጅ አይፀናም። ዛሬ ነገ ከነገ ወዲያ በመባል የሚደረግ መመላለስ አይኖርም ። ኦላይኑ ላይም ስህተት እንዳይፈጠር የበላይ አመራሮች ይቆጣጠሩታል። አንድ ማመልከቻ መች እንደገባ ፤ በስንት ጊዜ ጉዳዩ መጠናቀቅ እንደሚኖርበት ይታያል፤ ተገልጋዩ ካልተስተናገደ ሲስተሙ ስለሚያመለክት በምን ምክንያት ሙያተኛው እንዳላስተናገደ በመጠየቅ ብቻ ስራው እንዲቀላጠፍ ያደርገዋል።

ፕላን ስምምነት፣ የግንባታ ፈቃድ፣ ክትትል እና መሰል አገልግሎቶችን በዚህ እየሄድን ነው። በተቻለ መጠን ካሉ 20 በላይ ዝርዝር አገልግሎቶች አብዛኞቹ በኦን ላይን ሲስተም አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፤ ህንፃዎች ሲገነቡ ቤዝመንቱ ስፓርኪንግ፤ የተወሰነው የህንፃ ክፍል ስቢሮና ስተስያዩ አገልግሎቶች፡- የተቀረው ደግሞ ስመኖሪያ ቤት እንዲሆን ቅይጥ አገልግሎትን የሚሰጡ ህንፃዎችን ስመገንባት መመሪያ ወጥቶ እንደነበር ይታወሳል።አሁን በዛ ልክ እየተሰራ ነው?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** አጠቃላይ በከተማዋ የሚገነቡ ትላልቅ ህንፃዎች ላይ የቅይጥ አገልግሎት የሚሰጡ ህንፃዎችን ለማድረግ ፕላን ህጉ ይፈቅዳል። በፕላን ህጉ መሰረት ማስፈፀም ደግሞ የተቋሙ ኃላፊነት ነው። በተለይም መሀል ከተማ የሚባሉ አካባቢዎች ላይ ቅይጥ የተባሉት አይነት ህንፃዎች እየተገነቡ ነው።

ቤቶቹ መኖራቸው የከተማዋን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል። ህንፃዎቹ በሙሉ ልክ እንደመኖሪያ አፓርትመንት በመሆን በራሳቸው የንግድ ውድድር መሰረት ተወዳድሮ መከራየት ለቻለ በሙሉ በማቅረብ ይሰራል።

**አዲስ ዘመን፡- የከተማይቱን ውበት ስመጠበቅ በሚል የህንፃ ቀለም ቅብ እስታንዳርድን ከማስጠበቅ አንፃር ተቋሙ ምን እየሰራ ነው?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** የህንፃ ቀለም እስታንዳርድ ከባለፈው አመት ጀምረን ጥሩ ውጤት መጥቶበታል፤ እስታንዳርድም ተዘጋጅቷል። ከተማዋን ከመዘበራረቅ ቆንጆ እይታን ለመፍጠር፤ ለደህንነትም፤ለውበትም ችግር ሆኖ የነበረውን የህንፃ ቀለም መዘበራረቅ እና ሌሎች ስሜትን የሚጎዱ ቀለማት ለማስቀረት እየተሰራ ነው።

በዚህ መሰረት ሞዴል የሆነ አካባቢን፤ ቀጥሎ ክፍለ ከተማን፤ቀጥሎ እንደ ከተማ ወደ አንድ በመምጣት ከተማዋ የራሷ ብራንድ እንዲኖራት፤ ከተማዋ በአለም አቀፍ ደረጃ የምትታወቅበት የራሷ አንድ ቀለም እንዲኖራት ነው እሳቤው። የሚረብሹ ጤናን የሚጎዱ በፀሀይ ጊዜ ለማየት የሚያስቸግሩ የመስተዋት ህንፃዎች እንዳይኖሩ ያደርጋል።

በእስታንዳርዱ የተመረጡለት ቀለሞች አንድ ሁለት ሶስት አይደሉም በርካታ ናቸው። ከእነዛ ውጪ ሰው እንዳይጠቀም እየተደረገ ነው። ለምሳሌ ግራጫ ቀለም ውስጥ ራሱ እንደ ክሬም ከለር፤ ላይት ግሬይና ከ20 በላይ የሆኑ አማራጮች ይኖሩታል።

እንደ ገንቢ ግንባታ ፍቃድ ሲጠይቅ መጨረሻ ላይ ህንፃው ምን መምሰል እንዳለበት ቀድሞ ይታወቃል። ግንባታ ፍቃድ ሲጠይቅ የወሰደው የፕላን ስምምነት ላይ የህንፃውን ከፍታ፤ በሩን፣ የመስታወት አይነቱን፣ቀለሙ ምን እንደሚመስል ቀድሞ ያስቀምጣል። የሚመርጠው ቀለም ለአካባቢው የተፈቀደው ቀለም ሲሆን ከአጎራባች ቀለም ኮዶች ጋር የሚጣጣመው ታይቶ የተጣጣመ ቀለም ይመረጣል። በአሁኑ ሰአት በርካታ የቀለም እስታንዳርዶች እየተሰሩ ነው ያሉት። ሞዴል አካባቢ የሆነው ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ውስጥ ያለ አካባቢ ተጀምሯል ያም በጣም በጥሩ ሂደት ላይ ነው ያለው።

የከተማዋ ቀለም እስታንዳርድ ሲመረጥ ከስነልቦና ባለሙያዎች ጋር በመመካከር፤ የቀለም ባለሙያዎች፤ የኪነ ህንፃ ምሁራንን በማካተት ቀለሞቹ ነዋሪው ህዝብ ላይ ምንም ጫና እንደማይፈጥሩ ተረጋግጧል። አንዲት ከመቶ አመታት በላይ እድሜ ያላትን ከተማ በአንዴ መቀየር የማይቻል መሆኑ አሳቤ ውስጥ በማስገባት ከተማዋ ያላት ቀለም አይነት ሊለይ ተሞክሯል። በከተማዋ ያሉት ህንፃዎች ከስልሳ እስከ ሰባ በመቶ ድረስ በግራጫ የቀለም ክልል ውስጥ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

የህንፃ ቀለም እስታንዳርድ ሲቀመጥ የከተማዋ የአየር ሁኔታ፤ የአካባቢው የአፈር አይነት፤ የሙቀት መጠኑ ይታያል፤ መልከአ ምድሩ ምን እንደሚመስለ ታይቶ ቀለም ምርጫ ይወሰናል። በአጠቃላይ በብዛት በከተማዋ ያሉት ቀለማት ግራጫ ቀለም ውስጥ ያሉ ናቸው።

ለውጥ ሲመጣ ካሉ አሉባልታዎች የሚነሱት ለውጥን ከማይቀበሉ ሰዎች ነው እንጂ ከሙያተኞች ጋር የተወሰነ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለውበት ካነሳን የውጭ ማስታወቂያዎችስ በምን መልኩ ይመራሉ፤ አንዳንዴ ያስፈባቸው ማስታወቂያዎች ተስጥፈው ይታያሉ፤ ከከተማዋ ውበት አንፃር ያለው የውጪ ማስታወቂያ እስታንዳርድ እንዴት ይታያል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** አንዱ የከተማዋን ውበት ከመጠበቅ አንፃር የተሰራው ነገር የውጭ ማስታወቂያን በህግ የመምራት ስራ ነው። ከዚህ ቀደም የውጭ ማስታወቂያ መመሪያ ተዘጋጅቶ በዚያ መሰረት የት አካባቢ በምን አይነት ደረጃ ያሉ ማስታወቂያዎች መሰቀል አለባቸው የሚል እስታንዳርድ ተቀምጧል። ከዚህ ቀደም የተሰቀሉ ሁሉም ማስታወቂያዎች በክፍለ ከተሞችም በወረዳም ደረጃ በርብርብ እየተነሳ ይገኛል።

አሁን ወጥ በሆነ መንገድ ተቋሙ እየፈቀደ ዘመናዊ በሆነ መልኩ እንዲሰቀል እየተደረገ ነው። በከተማዋ ዲጂታል እስክሪኖች እንዲበዙ ተደርገዋል። ቢልቦርዶችም ቢሆኑም ደረጃቸውን የጠበቁ ቢል ቦርዶች እንዲኖሩ ተደርጎ ከዛ ውጭ ያሉት በሙሉ ግን ይነሳሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በአገልግሎት አሰጣጡ ሳይ ያስበትን ተግዳሮች ቢገስፁልን?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** አገልግሎቱ ላይ ከአቅም በላይ የሆነው ችግር ህገ ወጥነት ነው። ይህን ከተማ በፕላን መምራት አለብን፤ በፕላን የማይመራ ከተማ ለነዋሪዎቹ ምቹ አይሆንም፤ ስለዚህ ህገወጥ ግንባታ ህገወጥ ያልተፈቀዱ የውጭ ማስታወቂያ ፍቃዶች ሌሎች ህገወጥ ተግባሮችንም ለመከላከል ህብረተሰቡም መረባረብ አለበት።

ከተማዋ የጋራችን እንደመሆኗ ሁሉም አካላት በጋራ የሚሰሩባት፣ በጋራ የሚኖሩባትና በጋራ የሚንከባከቧት ከተማ እንድትሆን መሰራት ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ውድ ጊዜዎን ሰውተው ስቃስ ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም አመሰግናስሁ።**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# አወዛጋቢው ምናባዊ ገንዘብ(ክሪፕቶ ከረንሲ)፤

## (ክፍል ሁለት)

በመጀመሪያው ክፍል ለንባብ በበቃው መጣጥፌ በምናባዊ ገንዘብ ወይም በክሪፕቶ ከረንሲ ኢንዱስትሪው በ3ኛ ደረጃ የሚገኘው ግዙፉ FTX EXCHANGE እንዴት እንደተነሳና እንደተንኮታኮተ አውስቻለሁ ። ዛሬ ደግሞ የዚህን ግዙፍ ኩባንያ ብልሹ አሰራር ፍንጭ ስለሰጠው ተቋምና ኢንዱስትሪው ምን ያህል ለሌብነትና ለዘረፋ የተጋለጠ መሆኑን የሚያሳይ ተጨማሪ አብነት አነሳለሁ ።

የFTX የፋይናንስ አቅም ጉዳይ አደጋ ላይ መሆኑን ፍንጭ የሰጠው ኮይንዴክስ በተባለ ድረ ገጽ ነው ይለናል ቢቢሲ ፤ በዚሁ ድረ ገጽ የወጣው ዘገባ ፤ የFTX እህት ኩባንያ የሆነው አላሜዳ የሚደገፈው በራሱ በFTX በተቋቋመ ፈንድ እንጂ በገለልተኛ ተቋም አለመሆኑን የሚያጋልጥ ነው ።

ወዲያው"The Wall Street Journal " አላሜዳ የሚጠቀመው ከFTX ደንበኞች ቁጠባ መሆኑን ይፋ አደረገ። የመጨረሻው መጀመሪያ የFTX ተፎካካሪ የነበረው ባይናንስ ከቀናት በኋላ ከFTX የተገኙ የክሪፕቶ ሽርክናዎችን መሸጡ የተሰማለት ነው ይላል ቢቢሲ ።

የባይናንስ ክሪፕቶ ከረንሲ ዋና ስራ አስፈጻሚ ቻንግፔንግ ዣው 7.5 ተከታዮች ወዳሉት ቲዊተሩ ይሄድና ኩባንያው FTX ላይ ያለውን ሽርክና ሊሸጥ እንደሆነ ይፋ አደረገ ። በነገራችን የ22ኛው የአለም ዋንጫ ስፖንሰር ከሆኑ ድርጅቶች አንዱ ባይናንስ አንዱ ሲሆን በፖርቹጋላዊው ኮከብ ክሪስቲያን ሮናልዶ አማካኝነት ማስታወቂያውን እያስነገረ ይገኛል ። የFTXን ማስታወቂያም እነ ማት ዲመን ሲሰሩለት እንደነበር እዚህ ላይ ልብ ይሏል ።

ከዚህ በኋላ ነጮች እንደሚሉት የተቀረው ታሪክ ነው። The rest is history . በሁኔታው የተደናገጡ የFTX ደንበኞች ፤ ከFTX ክሪፕቶ ከረንሲ የነበራቸውን በቢሊየን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘባቸውን ከባንኮች አወጡ። የክሪፕቶ ከረንሲ ንጉሰ ነገስት ሳም ባንክማን ፍሬድ እንደ ሮማን ኢምፓየር ተንኮታኮተ ። ሚሊየኖችን ለኪሳራ ዳረገ ።

ባለሽርክናዎች ገንዘባቸውን እንዳያወጡ ከተደረገ በኋላ ባንክማን ፍሬድ FTXን ከውድቀት የሚታደጉ ኩባንያዎችን ማፈላለጊ ጀመረ ። መክሰሩን አውጆ ጣጥሎ ከመሔዱ በፊት የሚታደጉትን ኩባንያዎች እያፈላለገ ሳለ ባይናንስ ሊደርስለት ቃል ከገባ በኋላ ፤ መልሶ FTX ፈንዱን አላግባብ ስለተጠቀመ መንግስት ምርመራ ስለከፈተበት ልታደገው አልችልም በማለት ሸሸ። ከአንድ ቀን በኋላ FTX መክሰሩን ይፋ አደረገ። ንጉሰ ነገስቱ ዘውዱንም ዙፋኑንም በአንድ ጊዜ አጣ። የሚሊየኖች የFTX ሽርክና አጣብቂኝ ላይ ወደቀ። ገንዘባቸውን ስለማግኘታቸው እርግጠኛ አለመሆናቸውን ተረዱ ።

ሳም ባንክማን ፍሬድ በቲዊተር ገጹ ለተፈጠረው ሁሉ ይቅርታ እጠይቃለሁ በማለት ከFTX ዋና ስራ አስፈጻሚነት ለቀቀ። በቲዊተር ሁኔታዎች በዚህ መልኩ በመጠናቀቃቸው ደንግጫለሁ። ነገሮች ይስተካከላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ አለ። ይሄን ተከትሎ የቢትኮይን ዋጋ አሽቆለቆለ ፤ ብዙዎች የነገው ተረኛ ከሳሪ ክሪፕቶ ከረንሲ ማን ይሆን አሉ ። አዲሱ የFTX ኃላፊ ጆን ሬይ 3ኛ በሰራሁባቸው አመታት ሁሉ እንደዚህ ያለ ዝርክርክ ድርጅት ገጥሞኝ አያውቅም ማለታቸውን የእንግሊዙ ዘ ጋርዲያን ጋዜጣ ያወሳል።በአሜሪካ አንቱ የተባሉት የኩባንያዎች መዋቅር ማሻሻያ ጠበብት ጆን ሬይ የFTXን አወዳደቅ ታይቶ የማይታወቅ ሲሉ ይገልጹታል ።

በነገራችን ላይ ጆን በግዙፉ የኢነርጂ ኩባንያ ኢንሮን ኪሳራ ወቅት የመዋቅር መሻሻያ በማድረግ ባመጡት ለውጥ ስማቸው በበጎ ይነሳል ።በዘርፉ አራት አስርት አመታትን የተሻገረ የካበተ ልምድ ያላቸው ጆን እንደ FTX በብልሹ አሰራር የጨቀየና የቁጥጥር ስርዓት የሌለው ስድ ኩባንያ አላየሁም ይላሉ ። FTX አቅምና ብቃት በሌላቸው ጥቂት ግለሰቦች የሚመራ እና የማይታመን የፋይናንስ ሪፓርት ያለው ድርጅት መሆኑን ይናገራሉ። አብዛኛው የFTX ሀብት ተሰውሯል ወይም ተዘርፏል። ለዚህ የበቃው ኩባንያው በጥቂቶች መዳፍ ስር በመውደቁ ነው ይላሉ ጆን ሬይ ፤

የኩባንያው መንኮታኮት የክሪፕቶ ከረንሲውን ገብያ ክፉኛ አናግቶታል ። የቢትኮይን የገብያ ዋጋ ያሽቆለቆለ ሲሆን ፤ በርካታ የክሪፕቶ ከረንሲ ኩባንያዎች ደግሞ ኪሳራ እያስመዘገቡ ነው ይለናል ጋዜጣው ። መጭው ዘመን ለዘርፉ ፈታኝ ነው ።

የFTX ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ባህማስ ለሰራተኞችና አማካሪዎች በድርጅቱ ፈንድ ቤትና መኪና ይገዛ ነበር ይላሉ አዲሱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ።ድርጅቱ ይሄን የሚያደርገው መርህን በመጣስ መሆኑ ሳያንስ ምንም አይነት ሰነድ አለመያዙ ያሳዝናል ። ዞሮ ዞሮ ከዚህ እንዝህላልነትና ኬረዳሽነት በላይ አደገኛ ማጭበርበርና ዘረፋ መፈጸሙ ልብ ሊባል ይገባል ይላሉ ጆን ።

በፋይናንሽያል ታይምስ ጋዜጣ እጅ የገባ ሚስጥራዊ ሰነድ FTX ከመውደቁ አንድ ቀን በፊት 1 ቢሊየን ዶላር የሚደርስ ፤በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ገንዘብና የተለያዩ ንብረቶች የነበሩት ሲሆን እዳውም 9 ቢሊየን ዶላር ነበር። ጆን ሬይ ወደ ኩባንያው ከመጡ በኋላ ግን በFTX ካዝና የተገኘው የ740 ሚሊየን ዶላር ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ክሪፕቶ ከረንሲዎችን ብቻ ናቸው ።በካዝናው የተገኘው ከኩባንያው አጠቃላይ ሀብት ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ይላሉ ዋና ስራ አስፈጻሚው ።

የFTX መጠባበቂያ ፈንድ የሚያስተዳድረው አላሜዳ ለቀድሞው ዋና ስራ አስፈጻሚ ሳም ባንክማን፤ 1 ቢሊየን ዶላር አንስቶ በብድር መስጠቱን እና ለምህንድስና ዳይሬክተሩ ኒሻድ ሲን 543 ሚሊየን ዶላር እንዲሁ ማበደረጉ ጆን ሬይ ይፋ አድርገዋል ።የቀድሞው ዋና ስራ አስፈጻሚ ባንክማን ፍሬድ በስሩ ካሉም ሆነ ከእህት ኩባንያዎች ጋር የሚጻጻፈው ፤ ደብዳቤዎቹንና መልዕክቶችን ወዲያው ወዲያው ብዙም ሳይቆዩ በገዛ እጁ የሚያጠፋ መተግበሪያ በመጠቀም ስለሆነ ማስረጃ ማግኘቱን ፈታኝ አድርጎታል ።

ብዙዎቹ የFTX ውሳኔዎችና አሰራሮች በስራ አመራር ቦርዱ ሳይጸድቁ ይፈጸሙ ስለነበር ለዚህ አስደንጋጭ ውድቀት ዳርጎታል ይላሉ ባላደራው አዲሱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ።በመላው አለም የሚገኙ ተቆጣጣሪዎች በFTX ላይ ምርመራ ጀምረዋል ይላል The Economist መጽሔት። የአሜሪካ ፍትሕ ሚንስቴርና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት/ሴኔት/አበክሮ ምርመራ መጀመሩ ከፍ ብሎ ተመልክቷል ። በFTXና በእህት የክሪፕቶ ከረንሲ ኩባንያው ብልሹ አሰራር መኖሩ እንደተሰማ በ72 ሰዓት ውስጥ ሸሪኮቹ ተሯሩጠው 6 ቢሊየን ዶላራቸውን ወስደዋል። አበው "በእንቅርት ላይ ቆረቆር "እንዲሉ መክሰሩን ለመንግስት አመልክቶ ከለላ እንደጠየቀ ውስጥ አዋቂ እንደሆነ የሚገመት የኮምፒውተር ሰርሳሪ/hacker/470 ሚሊየን ዶላር እንደመነተፈው መጽሔቱ ይገልጻል ።

ነገርን ነገር ያነሳዋልና አለምን ጉድ ስለሰራችው የክሪፕቶ ንግስት ላንሳና ምናባዊ ገንዘብ ምን ያህል ለማጭበርበር እንደተጋለጠ ተጨማሪ አስረጅ እንመልከት። ፈልጎ አስፈልጎ ያጣት ኤፍቢአይ/FBI/ ሰሞኑን በጥብቅ ከሚፈልጋቸው 10 አደገኛ ተጠርጣሪዎች ዝርዝር አካቷታል። የታይም መጽሔት በሰው ልጅች ታሪክ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ማጭበርበር ይለዋል። ትውልደ ቡልጋሪያ ጀርመናዊ ናት ። ዋንኮይን ከተሰኘው አጭበርባሪ ኩባንያ ጋር ተያይዞ ስሟ በአለም ናኝቷል። ቢቢሲ የውሃ ሽታ የሆነችው የክሪፕቶ ንግስት ሲል የምርመራ ዘገባ ሰርቶባታል ።

ምን አልባት ተገድላ ይሆናል የሚሉ አሉ ። አይ በፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ማንነቷን ቀይራ ጀርመን እየኖረች ነው የሚሉም አልታጡም ። አይ ዱባይ ታይታለች ፤ የለም ራሽያ ነው ያለችው እየተባለች መንፈስ ሆና አርፋዋለች። በማጭበርበር ወንጀል ተጠርጥራ በመላው አለም እየታደነች ነው ። ከተሰወረች 5ኛ አመቷን ይዛለች ። ከ4 እስከ 15 ቢሊየን ዶላር በማጭበርበር የምትጠረጠረውና የክሪፕቶ ንግስት በሚል ቅጽል የምትታወቀው ዶ/ር ሩጃ ኢግናቶቫ ዕምጥ ትግባ ስምጥ ከተሰወረች 5ተኛ አመቷን ይዛለች።

ኤፍቢአይ ቢታከተው ማንነቷን ሳትቀይር አልቀረችም ማለት ጀምሯል ። በፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ወይም በሌላ መንገድ መሆኑ ነው ። ዕድሜዋ በ40ዎቹ የሚገመተው የቡልጋሪዋ ዕንስት አፍቢአይን ጨምሮ በኢንተርፓል የምትታደነው ዋንኮይን/Onecoin/በተሰኘ ክሪፕቶከረንሲ በተፈጸመ እጅግ ከፍተኛ ማጭበርበር ነው ።

ኤፍቢአይ በ2017 ዓም የዕስር ማዘዣ ይዞ ለጥያቄ ማፈላለግ ሲጀምር ነው የክሪፕቶ ንግስቷ ድንገት የውሃ ሽታ የሆነችው ይላል የቢቢሲው ሊዎ ሳንድስ። ነገሩ ወዲህ ነው በ2014 ዓም ራሱን ክሪፕቶከረንሲ ብሎ የሚጠራው ዋንኮይን፤ ከረንሲውን ለሚያሻሽጡለት ኮሚሽን እንደሚከፍል ይፋ አደረገ። ሆኖም ዋንኮይን እንደሌሎች ክሪፕቶከረንሲዎች ዋስትና ወይም መተማመኛ የሚሰጥ የብሎክቼይን አሰራር አልዘረጋም።

የኤፍቢይ መርማሪዎችም ሆነ የፌደራል አቃቢ ሕጎች ዋንኮይን ክሪፕቶከረንሲ ሳይሆን የማጭበርበሪያ ስልት ነበር የሚሉት ለዚህ ነው ። የማንሀተኑ አቃቢ ሕግ ዳሚን ዊሊያምስ ንግስቷ የማጥመጃ መረቧን የጣለችው ሕዝበ አዳም ከክሪፕቶከረንሲ ጋር እልል በቅምጤ የሚልበትን ትክክለኛ ጊዜ መርጣ ነው ይላሉ ። ኤፍቢይ ባለፈው ሰኔ 23 በ8 የተለያዩ ወንጀሎች ጠርጥሮ የከሰሳትን የክሪፕቶ ንግስት ያለችበትን ለጠቆመ 100ሺህ ዶላር በወሮታ እንደሚከፍል ቃል ገብቷል።

ኤፍቢአይ ይሄን ማስታወቂያ ማስነገሩ ዶ/ር ኢግናቶቫን ለመያዝ ያግዘዋል ይላል የዋንኮይንን ማጭበርበር በምርመራው ያጋለጠው የቢቢሲው ጄሚ ባርትሌት ፤ የክሪፕቶ ንግስቷን መያዝ አዳጋች ያደረገው እጇ ላይ ይገኛል ተብሎ የሚገመተው ረብጣ ግማሽ ቢሊየን ዶላር ነው ይላል የምርመራ ጋዜጠኛው ባርትሌት።

አበውስ ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ አይደል የሚሉት ፤ ሀሰተኛ ማስረጃዎችን በማዘጋጀት የተካነች መሆኗና ገጽታዋን መቀያየሯ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ ያደርገዋል ይላል ባርትሌት፤"ዶ/ር ኢግናቶቫ ለመጨረሻ ጊዜ የታየችው በ2017 ዓም ከትውልድ ሀገሯ ቡልጋሪያ ወደ ግሪክ ስትበር ነው ይለናል ቢቢሲ፤ በተለይ ባርትሌት እንዲያውም ሞታም ሊሆን ይችላል እስከ ማለት ደርሷል ።

በዋንኮይን ገንዘቧን የተጭበረበረችው ጄን ማከአዳም እሷም ሆነች ጓደኞቿ እስከ 250ሺህ ፓውንድ የሚደርስ እንደተበሉ ለቢቢሲ ተናግራለች ። ጓደኛዬ ሊያመልጠን የማይገባ የኢንቨስትመንት እድል ስትል መልዕክት ትልክልኛለች። ከዚያ ወዲያው በዌቢናር ሊንኩን ተጠቅሜ ዋንኮይንን ተቀላቀልሁ ትላለች ማከአዳም ያቺን ዕድለ ቢስ ቀን ስታስታውስ ።

መጭበርበሬን የተረዳሁት ከወራት በኋላ ነው ። ራሷን የክሪፕቶ ንግስት ብላ የምትጠራው ዶ/ር ሩጃ ኢግናቶቫ ቢትኮይንን የሚፎካከር ዋንኮይን የተሰኘ ክሪፕቶከረንሲ ፈጥሪያለሁ በማለት በማይጨበጥ ተስፋ እየሞላች ቢሊዮኖችን ኢንቨት እንዲያደርጉ ታግባባ ነበር ሲል ያስታውሳል የቢቢሲው ባርትሌት ፤ በ2016 ሰኔ ግም ሲል ዓም የዛን ጊዜዋ የ36 አመት የንግድ ሰው ዶ/ር ሩጃ ኢግናቶቫ ከአፍ እስከ ገደፍ በአድናቂዎቿና በተከታዮቿ በተሞላው በታዋቂው የዌምብሌ አሪና/የመሰብሰቢያ አዳራሽ/በውድ ቀሚሲ ተውባ በአልማዝ ጉትቻ አጊጣና ደማቅ ቀይ ሊፕስቲክ ተቀብታ ብቅ ስትል አዳራሹ በጩኸትና በፉጨት አስተጋባ ።

ዋንኮይን በአለማችን ታላቁ የክሪፕቶከረንሲ ለመሆን እየገሰገሰ መሆኑን ፤ በየትም ቦታ ማንኛውንም ክፍያ መፈጸም እንደሚያስችል ለአድናቂዎቿ ገለጸች ይለናል ባርትሌት ፤ ቢትኮይን ዋጋው ከሽርፍራፊ ሳንቲሞች ተነስቶ በ2016 ዓም አጋማሽ ላይ ወደ መቶ ዶላሮች ማሻቀቡ የብዙ ኢንቬስተሮችንና ሌሎችን ቀልብ መሳቡና ተፈላጊነቱ ማደጉ ይነገራል ። ዶ/ር ሩጃ ዋንኮይን ቢትኮይንን በቅርቡ እንደሚዘርረውና በሁለት አመታት ውስጥ ማንም ስለቢትኮይን እንደ ማያወራና ታሪክ እንደሚሆን በመፎከር በአሪናው የታደሙ የደጋፊዎቿን ልብ አሞቀች ።

ወቅቱ በመላው አለም የሚገኙ ሰዎች ዋንኮይን ላይ ኢንቨስት በማድረግ የዚህ አዲስ ክስተት አካል ለመሆን የቋመጡበት ነበር ይላል የምርመራ ጋዜጠኛው ባርትሌት ፤ ለቢቢሲ ሾልኮ የደረሰ ሰነድ በዚሁ አመት የመጀመሪያዎቹ 6 ወራት ብቻ እንግሊዛውያን 30 ሚሊየን ፓውንድ ኢንቨስት ማድረጋቸውን ያስረዳል። እንግሊዛውያን በአንድ ሳምንት ብቻ ዋንኮይን ላይ 2ሚሊየን ፓውንድ ኢንቨስት አድርገዋል። ከነሐሴ 2014 እስከ 2017 ዓም ከመላው አለም ከፓኪስታን እስከ የመን ፣ ከብራዚል እስከ ፓሊስታይን ፣ ከሆንግኮንግ እስከ ኖርዌ 4 ቢሊየን ፓውንድ ዋንኮይን ላይ ኢንቨስት አድርገዋል።

የሚያሳዝነው ይላል የምርመራ ጋዜጠኛው እነዚህ ሁሉ ኢንቨስተሮች ያላወቁት ነገር ይልና ፤ ከዚያ በፊት ግን ክሪፕቶከረንሲ እንዴት እንደሚሰራ ያብራራል ። በዘርፉ ሙያ የሌለው ማንኛውም ሰው በቀጥታ ድረ ገጽ ውስጥ ገብቶ ስለ "ክሪፕቶከረንሲ"ቢጎለጉል ፤ ግራ የሚያጋቡና የሚያምታቱ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ውጤቶችን ይዘረግፍለታል። ስለሆነም ገንዘብን የሚያህል ነገር እንዲህ ባልለየለት ነገር ላይ ማፍሰስ አይመከርም ይላል ባርትሌት። ለዛሬ በዚህ ላብቃ ። ፈጣሪ የተጀመረውን ሰላም ያጽናልን !

አሜን ።

# የዲጂታል ፋይናንሻል ግብይት ተጠቃሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ወቅቱ ቴክኖሎጂን በሁሉም አማራጮች በመጠቀም ከዘመኑ ጋር አብሮ መዘመንን የግድ ብሎ የሚጠይቅበት ነው፡፡ ኢትዮጵያም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የዲጅታል ዓለምን እየተቀላቀለች ባለችበት በዚህ ወቅት በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተግባራዊ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በተለይም የዜጎችን ሕይወት ቀለል ማድረግ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ከፍተኛ ትኩረትን የሚሰቡ ናቸው፡፡ ቴክኖሎጂን ከመተዋወቅ ባለፈ ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ዕለት ተዕለት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የመተዋወቅ ዕድል እየተፈጠረ ያለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

ከሰሞኑም የክፍያ ሥርዓቶችን ቀላልና ለሁሉም ሰው የተመቸ እንዲሆን ማድረግ የሚያስችለው ሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን አክሲዮን ማህበር አዲስ የክፍያ ስርዓትን ይፋ አድርጓል፡፡ ሳንቲም ፔይ የክፍያ ስርዓት በወጣትና አንጋፋ በሆኑ ሥራ ፈጣሪዎች የተቋቋመ አገር በቀል ድርጅት ሲሆን፤ ኢትዮጵያን ወደ ዲጅታሉ ዓለም ለመቀየር የተቋቋመ የፋይናንስ ድርጅት ስለመሆኑም ተነግሯል፡፡

አዲስ የክፍያ ስርዓትን ይዞ የመጣው የሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን አክሲዮን ማህበር የኢትዮጵያን የዲጅታል ዓለም ከፍ ማድረግ የሚችልና ከዓለም አቀፍ ተቋማትና የፋይናንስ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን ፍጥነት እየተሳሰረ የሚገኝ ነው፡፡ ድርጅቱ በኢትጵያ የክፍያ ስርዓት ውስጥ ማገልገል እንዲችል ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባገኘው ህጋዊ ፈቃድ መቋቋም እንደቻለም ተጠቅሷል፡፡ ሳንቲም ፔይ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ አህጉር ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ ከገንዘብ ንክኪ ነጻ በማድረግ የዘመናዊ ግብይትን ለማስጀመር ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ እየሠራ ያለ የገንዘብ ድልድይ ነው፡፡

የሳንቲም ፔይ የቦርድ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው ኢትዮጵያ ቀደምት ስልጣኔ የነበራት፤ ሰፊና አኩሪ ታሪክ ያላትና ተከባብረው የሚኖሩ ሕዝቦች ባለቤት ስለመሆኗ አንስተው፤ ብዙዎቹ የዓለም አገራት መገበያያ ገንዘብ ሳይኖራቸው ኢትዮጵያ በአክሱም ዘመነ መንግሥት የመገበያያ ገንዘብ ኮይን የነበራት መሆኑን አስታውሰዋል፡፡ ገንዘብና የገንዘብ ዝውውር ለአገር ዕድገት ዋናው ምሰሶ መሆኑም አስረድተው፤ ለአንድ ሀገር ጤናማ እንቅስቃሴና ዕድገት ገንዘብ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ መዘዋወር አለበት፡፡ ለዚህም ባንኮች በፋይናንሻል ሶሉሽን በመጠቀም ሥራቸውን እንዲያቀለጥፍ ማድረግ የሚገባቸው እንደሆነም አንስተዋል፡፡

ዓለም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ዕለት ተዕለት በሚያስደንቅ ፍጥነት እየተቀየረች እንደሆነ ያነሱት ፕሮፌሰር ዳንኤል፤ በተቀየረውና በመቀየር ላይ ባለው ዓለም በቀደመ ጊዜ አሰራርና ልምድ መጓዝ አዋጭ እንዳልሆነ ገልጸው፤ አዋጭ ካለመሆኑም በላይ በዘመኑ የሚመጡ ችግሮችን መቋቋም አይቻልም ብለዋል፡፡ በተለይም በዚህ ዘመን ገንዘብን በቤት ውስጥ መደበቅና ቆፍሮ ማስቀመጥ ጊዜው ያለፈበት እንደሆነ ሁሉ ገንዘብን ይዞ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስም እንዲሁ ዘመኑን የዋጀ አይደለም፡፡ ለዚህም ሳንቲም ፔይን የመሰሉ ዘመናዊ የክፍያ ስርዓቶች ሊበራከቱ ይገባልም ብለዋል፡፡

‹‹በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት በሚኖር እንቅስቀሴ ሁሉ ገንዘብ በእጅ ይዞ መንቀሳቀስ ጊዜው አይደለም›› ያሉት ፕሮፌሰር ዳንኤል፤ በአሁን ወቅት ዓለም በሙሉ ካርድ እየተጠቀመ እንደሆነ በመጥቀስ ለአብነትም ማስተር ካርድ፣ ቪዛ ካርድ፣ ዩኒየን ፔይ፣ አሜሪካን ኤክስፕረስና ሌሎችም የሚገኙበት እንደሆነ አስረድተው፤ ይህም ገንዘብ ሳይሆን ቴክኖሎጂ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ዓለም ተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የገንዘብ ዝውውር በማድረግ ግብይት መፈጸም ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ኢትዮጵያም ከዚህ ውጭ መሆን አትችልም በማለት ሲያስረዱ፤

ዓለም በፈጣን የስልጣኔ ጎዳና ላይ በመሆኗ ኢትዮጵያም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ስርዓት ብቁ መሆን ይኖርባታል፡፡ ይህ ካልሆነና ዛሬም በድሮ አሰራር እንስራ ካልን ከዓለም ገበያ ውደድር የሚያስወጣት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የገንዘብ ኖቶች ህትመት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ ጫናው ይበረታል፡፡ ስለሆነም መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶችን መጠቀም የግድ በመሆኑ የውጭ ዜጎች የሰሩትን ኢትዮጵያውን ለምን አይሰሩም በሚል ቁጭትና በይቻላል መንፈስ ሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶልሽንን ማቋቋም ተችሏል፡፡

ድርጅቱ በኢትዮጵያውያን ወጣቶች የተሰሩ የተለያዩ ሶፍትዌሮችን ማበልጸግ የቻለ ሲሆን በተጨማሪም ባንኮች ለፖስና ለሶፍትዌር ግዢ የሚያወጡትን ከፍተኛ ወጪ መቀነስ አስችሏል፡፡ በቀጣይም ለባንክ የሚሆኑ የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በመሥራት ባንኮች ከከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መዳን እንዲችሉ ያደርጋል፡፡ በአሁን ወቅትም ባንኮች ለፖስ የሚወጡትን ዋጋ 20 ጊዜ በመቀነስ በተሻሉ የፖስ ማሽኖች በመተካት የውጭ ምንዛሪን ማዳን ተችሏል፡፡ ከውጭ ባንኮች ጋር መሥራት የሚያስችል መደላድልም ተፈጥሯል፡፡ ከአገር ውጭ ባሉ ከጎረቤት ሀገራት ጭምር መሥራት የሚችል በመሆኑ በቅርቡም ከአውሮፓ ባንኮችና አስር ሺህ ከሚደርሱ የአሜሪካን ባንኮች ጋር መሥራት የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

የኢፌዴሪ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ትዕግስት ሀሚድ በኩላቸው፤ የሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን አክሲዮን ማህበር በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘረፉን ለማሻሻልና አጋዥ የሆኑ ሥራዎችን ከስድስት ባንኮችና ከቴሌ ብር ጋር በመተባበር ሥራውን የጀመረ መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ የዲጅታል ምህዳሩንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የበለጸገ ማህበረሰብን መፍጠር የሚያስችላትን ከፍተኛ አቅም መገንባት ባትችልም በዲጅታል ምህዳሩ አቅም በመፍጠር፣ የተለያዩ ዕውቀቶችንና ክህሎቶችን በማደራጀት ላይ የምትገኝ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

መንግሥት ቴክኖሎጂ የመጪው ጊዜ ወሳኝ መወዳደሪያ መሆኑን በማመን መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ እና ልዩ የፈጠራ ችሎታ ላላቸው እንዲሁም ቁርጠኛ ለሆኑ ግለሰቦች አዳዲስ ቢዝነሶችንና አገልግሎቶችን እንዲጀምሩ አስቻይ ሁኔታዎችን እየፈጠረ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን አክሲዮን ማህበርም መንግሥት የክፍያ ሰርዓት ላይ ያደረጋቸውን የፖሊሲ ማሻሻያዎች እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ወደ ምህዳሩ የገባ የክፍያ ስርዓት እንደሆነ ገልጸው፤ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ወደ ተግባር የሚያስገባው የቴክኖሎጂ ስርዓት በኢትዮጵያ የዲጅታል ዘርፉ ላይ የተፈጠረውን ክፍተት የሚሞላ በመሆኑ የሚበረታታ ነውም ብለዋል፡፡

‹‹መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁን ወቅት የቁጥጥር ስርዓትን ማሻሻል ችሏል›› ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዲጅታል የፋይናንሻል አገልግሎት ሰጪዎችን በማካተትና አዋጁን በማሻሻል በዘርፉ አቅም ያላቸው የዲጅታል የክፍያ ስርዓትን የሚያቀርቡ ተቋማት እንዲበራከቱ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ይህም የአገሪቱን የፋይናንስ ስርዓት የዘመነ በማድረግ ማህበረሰቡም ለዘርፉ ምቹና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ ሳንቲም ፔይ በአገሪቱ ያለውን የዲጅታል ፋይናንሻል ግብይት ተጠቃሚ የሆነ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚያግዝ ሥርዓት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክፍያ ስርዓትን በማዘመን የተለያዩ የፋይናንሻል መድረኮች ማለትም ባንኮችና የክፍያ ሞባይል ዋሌት መተግበሪያዎች መካከል የክፍያ ስርዓትን ለመፍጠር የመጣ በመሆኑ በዘርፉ ያለውን እጥረት በከፍተኛ መጠን ሊቀርፍ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

ድርጅቱ ሀገሪቷ ለፖስ ማሽኖች መግዣ በየዓመቱ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚቀንስ እንደሆነ የታመነበት ሲሆን፤ ከዚህም ባለፈ ቴክኖሎጂው በኢትዮጵያ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ ላይ ያልተመሰረተ ዘመናዊ የገንዘብ ዝውውር እንዲመሰረት ያደርጋል፡፡ የገንዘብ ዝውውሮችን ምቹና ቀልጣፋ እንዲሁም ከማጭበርበር የጸዳ እንዲሆንም ያስችላል፡፡ መንግሥት ለጥሬ ገንዘብ ህትምት የሚያወጣውን የውጭ ምንዛሪ በእጅጉ ከመቀነስ ባሻገር አገሪቷ የያዘችውን የዲጅታል ኢትዮጵያ የ2025 ስትራቴጂ ዕቅድ ከማሳካት አንጻር ሳንቲም ፔይ የራሱን አሻራ ማኖር የሚችል ነው ያሉት ምክትል ዳይሬክተሯ፤ ማህበረሰቡም በፋይናንስ ዘርፍ ያለውን የኋላ ቀር አሰራር ቀልጣፋ፣ ጊዜ ቆጣቢና ከጥሬ ገንዘብ ንክኪ ነጻ የሆነውን ፋይናንሻል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የራሱን ሚና እንዲወጣም አሳስበዋል፡፡

የኢትጵያን የዲጂታል ዓለም ከፍ ማድረግ ያስችላል የተባለውና በኢትዮጵያውያን ተመስርቶ ይፋ የሆነው የሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን አክሲዮን ማህበር አገር በቀል እንደመሆኑ ተደራሽነቱም ሰፊ ነው በማለት ያስረዳው የድርጅቱ መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ወጣት ትንሳኤ ደሳለኝ ነው፡፡ እንደ ወጣት ትንሳኤ ገለጻ፤ የክፍያ ሥርዓቶችን ቀላልና ለሁሉም ሰው የተመቸ ለማድረግ እየሠራ ያለ ተቋም ሲሆን በወጣትና አንጋፋ በሆኑ ሥራ ፈጣሪዎች የተቋቋመ አገር በቀል ድርጅት እንደሆነም ገልጿል፡፡

ድርጅቱ በኢትዮጵያ የክፍያ ስርዓት ውስጥ ኦፕሬተር ሆኖ እንዲያለማ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፍቃድ አግኝቶ በሐምሌ ወር 2014 ሥራ መጀመሩን አንስተው፤ ሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን አክስዮን ማህበር፤ ሦስት አይነት የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቶችን ይዞ መምጣቱንም አስረድቷል።

ሳንቲም ፔይ ይፋ ያደረጋቸው፤ ፖስ (ተንቀሳቃሽ የክፍያ መተግበሪያ)፣ ዩኒፋይድ ፔይመንት ኢንተርፌስ (ዩ ፒ አይ) (ባንኮችን የሚያስተሳስር የክፍያ ስርዓት) እና ፔይመንት ጌትዌይ (በኢንተርኔት የሚደረጉ ክፍያዎችን የሚያስተሳስር) የተባሉ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቶችን ነው። እነዚህን የክፍያ ሥርዓቶች ከስድስት አጋር ባንኮች ማለትም ከአቢሲንያ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ቡና ባንክ፣ አዋሽ ባንክ አማራ ባንክ፣ ብርሃን ባንክ፣ ይሙሉ እና ከቴሌብር ጋር በመተባበር ተግባራዊ ማደረግ ተችሏል።

ይህ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓትም በኢትዮጵያ ደህንነት መረብ ኤጀንሲ የደህንነት ምርመራ ሰርተፊኬት ያገኘ ሲሆን፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም፤ በፒሲ አይ ኤስ ኤስ ሲ (PCSSC PAYMENT CARD INDUSTRY SECURITY STANDARDS COUNCIL) በኩል ደህንነቱ መረጋገጡን የቦርድ ሰብሳቢው ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው ሲያስረዱ፤ ሳንቲም ፔይ ከገንዘብ ንክኪ ነጻ የሆነ ዲጂታል እና የዘመናዊ ግብይት ተጠቃሚ የሆነ ማህረሰብን ለፍጠርና፤ የክፍያ ሥርዓትን ለማዘመን እየሠራ የሚገኝ ነው ብለዋል፡፡ በዚህም መሠረት ሀገራዊ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቱን ለማፋጠን ፖስ ማሽኖችን ጨምሮ ሦስት አዳዲስ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቶችን በማምጣት የዲጂታል ፋይናንስ ኢንዱስትሪውን መቀላቀል እንደቻለም ገልጸዋል።

ተንቀሳቃሽ ፖስ ማሽኖቹ ለነጋዴዎች ምቹና ከተለያዩ የክፍያ ሥርዓቶች ጋር የተገናኙ መሆናቸውን የገለጸው ዋና ሥራ አስኪያጁ ወጣት ትንሳኤ፤ ኔትወርካቸውም አሁን ካሉት ፖስ ማሽኖች 65 በመቶ ድረስ የተሻሉ መሆናቸውን አስረድቷል። በተጨማሪም በላያቸው ላይ በተገጠሙላቸው የፖስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ አማካኝነት፤ ችግሮች ሲከሰቱ ከቢሮ ሆኖ ማወቅና ማስተካከል ስለሚቻል የጥገና ጊዜና ወጪን ከመቀነስ አንጻር ጠቀሜታቸው ከፍተኛ እንደሆነም አስረድቷል። ባንኮችም ለፖስ የሚያወጡትን ዋጋ በ20 በመቶ በማሳነስ ትልቅ የውጭ ምንዛሪ ወጪን ማዳን እንደሚያስችል ተናግሯል።

ተንቀሳቃሽ ፓስ ማሽኖቹ የውጪ ሀገራት የክፍያ ካርዶችን የሚቀበሉና ማስተናገድ የሚችሉ መሆናቸውን ያነሳው ወጣት ትንሳኤ፤ በቅርቡም ከአውሮፓ ባንኮች እንዲሁም ከ10 ሺ በላይ የሆኑ የአሜሪካን ባንኮች ወደ ሥርዓቱ የሚገቡበት ሁኔታ ስለመፈጠሩና አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ስለመሆናቸው አስረድቷል። በተጨማሪም ዩኒፋይድ ፔይመንት ኢንተርፌስ (ዩ ፒ አይ) ባንኮችን የሚያስተሳስር የክፍያ ስርዓት ሲሆን፤ የሁሉም ባንክ ተጠቃሚዎችን በአንድ ቦታ ፈጣን አገልግሎትን እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑን ተገልጿል፡፡ ፔይመንት ጌትዌይ ደግሞ በኢንተርኔት የሚደረጉ ክፍያዎችን የሚያስተሳስርና፤ የኦን ላይን ክፍያዎችን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው እንደሆነም ተነግሯል።

የሳንቲም ፔይ ፖስ ማሽኖችን በመጠቀም የታክስ፣ የአገልግሎቶች፣ የኢንተርኔት፣ ትራፊክ፣ DSTV እና የአየር መንገድ ክፍያዎችን ማከናወን የሚቻል ሲሆን፤ በቀጣይ ሁለት ዓመት ውስጥም ሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን 70 ሺ የፖስ ማሽኖችን በመላው ሀገሪቱ ለማሰራጨት ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በዚህም ከ250 ሺ በላይ ተገልጋዮች ይጠቀሙበታል ተብሎ ይጠበቃል።

**ሳንቲም ፔይ ከገንዘብ ንክኪ ነጻ የሆነ ዲጂታል እና የዘመናዊ ግብይት ተጠቃሚ የሆነ ማህበረሰብን ለመፍጠርና የክፍያ ሥርዓትን ለማዘመን እየሠራ ይገኛል፡፡**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የሀሜት ልማድ

ዋለልኝ አየለ

አንድ ጋዜጠኛ ከዓመታት በፊት በማህበራዊ ገጹ የጻፈው ትዝብት ትዝ አለኝ።ሚዲያ ውስጥ ከመግባቱ በፊት በኢህአዴግ ዘመን በነበረው የመንግሥት ጉዳዮች ኮምኒኬሽን ይሰራ ነበር።እዚያ ሲሰራ ያጋጠመውን ነው የጻፈው፡፡

ወደ አርባ ምንጭ ለሥራ ይሄዳሉ።የሄዱት የመንግሥት ኮምኒኬሽን ለሚሰራው ጥናት ነው።በጥናቱ ማወቅ የተፈለገው መንግሥት በሚሰጠው የመሰረተ ልማት አገልግሎት የሕዝቡን ትክክለኛ የልብ ትርታ ማወቅ ነው፡፡

በየቴሌቭዥኑ እና ሬዲዮው የሚታየውና የሚሰማው ሕዝቡ በመሰረተ ልማት ያገኘውን አገልግሎት ሲያደንቅና ሲያመሰግን ነው።እዚህ ላይ ታዲያ አንድ ሀሜት አለ፤ ጋዜጠኛው ቀድሞ ‹‹እንዲህ ነው ማለት ያለባችሁ›› ብሎ ይነግራቸዋል የሚል ወቀሳ በየጊዜው የምንሰማው ነው።

ይህን ሀሜት የሚያውቀው የመንግሥት ኮምኒኬሽን ሰራተኛ (ጋዜጠኛ መባል ይችላል) ጋዜጠኛ መሆኑን ሳያሳውቅ እንደማንኛውም መንገደኛ ሆኖ ያገኘውን ሁሉ ይጠያይቃል።የተጠቀመውን ዘዴ ተጠቅሞ ስለመሰረተ ልማት ይጠይቃቸዋል።የሚነግሩት ሁሉ መንግሥትን ወቀሳ ነው።መንግሥት የመሰረተ ልማት ተጠቃሚ እንዳላደረጋቸው ነው፡፡

በኋላ ጋዜጠኛ መሆኑን አሳውቆ ‹‹አሁን የነገራችሁኝን ምንም ሳትቀንሱ ንገሩኝ›› ብሎ ካሜራውን ደቀነ።የነገሩት ግን በተቃራኒው ነበር።መሰረተ ልማት እንደተሟላላቸው፣ መንግሥት ልማት ላይ ጠንክሮ እየሠራ እንደሆነ ነው የተናገሩት።ጋዜጠኛው እንደዚያ በሉ አላላቸውም፤ እንዲያውም እሱ የፈለገው ትክክለኛው ችግር እንድነገር ነበር፡፡

ሰዎቹ ካሜራ ፊት በተቃራኒው ለማውራታቸው ብዙ ነገር ሊባል ይችላል።የመንግሥትን ችግር የተናገረ ይታሰራል፣ የሆነ ጥቅም አያገኝም… ስለሚባል ፈርተው ነው ሊባል ይችላል። ወይም በየቴሌቭዥኑና ሬዲዮው የሚሰሙት አድናቆት ብቻ ስለሆነ በካሜራና መቅረጸ ድምጽ ፊት የሚወራው ምስጋና ብቻ ነው ስለሚመስላቸው ይሆናል፡፡

በነገራችን ላይ ይሄ ነገር በተደጋጋሚ ያስተዋልኩትና የታዘብኩት ነው።በሆነ ጉዳይ ላይ አስተያየት ስጠይቅ የሚነግሩኝ ያንን የተማረሩበትን ነገር አይደለም፤ በአብዛኛው መገናኛ ብዙኃን ላይ የሚሰሙትን ነው። እንደዚያ በሉልኝ ስላላልኳቸው ‹‹ለምንድነው ያንን የተማረሩበትን ያልነገሩኝ›› ብየ ተገርሜ አውቃለሁ። ምናልባት መንግሥትን የወቀሰ እንዲህ ይደረጋል ሲባል ስለሚሰሙ ፈርተው ይሆናል።

ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ግን በግልጽ የመናገር ልማዳችን ደካማ ነው። ይህን ሁሉ ያስታወሰኝ ከትናንት በስቲያ (ሰኞ) በመንግሥት ሰራተኞች ማመላለሻ አውቶብስ (ፐብሊክ ሰርቪስ) ውስጥ የሰማሁት ሀሜት ነው።

ሁለት ሰዎች አንዲትን የመስሪያ ቤታቸው የበላይ አመራር ያብጠለጥላሉ።በወቀሳቸው ውስጥ፤ ተቋሙን የግል ካምፓኒዋ እንዳደረገችው፣ በማን አለብኝነት ‹‹አባርርሃለሁ!›› እያለች እንደምትናገር፣ በአጠቃላይ ፈላጭ ቆራጭነቷን ነው የሚያወሩት።

ሀሜቱን ስሰማ በውስጤ የመጡ ጥያቄዎች ‹‹እነዚህ ሰዎች ይህን ችግሯን ፊት ለፊት ነግረዋት ያውቁ ይሆን?›› የሚል ነው።በፍፁም አይመስለኝም።ምክንያቱም እንዲህ አይነት ሀሜት ከቅርቤ ጀምሮ ስለማውቅ ነው።ፊት ለፊት የመናገር ልማድ የለንም።በየካፌውና በመስኮቱ የምንንሾካሾከውን በባለቤቱ ፊት ግን በተቃራኒው አድንቀን ነው የምንናገር። ይሄ የአድርባይነት ባህሪ ነው። እወደድባይነት ነው። በተለይም የበላይ አመራር ከሆነ የተለየ ተወዳጅነትንና ተደናቂነትን ለማግኘት ነው፤ በዚህ ደግሞ የሆነ ጥቅም ያስገኝልኛል ተብሎ ይታሰባል ማለት ነው፡፡

በእርግጥ ይሄ የሀሜተኞች ችግር ብቻ አይደለም። የባለቤቶችም ችግር ነው፤ በግልጽ ሲነገረው ራሱን የሚያዞረው ብዙ ነው።እውነታው በግልጽ ከሚነገረው ይልቅ የድለላ አድናቆት ያሞቀዋል። በሽንግላ ሙገሳ የሚኮራ ብዙ ነው።

አንዳንድ አመራር ወይም ሰራተኛ እውነተኛ ነገር ሲነገረው የምርም ያኮርፍ ይሆናል፤ ሥልጣን ያለው ከሆነ ደግሞ ምናልባትም ተናጋሪውን ለመጉዳት ያስብ ይሆናል። እንዲህ አይነት ነገር ሀሜትን ማበረታታት ነው። ጠቃሚው ግን ፊት ለፊት የሚነገር አስተያየት ነው። ምክንያቱም ያ ባለሥልጣን ሲወደስና ሲሞካሽ ኖሮ ከሥልጣን የወረደ ዕለት የሚያበሻቅጠው ይበዛል፤ በዚያው ሞራሉ ይነካል።ትችትንና ወቀሳን የተላመደ ቢሆን ግን ምንም አይመስለውም።ስለዚህ ሀሜተኞችን በወቀስነው ልክ ግልጽ አስተያየትን የሚጠሉትንም ልንወቅስ ይገባል።

ሀሜት ልማዳችን ነው። የተማረው ክፍል ሊያስቀረውና ሊያሻሽለው ሲገባ እንዳለ እያስቀጠለው ነው። በቡና ላይ ወሬ ሀሜት የተለመደ ነው። በዚህ ልማድ በታዳሚዎች ውስጥ የሌለ ሰው ነው የሚታማ፤ አብሮ ያለ ሰው አይታማም። እንዲያውም በዚሁ ምክንያት ‹‹ጓደኛህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ›› የሚባል አባባል ሁሉ አለን።‹‹ጆሮ ለባለቤቱ ባዕዳ ነው›› የሚባል ሌላ አባባልም አለ፤ የዚህ አባባል ትርጉም ደግሞ ሀሜት ስንታማ ጆሯችን የማይሰማ መሆኑን ለመግለጽ ነው። የሁለቱም አባባሎች መልዕክት ሀሜት ሰውየው በሌለበት የሚደረግ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

እንግዲህ ይህ በድሮው ዘመን የነበረ፣ዘመናዊ ትምህርት ያልነበረበትና በልማድ ብቻ የሚኖርበት ነው እንበል! አሁን በዚህ ዘመን ግን ስለግልጸኝነት፣ ስለሒስ እና ግለ ሂስ በትምህርትም በመድረክም እየተማርን እዚህ ደርሰን አሁንም ሀሜተኞች ነን።‹ ‹የተማረ›› ተብሎ ሀሜተኛ መሆን ደግሞ የበለጠ ነውር ነው።

በስነ ጽሑፍ ሙያ ውስጥ ‹‹ሂስ›› የሚባል ነገር አለ።በፖለቲካ ዘርፍ ደግሞ ግምገማ የሚባል ነገር አለ። በስነ ጽሑፍ ዘርፍ ሂስ ማለት ባለሙያም ሆነ ሌላ ታዳሚ የሚሰጠው አስተያየት ነው። የሰውየውን ስህተቶች መንገር ነው። ዳግም ሌላ ስህተት እንዳይሰራ ማስተማሪያ ማለት ነው፡፡

በፖለቲካም ግምገማ የሚባለው እንደዚሁ ነው። የሰውየውን ደካማ ጎኖች በግልጽ ከፊት ለፊቱ መናገር ማለት ነው። የሚነገረው እነዚያን ስህተቶች እንዳይደግም ነው፡፡

የታደሉት ሂስ ሲነገራቸው ደስ ይላቸዋል።በግልጽ የሚናገራቸውን ሰው ይወዳሉ። ያ በግልጽ የተናገረ ሰው ውስጥ ለውስጥ የሚያንሾካሹከው አይኖረውም። በውስጡ የሚያስበው አይኖረውም፡፡

ሀሜተኛ ግን ግልጽ አይደለምና ሌላ ተጨማሪ ሴራ ሁሉ ሊያስብ ይችላል። ለዚያ ለሚያማው ሰው ወጥመድ ሊያጠምድ ሁሉ ይችላል።እንዳለመታደል ሆኖ ግን በግልጽ ከሚነግረን ሰው ይልቅ እየሸነገለ የሚያሞካሸንን እንወዳለን። ይህ ሰው አይጠቅመንም፤ ወደ ወጥመድ ነው የሚወስደን፡፡

በተለይ ትንሽ ታዋቂነት ወይም ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ላይ ደግሞ ሀሜት ይበዛል። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ አድርባዮች የምንሆን። ታዋቂ ሰው የሆነ ነገር ቢጽፍ አብዛኛው ሰው የሚሰጠው አስተያየት ‹‹የኛ ጀግና›› የሚል ነው። ከልባቸው ለሚሉት ችግር የለውም፤ ዳሩ ግን እነዚሁ ሰዎች ሰውየን የሚወቅስ ሰው ሲያገኙ አብረው ነው የሚያብጠለጥሉት።

አንዳንዶች ላይ ደግሞ የምታዘበው አንድን ታዋቂ ሰው ወይም ባለሥልጣን አላገኘውም በሚል ይወቅ ሱታል፣ ይሰድቡታል። ሰውየውን የማግኘት ዕድል ሲያጋጥማቸው ግን ከማንም በላይ አድናቂው መሆናቸውን የሚናገሩ እነርሱ ናቸው።ሥራዎቹ ሁሉ እንከን የማይወጣላቸው አድርገው ነው የሚነግሩት።ይሄ አድርባይነት ነው። ይሄ ልማድ ቢያንስ በተማረው ክፍል ዘንድ ሊቀረፍ ይገባል፡፡

ታዋቂ ሰዎችና ባለሥልጣናትም በሽንገላ ከሚያቆለጳጵሳችሁ ይልቅ እውነተኛ ስሜቱን በግልጽ የሚነግራችሁን አመስግኑ!

# ዓለም አቀፍ




## ሜታ ኩባንያ የዜና ይዘቶችን ከፌስቡክ ገጹ አግዳለሁ አለ

ኢንስታግራም፣ ፌስቡክን እና ዋትስአፕን የሚያስተዳድረው ሜታ ኩባንያ ከፌስቡክ ገጾች ላይ የዜና ይዘቶችን ጨርሶ ሊያስወግድ እንደሚችል ዛተ። ይህ ዛቻ የመጣው የዜና አገልግሎቶችን ሜታ ከሚያጋብሰው ትርፍ ተጠቃሚ ለማድረግ በአሜሪካ አንድ አዲስ ረቂቅ ሕግ መርቀቁን ተከትሎ ነው።

የዜናና መረጃ ነክ ይዘት ያላቸው የጋዜጠኝነት ሥራዎች በስፋት በገጹ እያጋራ ነገር ግን የማስታወቂያ ትርፉን ለብቻው ይወስደዋል በሚል ሲከሰስ የቆየው ሜታ በበኩሉ ‘እኔ ውለታ በዋልኩላችሁ…’ እያለ ነው።ድርጅቱ እንደሚለው ከዜናና መረጃ ነክ ገጾች የሚገኘው የማስታወቂያ ትርፍ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። የሚዲያ መረጃዎችን ወደ ፌስቡክ እድምተኛ የምወስደውም በግድ እንዲነበቡ ለማድረግ ነው ይላል።

ኩባንያው እንደሚለው ተጠቃሚዎቹ ዜናና መረጃዎችን ከፌስቡክ ለማንበብ ፍላጎታቸው እምብዛምም ነው። የሚዲያ ተቋማት በበኩላቸው እኛ ለፍተን ደክመን ባሰናዳነው ዜናና መረጃ ፌስቡክ የማስታወቂያ ትርፍ ያጋብሳል፣ ለኛ ግን ጠብ የሚል ነገር የለም ሲሉ ያማርራሉ። ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ተቃውሞ ከሚዲያዎች ለፌስቡክ ቀርቦ ያውቃል፤ ይህም የሆነው በአውስትራሊያ አገር ነው።

ፌስቡክ በውስትራሊያ ቀርቦበት ለነበረ ተመሳሳይ ቅሬታ ‘እንዲያውም በገጼ ዜናን አላስተናገድም’ ሲል ዝቶ ነበር።የኋላ ኋላ ግን ሐሳቡን አጢኖ፣ ከመንግሥት ጋር ተደራድሮ ለሚዲያዎች ትርፍን የማጋራት ስምምነት ለማድረግ ተገዷል።በተመሳሳይ አሁን በአሜሪካ የቀረበው ረቂቅ ድርጅቱን ከሚያገኘው ትርፍ ከፊሉን ለመገናኛ ብዙኃን እንዲያካፍል ሊያስገድደው ይችላል።

በአሜሪካ የመገናኛ ብዙኃን ከትንሽ እስከ ግዙፎቹ ጭምር ‘ሜታ በኛ ላብ ሚሊዮን ዶላር ይሰበስባል’ ሲሉ የሚከሱት በተደጋጋሚ ነው። ፌስቡክ ግን ሁልጊዜም የሚለው ሚዲያዎቹ እንደሚያስቡት ይዘታቸው በገጹ ላይ በደንበኞች ተፈላጊም ተነባቢም አይደለም።

አሁን የቀረበውና በምህጻሩ ጄሲፒኤ የሚባለው ረቂቅ ሕግ በሚኔሶታ እንደራሴ በሆኑት አሚ ክሎቡቻር ፊታውራሪነት የቀረበ ነው።ረቂቅ ሕጉ በዲሞክራቶችና በሪፐብሊካኖች ዘንድም ከፍ ያለ ድጋፍ አለው።ረቂቅ ሕጉ ከጸደቀ ለሚዲያ ኩባንያዎች ትልቅ ድል ነው ተብሏል።ምክንያቱም መገናኛ ብዙኃኑ ለሚያመርቱት መርሃግብር ፌስቡክ ከትርፍ ሊያጋራቸው ይገደዳል።

ይህም በገቢ ድርቅ ለተመቱ አነስተኛና መለስተኛ የአካባቢ መገናኛ ብዙኃን እንደ አዲስ እንዲያንሰራሩ ሊያደርጋቸው ይችላል። በርካታ አነስተኛና መለስተኛ ሚዲያዎች በአሜሪካ በወረርሽኙ ጊዜ የትርፍ ማሽቆልቆል ገጥሟቸው ለመዘጋት ተቃርበው ነበር።በአንጻሩ የነርሱኑ ይዘት የሚያጋራው ፌስቡክ በትርፍ ተንበሽብሾ መሰንበቱ አይዘነጋም።

አሜሪካ ያለመጠን ገዝፈው የገበያ ውድድር እንዲቀጭጭ አድርገዋል ከምትላቸው ኩባንያዎች አንዱ ሜታ ነው።ሜታ ኩባንያ መቀመጫውን ካሊፎርኒያ ያደረገና ግዙፎቹን የማኅበራዊ ሚዲያዎች ማለትም ፌስቡክን ዋትስአፕንና ኢኒስታግራምን በባለቤትነት የሚያስተዳድር ድርጅት ነው።

የአሜሪካ የኢኮኖሚክ ሊበሪቲስ ፕሮጀክት ዳይሬክተር የሆኑት ማት ስቶለር ‘ሜታ ቀጫጭን ሚዲያዎችን ሰልቅጦ እየበላቸው ነው’ ሲሉ የውድድር ሜዳው እየጠፋ ስለመሆኑ አስተያየት መስጠታቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው።



## አሜሪካና አጋሮቿ ሱዳን ቀውሷን ለመፍታት አዲስ ስምምነት መፈረሟን በበጎ የምናየው ነው አሉ

አሜሪካ እና አጋሮቿ ባለፈው ዓመት በመፈንቅለ መንግስት የተቀሰቀሰውን የፖለቲካ ቀውስ ለማስቆም በሱዳን ወታደራዊ እና ሲቪል መሪዎች መካከል ስምምነት መፈረሙን በበጎ እንቀበላለን አሉ።

የሱዳን ኃይሎች የሽግግር ሲቪል መንግስት ለማቋቋም ያለመ የመጀመሪያ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡በዚህም አሜሪካ፣ ኖርዌይ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ አረብ ኤምሬትስ እና ብሪታንያ “የመጀመሪያውን የፖለቲካ ማዕቀፍ ስምምነት በደስታ ተቀብለዋል” ሲል የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር በጋራ ባወጣው መግለጫ ገልጿል።

ሱዳን በፈረንጆቹ በጥቅምት 2021 የጦሩ አዛዡ አብዱልፈታህ አል ቡርሃን ስልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላ በተቃውሞ እና በምጣኔ-ሀብት ቀውስ ስትናጥ ቆይታለች። ይህም አንጋፋው መሪ ኦማር አል በሽርን ከስልጣን ከተወገዱ በኋላ የተጀመረውን የሲቪል አገዛዝ ሽግግር ማደናቀፉን ጋርዲያን አጃንስ ፍራንስ ፕረስን ጠቅሶ ዘግቧል።

ሰኞ እለት ቡርሃን፣ የፓራሚታሪ አዛዥ መሀመድ ሃምዳን ዳጋሎ እና በርካታ የሲቪል ቡድኖች፣ በመፈንቅለ መንግስቱ ከስልጣን የተባረረው ዋና የሲቪል ቡድን በተለይም የነፃነት እና የለውጥ ኃይሎች የሽግግር ሲቪል መንግስት ለማቋቋም ያለመ የመጀመሪያ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

አጋሮቹ በመግለጫቸው ስምምነቱን “በሲቪል የሚመራ መንግስት ለመመስረት እና ህገመንግስታዊ ዝግጅቶችን ለመወሰን ሱዳንን ወደ ምርጫ ለሚወስድ የሽግግር ጊዜ አስፈላጊ የመጀመሪያ እርምጃ ነው” ሲሉ አወድሰዋል።ስምምነቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባለስልጣናት፣የምዕራባውያን ዲፕሎማቶች እንዲሁም የሳውዲ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ባለስልጣናት በተገኙበት መደረጉን አጃንስ ፍራንስ ፕረስ ዘግቧል።

ይሁን እንጂ አንዳንድ የሲቪል ቡድኖች ከጦሩ ጋር የተደረገውን ድርድር ውድቅ በማድረግ ስምምነቱን እንደ ክህደት በመቁጠር ቁጣ ተነስቷል ነው የተባለው።የጋራ መግለጫው “ሁሉም የሱዳን ተዋናዮች በዚህ ድርድር ላይ በአስቸኳይ እና በቅን ልቦና እንዲሳተፉ እናሳስባለን” ብለዋል።

ሁሉም ወገኖች የሱዳንን ብሔራዊ ጥቅም “ከጠባብ የፖለቲካ ዓላማዎች” በላይ እንዲያስቀድሙም ሀገራቱ ጥሪ ማቅረባቸውን አል ዐይን ዘግቧል።

# ባለውለታዎቻችን

## ሲየተናል ጄኔራል ነጋ ኃይለሥላሴ (አባ ይባስ)
## (1910 – 2000 ዓ.ም)

ግርማ መንግሥቴ

መቸም ጀግናና ጀግንነት ሲነሱ የሚያስነሱት ርእስና ርእሰ ጉዳይ የዋዛ አይደለም። የቱን ጥዬ፣ የቱን ይዤ ... እስኪባል ድረስ ነው የሚያስጨንቁት። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ጀግንነትም ሆነ ጀግናነት (ጀግና መሆን) በቀላሉ ፊጥ የሚባልበት ባለመሆኑና እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ የሚዘልቅ ተግባር መፈፀምን ስለሚጠይቅ ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው፣ የሚወደሰውና ከባለ ውለታነት ተርታ የሚያሰልፈው የጀግንነት ውሎውና ተግባሩ ለአገርና ለሕዝብ እስከሆነ ድረስ ነውና የዛሬውን ባለውለታችንን ከዚሁ አኳያ የምናነሳቸው ይሆናል።

ሊየተናል፡ጄኔራል፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ ይባላሉ፤ በሌላኛው (በጀግንነት) ስማቸው ደግሞ አባ፡ ይባስ።

ሊየተናል፡ ጄኔራል፡ ነጋ፡ ተጽፎም ሆነ ተነግሮ የማያልቅ ታሪክ ባለቤት ናቸው። ያልወጡት ዳገት፤ ያልወረዱት ቁልቁለት የለም። ይሁን እንጂ በዚህ አንድ ገፅ ጋዜጣ ሁሉንም ቀርቶ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህሏን ታሪካቸውን እንኳን ልናወራላቸው አንችልም። በመሆኑም፣ ያለን አማራጭ አንባቢ ስለ ባለታሪኩ ሰነዶችን በማገላበጥ ገድላቸውን መገንዘብ ያለበት መሆኑን መጠቆም ነው።

### ትውልድና፡ እድገት

ሊየተናል. ጄኔራል፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ ካባታቸው፡ ከልጅ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ሞላ ከናታቸው፡ ከወይዘሮ፡ ደስታ፡ አባዬ የይፋት፡ አውራጃና፡ የመንዝ፡ አውራጃ፡ አዋሳኝ፡ በሆነው ጎራት፡ አካባቢ ሚያዝያ፡ 30፡ ቀን፡ 1910 ዓ.ም.፡ ተወለዱ።

ልጅ፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ አብዛኛውን፡ የሕፃንነትና፡ የልጅነት፡ ዘመናቸውን፡ ይፋት፡ (መንግሥት፣ ጎራት፣ ዐማች፡ ዐምባ፣ ቊጫጭ፡ ዐምባ፣ ቆቦ)፡ አሳለፉ።

### ትምህርት

በጥንታዊው፡ የኢትዮጵያ፡ ልማድ፣ አራት፡ ዓመት፡ ካራት፡ ቀን፡ ሲሞላቸው፣ ደብተራ፡ ገብረ፡ ክርስቶስ፡ ዘንድ፣ ቀጥሎም፡ አጎታቸው፡ አለቃ፡ ገብረ፡ ክርስቶስ፡ ዘንድ፣ እንዲሁም፡ መምህር፡ ተቀጥሮላቸው፣ ከፊደል፡ መቍጠር፡ እስከ፡ ዳዊት፡ መድገም፡ ያለውን፡ ባህላዊ፡ የቀለም፡ ትምህርት፡ ባስደናቂ፡ ፍጥነት፡ አጠናቀቁ። በጊዜው፡ ለጨዋ፡ ልጅ፡ ኹሉ፡ ይሰጥ፡ የነበረውንም፡ የሥርዐት፣ የጠመንጃ፡ ተኩስ፣ የውሃ፡ ዋና፣ የፈረስ፡ ግልቢያና፡ የመሳሰለውን፡ ትምህርት፡ አገኙ።

በ1917 ዓ.ም፣ ልጅ፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ ከወንድሞቻቸው፡ ከልጅ፡ አሰፋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴና፡ ከልጅ፡ ለማ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ጋራ፣ እናታቸውን፡ ወይዘሮ፡ ደስታ፡ አባዬን፡ ተከትለው፣ በሕይወት የሌሉትን ያባታቸው (ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ሞላ)ን የወግ፡ ዕቃ፡ ለመንግሥት፡ ለማግባት፣ አዲስ፡ አበባ፣ ራስ፡ ተፈሪ፡ መኰንን፡ ዘንድ፡ ቀረቡ። ልጅ፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ ራስ፡ ተፈሪ፡ መኰንን፡ በዚህ፡ ዕለት፡ ለመጀመሪያ፡ ጊዜ፡ አዩአቸው፤ ስላባታቸውም፡ ማረፍ፡ የገለጹላቸው፡ የሐዘን፡ ስሜትና፡ የማጽናናት፡ ቃል፡ በልጅነት፡ አእምሯቸው፡ ለመቼውም፡ ተቀርጾ፡ ኖረ።

ራስ፡ ተፈሪ፡ መኰንን፣ የልጅ፡ ኀይለ፡ ሥላሴን፡ ልጆች፡ ማስተማር፡ የኛ፡ ተግባር፡ ነው፡ ቢሉም፣ የልጆቹ፡ ዕድሜ፡ ማነስ፡ ከቤተሰብ፡ ርቆ፡ ለመኖር፡ ስላልፈቀደ፣ ከሁለት፡ ዓመት፡ በኋላ፡ ከይፋት፡ ይዘዋቸው፡ እንዲመጡ፡ ወይዘሮ፡ ደስታን፡ ዐደራ፡ አሉ።

ይፋት፡ ተመልሰው፣ ሁለት፡ ዓመት፡ እንደ፡ ሞላም፣ በ1919፡ ዓ.ም.፣ የልጅ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ማኅበርተኞች፣ እነደጃዝማች፡ አበበ፡ አውራሪስ፣ ልጅ፡ (ኋላ፣ ቢትወደድ)፡ መኰንን፡ እንዳልካቸው፣ ልጅ፡ መኵሪያ፡ ይገባሻል፣ ባላምባራስ፡ (ኋላ፣ ራስ)፡ አበበ፡ አረጋይ፣ ነጋድራስ፡ አበበ፡ ድረስ፣ ልጅ፡ ኀይለ፡ ማርያም፡ ገዝሙ፡ አንድጋ፡ ኾነው፣ "ዐልጋ፡ ወራሽ፡ ራስ፡ ተፈሪ፡ መኰንን፡ ባዘዙት፡ መሠረት፣ ልጆችዎ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እንዲገቡ፡ ወዳ አዲስ፡ አበባ፡ ይላኳቸው"፡ የሚል፡ ማስታወሻ፡ ደብዳቤ፡ ለወይዘሮ፡ ደስታ፡ ጻፉላቸው። ከጥቂት፡ ወራት፡ በኋላ፣ ሦስቱ፡ ወንድማማቾች፡ (ልጅ፡ ነጋ፣ ልጅ፡ አሰፋ፣ ልጅ፡ ለማ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ) አዲስ፡ አበባ፡ እንደ፡ መጡ፥ ካባታቸው፡ ማደሪያ፡ በደጃዝማች፡ ይገዙ፡ በሀብቴ፡ በኩል፡ እየተሰበሰበ፥ በወር፡ 30፡ ብር፡ እንዲከፈልላቸው፡ ሆኖ፣ እተፈሪ፡ መኰንን፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ባአዳሪነት፡ ተመዝግበው፣ ዘመናዊ፡ ትምህርታቸውን፡ በፈረንሳይኛ፡ ቋንቋ፡ ለሰባት፡ ዓመት፡ ተከታተሉ።

ሦስቱም፡ ወንድማማቾች፡ እጅግ፡ ብሩህ፡ አእምሮ፡ ነበራቸውና፣ በመጀመሪያው፡ ዓመት፣ ያንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርታቸውን፡ ባስደናቂ፡ ውጤት፡ አጠናቀው፣ ባምስተኛው፡ ዓመት፡ ልጅ፡ አሰፋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ በሰባተኛው፡ዓመት፡ደግሞ፣ልጅ፡ለማና፡ልጅ፡ነጋ፡ኀይለ፡ ሥላሴ፡ የሁለተኛ፡ ደረጃ፡ መፈጸሚያና፡ የዩኒቨርሲቲ፡ መግቢያ፡ "ባካሎሬያ፡ ሲያንቲፊክ"፡ ፈተናቸውን፣ በ1924ና፡ በ1926 ዓ.ም. መጨረሻ፣ በ"ፍጹም፡ ጥሩ"፡ ("ኤክሰለንት")ና፡ በ"እጅግ፡ ጥሩ"፡ ("ትሬ፡ ቢየን")፡ ማዕርግ፡ አልፈዋል። ይኸውም፡ የባካሎሬያ፡ ፈተና፡ በኢትዮጵያ፡ ለመጀመሪያ፡ ጊዜ፡ መካሄዱ፡ ነበር። በዚሁ፡ ብልህነታቸው፣ እንዲሁም፡ በትሕትናቸውና፣ በግብረ፡ ገብነታቸው፣ አስተማሪዎቻቸውም፡ ሆኑ፡ የተማሪ፡ ቤት፡ ጓደኞቻቸው፡ በተለይ፡ ወደዷቸው፣ አከበሯቸው፣ ተመኩባቸውም፤ "የተፈሪ፡ መኰንን፡ ኮከቦች"፡ የሚል፡ ማቈላመጫ፡ ስምም፡ አወጡላቸው። ልጅ፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ በሒሳብ፣ በሳይንስ፣ በሥዕልና፡ በሙዚቃ፡ የተለየ፡ ስጦታ፡ ነበራቸው። ባአዲስ፡ አበባ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ መካከል፡ በተደረጉ፡ የሙዚቃም፡ የሥዕልም፡ ውድድሮች፣ አንደኛ፡ እየወጡ፣ ከንግሥተ፡ ነገሥታት፡ ዘውዲቱ፡ እጅ፡ ሽልማትን፡ ተቀብለዋል።

ባካሎሬያቸውን፡ አግኝተው፣ ለከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ወደ፡ አውሮፓ፡ እንዲሄዱ፡ መወሰኑ፡ ሲነገራቸው፣ "ፋሺስት፡ ኢጣሊያ፡ ኢትዮጵያን፡ ለመውረር፡ እየተሰናዳች፣ አገሬን፡ ጥዬ፡ አልሄድም"፡ ብለው፣ ወደ ጦር፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ለመግባት፡ ያላቸውን፡ ፍላጎት፡ ገለጹ። ጦር፡ ትምህርት፡ ለመግባት፡ የዕድሜያቸው፡ ማነስ፡ እንደማይፈቅድላቸው፡ ቢነገራቸውም፣ ለግርማዊነታቸው፡ አመልክተው፣ ከስድስት፡ ወር፡ ጥበቃ፡ በኃላ፣ በልዩ፡ ፈቃድ፣ በጥር፡ ወር፡ 1927፡ ዓ.ም እገነት፡ ሆሎታ፡ ቀዳማዊ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ጦር፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ገብተው፣ ከትምህርቱ፡ ተሳተፉ።

በስዊድን፡ ወታደራዊ፡ ተልእኮ፡ በፈረንሳዊ፡ ቋንቋ፡ የተሰጠው፡ የጦር፡ ትምህርት፡ ሙሉ፡ በሙሉ፡ የፈረንሳይ፡ ጦር፡ አካዳሚ፡ ትምህርት፡ መርሐ፡ ግብር፡ ነው። ወቅቱ፡ አስቸኳይ፡ ስለ፡ ሆነ፣ የሦስቱን፡ ዓመት፡ የጦር፡ ትምህርት፡ መርሐ፡ ግብር፣ ዓመት፡ ተመንፈቅ፡ ባልሞላ፡ ጊዜ፣ አንደኛ፡ በመውጣት፡ አጠናቀው፣ በመድፈኛ፡ ደንብ፡ ውስጥ፣

- ኅዳር፡ 14፡ ቀን፡ 1928፡ ዓ.ም.፣ የመቶ፡ አለቃ፤
- ታኅሣሥ፡ 14፡ ቀን፡ 1928፡ ዓ.ም፣ የሻምበል፤
- ጥር፡ 21፡ ቀን፡ 1928፡ ዓ.ም.፣ የሻለቃ፡ (የ5፡ ሻምበል፡ አዛዥ)፤
- በመጨረሻም፣ የካቲት፡ 21፡ ቀን፡ 1928፡ ዓ.ም.፣ በሊየተና፡ ኮሎኔልነት፡ ማዕርግ፣ አዲስ፡ ለተቋቋመው፡ ብሪጌድ፡ ዋና፡ ኤታ፡ ማዦር፡ ሹም፡ ሆነው፡ በንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ተሠየሙ።

### አገልግሎት

ወዲያው፣ ሚያዝያ፡ 13፡ ቀን፡ 1928፡ ዓ.ም.፣ አዲሱን፡ ጦር፡ በኤታ፡ ማዦር፡ ሹምነት፡ በጣርማ፡ በር፡ ግንባር፡ አዘመቱ። የኢትዮጵያ፡ ጦር፡ ከተፈታ፡ በኋላ፣ ጥቂት፡ የገነት፡ መኰንኖችንና፡ ሰራዊቱን፡ ይዘው፣ ሚያዝያ፡ 24፡ ቀን፡ 1928፡ ዓ.ም.፡ አርበኝነት፡ ወጡ። እስካ 1930፡ ዓ.ም.፡ ፍጻሜ፡ ድረስ፣ ለሁለት፡ ዓመት፡ ተኩል፣

- ሸዋ፡ (አዲስ፡ አበባ፡ ዙሪያ፣ ሙሎ፣ ሰላሌ፣ ተጒለት፣ መርሐቤቴ፣ ግንደበረት፣ ጊዳ፣ ሜጫ፣ ሜታ፣ ...)፤
- ወለጋ፡ (አሞሩ፣ ኤበንቱ፣ ጨልያ፣ ሆሮ፣ ጉድሩ፣ ...)፣
- ጎጃም፡ (አለፋ፡ ጣቁሳ፣ ቡሬ፣ አሰዋ፡ ጉደራ፣ አገው፡ ምድር፣ ማቻከል፣ ...)

ከደጃዝማች፡ ዘውዴ፡ አስፋው፡ ዳርጌ፣ ከራስ፡ አበበ፡ አረጋይና፣ ከታላላቅ፣ ያርበኝነት መሪዎች፡ ጋራ፡ በጦር፡ መሪነት፣ እዚህ፡ ሊዘረዘሩ፡ በማይችሉ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ውጊያዎች፡ በታላቅ፡ ጀግንነት፡ ተዋግተውና፡ አዋግተው፣ ባርበኞች፡ ዘንድ፡ የላቀ፡ ዝናን፣ የተለየ፡ አድናቆትን፡ አትርፈዋል።

በወቅቱ፣ ሱዳንን፡ በቅኝ፡ ግዛትነት፡ ይገዛ፡ የነበረው፡ የብሪታንያ፡ መንግሥት፣ ኢትዮጵያን፡ ለኢጣሊያ፡ አፅድቆ፡ ኖሮ፣ መስከረም፡ 19፡ ቀን፡ 1931፡ ዓ.ም.፣ ሊ.፡ ኮሎኔል፡ ነጋ፡ ኀይል፡ ሥላሴ፡ ከተከተሏቸው፡ ዐርበኞች፡ ጋራ፣ የሱዳንን፡ ጠረፍ፡ እንዳለፉ፣ ጠረፉን፡ የሚጠብቀው፡ የብሪታንያ፡ ጦር፡ ይይዛቸዋል። ጥቂት፡ ወራት፡ በጦር፡ እስረኝነት፡ ገዳሬፍና፡ ካርቱም፡ እንደ፡ ቈዩ፣ ኢጣልያ፡ በታላቋ፡ ብሪታንያ፡ ላይ፡ ጦርነት፡ በማወጇ፣ የታሰሩት፡ ዐርበኞች፡ ተፈቱ።

ሊ.፡ ኮሎኔል፡ ነጋ፡ ኀይል፡ ሥላሴም፣ ከሰራዊቱ የተላኩትን፡ መልክት፡ (ያርበኝነት፡ ተጋድሎው፡ የደረሰበትን፡ ደረጃ፣ ያስገኛቸውንም፡ ውጤቶች፡ አስታውቆና፣ ከንጉሠ ነገሥቱ፡ ጋራ፡ ግንኙነትን፡ መሥርቶ፣ የጦር፡ መሣሪያና፡ የሥንቅ፡ ርዳታ፡ በቶሎ፡ ላርበኛው፡ እንዲደርስ እንዲያደርጉ የሚጠይቀውን ደብዳቤ) በብሪታንያ፡ ባለሥልጣኖች፡ በኩል፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ አስተላልፈው፣ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ለመመለስ፣ ዐብረዋቸው፡ የሚዘምቱ፡ ሁለት ሺህ፡ የሚኾኑ፡ ስደተኞችን፡ ላርበኝነት፡ አሰባስበው፡ በሚያደራጁበት፡ ጊዜ፣ የታላቋ፡ ብሪታንያ፡ መንግሥት፡ በጎ፡ ፈቃድና፡



ወታደራዊ፡ ድጋፍ፡ ደረሰላቸው።

ሰኔ፡ 27፡ ቀን፡ 1932፡ ዓ.ም.፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ከብሪታንያ፡ ወደ፡ ካርቱም፡ እንደ፡ ተመለሱ፣ ሊ.፡ ኮሎኔል፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴን፡ አስጠርተው፣ ሶባ፡ እተባለው፡ የሱዳን፡ ቀበሌ፣ አዲስ፡ የሚቋቋመውን፡ ቅዱስ፡ ጊዮርጊስ፡ የጦር፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ከብሪታንያ፡ ጦር፡ መኰንኖች፡ ጋራ፡ በጣምራ፡ እንዲመሩ፡ አዘዟቸው።

በወቅቱ፡ የመርድ፡ አዝማች፡ አስፋ፡ ወሰን፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ወታደራዊ፡ ማዕረግ፡ የሻለቃ፡ ስለ፡ ነበር፣ ከርሳቸው፡ ማዕርግ፡ በልጦ፡ እንዳይገኝ፣ ሊ.፡ ኮሎኔል፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ ማዕርጋቸው፡ አንድ፡ ደረጃ፡ ዝቅ፡ ብሎ፣ በሻለቅነት፡ ማዕርግ፡ ሥራቸውን፡ እንዲቀጥሉ፡ ከንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ታዘዙ። ኮሎኔሉም፣ ጃንሆይ፤ ጉዳዬ፡ ከሥራው፡ እንጂ፡ ከማዕረጉ፡ አይደለም፤ ብለው፡ ተቀበሉ።

የካቲት፡ 1933፡ ዓ.ም.፡ ኢትዮጵያ፡ ገብተው፣ ከ3፡ ወር፡ ዘመቻ፡ በኃላ፣ ደብረ፡ ማርቆስ፡ ከኢጣሊያ፡ ጦር፡ እጅ፡ ነጻ፡ ወጣች። ሻለቃ፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ በጦሩ፡ በኩል፡ ለሚኖረው፡ ጉዳይ፡ ኹሉ፡ ኀላፊ፡ ኾነው፣ የንጉሠ፡ ነገሥቱንም፡ ወታደራዊ፡ መመሪያ፡ ይዘው፣ ከምክትሎቻቸው፡ ከሻለቃ፡ ዐቢይ፡ አበበና፡ ከሻለቃ፡ ሙሉጌታ፡ ቡሊ፡ ጋራ፣ የንጉሠ፡ ነገሥቱን፡ ባለሙሉ፡ ሥልጣን፡ እንደራሴ፡ ቢትወደድ፡ መኰንን፡ እንዳልካቸውን፡ ዐጅበው፣ ሚያዝያ፡ 5፡ ቀን፡ 1933፡ ዓ.ም.፡ በማለዳ፡ ከደብረ፡ ማርቆስ፡ ባየርዠበብ፡ (አይሮፕላን)፡ ተጒዘው፣ የኢትዮጵያ፡ መናገሻ፡ ከተማ፣ አዲስ፡ አበባ፣ ጧቱኑ፡ ገቡ። ሻለቃ፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴን፡ ካርበኝነት፡ ዘመን፡ አንሥቶ፡ ያውቋቸውና፡ ያደንቋቸው፡ የነበሩት፣ ዝነኛዋ፡ ባለቅኔ፡ ንጋቷ፡ ከልካይ፣ የምሥራቹን፡ እንደ፡ ሰሙ፣

ጠቅል፡ ባንዲራውን፡ ጠረፍ፡ ቢዘረጋ፣
አዲስ፡ አበባ፡ ላይ፡ አስቀድሞ፡ ነጋ።
ሲሉ፡ ገጠሙላቸው።

አዲስ፡ አበባ፡ እንደ፡ ገቡም፣ ጽሕፈት፡ ቤታቸውን፡ በጃንሆይ፡ ዐፄ፡ ምኒልክ፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ ግቢ፡ ውስጥ፡ አድርገው፣ ያርበኛውን፡ ጦር፡ በከተማዋ፡ ዙሪያ፡ አዋቅሮ፡ በማሰምራትና፣ ከብሪታንያ፡ ጦር፡ ኀላፊዎች፡ ጋራ፡ ዐብሮ፡ በመሥራት፣ የከተማውን፡ ጠቅላላ፡ ጸጥታ፡ አረጋግጠው፣ ወታደራዊ፡ አስተዳደሩን፡ አደራጅተው፣ ንጉሠ፡ ነገሥታቸውን፡ በመናገሻ፡ ከተማዋ፡ ለመቀበል፡ አስፈላጊውን፡ ዝግጅትና፡ መስተንግዶ፡ አከናወኑ። በዚህ፡ ሥራቸው፣ ከብሪታንያ፡ ጦር፡ አመራር፡ ጋራ፣ አልፎ፡ አልፎ፣ አለመግባባትና፡ ግጭት፡ ቢፈጠርም፡ ቅሉ፣ ሻለቃ፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ አንዳችም፡ ጊዜ፡ ቢኾን፡ የኢትዮጵያን፡ እግዚእና (ሉአላዊነት)፡ ሳያስደፍሩ፣ ክብሯንም፡ ሳያስነኩ፣ ተልእኳቸውን፡ ጠንቅቀው፡ ፈጽመዋል።

ሰኔ፡ 7፡ ቀን፡ 1954፡ ዓ.ም፣ የሊዩተና፡ ዤኔራልነት፡ (ታኅሣሥ፡ 11፡ ቀን፡ 1951፡ ዓ.ም.፣ የሜጀር፡ ዤኔራልነት፡ ማዕረግ) ተሰጥቷቸው ወደ ጎንደር፡ ሄዱ። ጎንደር እንደ፡ ገቡም፤

"አህያ፡ መጣች፡ ተጭና፡ ሞፈር፤
በነጋ፡ ጊዜ፣ እኽል፡ እንዳፈር።"
በሚል፡ ትንቢታዊ፡ ቃል፡ ሕዝቡ፡ ተቀበላቸው።

ወደ ሲዳሞ ተሹመው በሄዱበትም ጊዜ ልክ እንደ ጎንደሩ ሁሉ፤

በባሌ፡ ዑጋዴ፣ በጎንደር፡ አስመራ፣
እየነጋ፡ ሲኼድ፣ ሥራው፡ እያበራ፣
በየደረሰበት፡ ሀገሩን፡ ሲያኰራ፣
ዕድል፡ ሲያጋጥመው፡ እንዲሁ፡ በተራ፣
ብቅ፡ አለ፡ በደቡብ፡ ለሲዳሞ፡ ጮራ።
ሲሉ፡ ተቀኝተውላቸዋል።

ሊ.፡ ዤኔራል፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ በ1953፡ ዓ.ም.፡ በመከላከያ፡ ሚኒስቴር፡ ሚኒስትር፡ ዴኤታ፡ በነበሩበት፡ ወቅት፣ ስላርበኝነት፡ የአምስት፡ ዓመት፡ ታሪክ፡ ለቀረበላቸው፡ ጥያቄ፣ ያሰናዱትናቀ ከ50 አመት በኋላ ለ70ኛው የድል በአል መታሰቢያን ምክንያት በማድረግ፣"የ1928—1933፡ ዓ.ም.፡ ዐርበኝነት፤ እንዴት፡ እንደተወጠነና፡ እንደተስፋፋ፡ የሚገልጥ።" በሚል ርእስ ለህትመት የበቃውን ባለ 12 ገጽ ጽሑፋቸውን መመልከት እጅግ ጠቃሚ ይሆናል። (ለተጨማሪ በወሌ፡ ነጋ የተዘጋጀውና የ1928-1933፡ ዓ.ም፡ ዐርበኝነት፤ እንዴት፡ እንደተወጠነና፡ እንደተስፋፋ፡ የሚገልጥ። (ሚያዝያ፡ 27፡ ቀን፣ 2003፡ ዓ.ም)" በሚል ርእስ "የሚያዝያ፡ 27፡ ድል፡ በዓል፡ መታሰቢያ" ይሆን ዘንድ ለንባብ የበቃው ስራቸውን ማየት ተገቢ ነው።)

### የድርስት ሕይወታቸው

ከስራዎቻቸው እጅግ፡ ጥቂቶቹ፡ ብቻ፡ ለህትመት የበቁላቸው ሲሆን፣ ስለ፡ ታሪክም፡ ኾነ፡ ስለግዛት፡ ፍልስፍና፣ ስለ፡ ቀለምም፡ ኾነ፡ ስለ፡ ቋንቋ፣ ዐያሌ፡ ጽሑፎችን፡ ደርሰዋል። ተጽፈው፡ የተዘጋጁና ያለቀላቸው፤ ነገር፡ ግን፡ ገና፡ ያልታተሙ፡ ሌሎች፡ በርካታ መጽሐፎችም፡ አሏቸው። ያገር፡ ፍቅር፡ መዝሙሮችም የስራዎቻቸው አካል ነበሩ።

### ማህበራትን ከማቋቋም እስከ መምራት

አገር አቀፍና የልማት ማኅበራትን፣ ድርጅቶችን፡ ... አቋቁመዋል፤ ብዙዎቹንም፡ በሊቀ፡ መንበርነት፡ መርተዋል። ጥቂቶቹም፤

ጥንታዊት፡ ኢትዮጵያ፡ ሀገራዊ፡ የዠግኖች፡ ማኅበር፡ (ሚያዝያ፡ 1956፡ ዓ.ም.)፣ ሊቀ፡ መንበር፤ የይፋት፡ ልማት፡ ሕዝባዊ፡ ኅብረት፡ (ግንቦት፡ 10፡ 1960፡ ዓ.ም.)፣ ሊቀ፡ መንበር፤ የኢትዮጵያዊያን፡ ሀገራዊ፡ ሥልጡንሕዝባዊ፡ አንድነት፣ ሐምሌ፡ 1፡ ቀን፡ 1967፡ ዓ.ም.፣ ሊቀ፡ መንበር፤ (ሚያዝያ፡ 10፡ 1982፡ ዓ.ም.)፡ የጊዜያዊ፡ ከዋኝ፡ ምክር፡ ሊቀ፡ መንበር፤ የኢትዮጵያ፡ ዐውደ፡ ቀለም፡ (መስከረም፡ 24፡ ቀን፡ 1990፡ ዓ.ም.)፣ ሊቀ፡ መንበር። በ1954፡ ዓ.ም.፣ የኢትዮጵያ፡ እግር፡ ኳስ፡ ፌደሬሽን፡ ሊቀ፡ መንበር፡ በነበሩበት፡ ወቅት፣ ኢትዮጵያ፡ የአፍርካ፡ ዋንጫን፡ ለመጀመሪያ፡ ጊዜ፡ አሸንፋለች። በብፁዕ፡ ወቅዱስ፡ አቡነ፡ ባስልዮስ፡ ርእሰ፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ወፓትሪያርክ፡ ዘኢትዮጵያ፡ ሠያሚነት፣ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋሕዶ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሥጋዊ፡ አስተዳደር፡ ጉባኤ፡ አባል፡ ኾነው፡ ለጥቂት፡ ዓመት፡ አገልግለዋል። በሌሎች በርካቶችም እንዲሁ። አምባሳደርም ነበሩ።

### ሽልማቶች

ከኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፤

- ያርበኝነት፡ ሜዳይ፣ ጥር፡ 12፡ ቀን፡ 1937፡ ዓ.ም፤
- የቅዱስ፡ ጊዮርጊስ፡ የጦር፡ ሜዳ፡ ሜዳይ፣ ጥር፡ 12፡ ቀን፡ 1937፡ ዓ.ም፤
- የዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ የመኰንን፡ ደረጃ፡ ሊሻን፣ መጋቢት፡ 12፡ ቀን፡ 1943፡ ዓ.ም፤
- የኢትዮጵያ፡ የክብር፡ ኮከብ፡ ታላቅ፡ መኰንን፣ ሚያዝያ፡ 27፡ ቀን፡ 1943፡ ዓ.ም፤
- የድል፡ ኮከብ፡ ሜዳይ፣ ሚያዝያ፡ 16፡ ቀን፡ 1948፡ ዓ.ም፤
- የዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ኮርዶን፡ ኒሻን፣ ሚያዝያ፡ 27፡ ቀን፡ 1958፡ ዓ.ም።

### የውጭ፡ መንግሥታት፡ ከሸለሟቸው፡ ውስጥ፤

- ከስዊድን፡ መንግሥት፣ Kömmendor med stora av Kungl. Svärdsorden፥
  የካቲት፡ 1952፡ ዓ.ም፤
- ከታላቋ፡ ብሪታንያ፡ መንግሥት፣ Knight Commander of the Victoria Order፤ 1957፡ ዓ.ም.፤ ይገኙባቸዋል።

ከባለቤታቸው፡ ከክብርት፡ ወይዘሮ፡ ከፈይ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ሰባት፡ ልጆች፡ ወልደዋል፤ ሦስት፡ የልጅ፡ ልጆችንም፡ አይተዋል።

ሊ.ጄኔራል፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፣ እንግሊዝ፡ አገር፡ 32፡ ዓመት፡ በስደት፡ ከቈዩ፡ በኋላ፣ ሚያዝያ፡ 8፡ ቀን፡ 1999፡ ዓ.ም.፡ ከባለቤታቸው፡ ጋራ፡ ወደ፡ ውድ፡ አገራቸው፡ ኢትዮጵያ፡ ተመልሰው፣ ዓመት፡ ከሦስት፡ ወር፡ አዲስ አበባ ተቀምጠዋል። ሐምሌ፡ 15፡ ለ16፡ አጥቢያ፡ 2000፡ ዓ.ም.፡ ዐርፈዋል።

የክቡር፡ ሊ.፡ ዤኔራል፡ ነጋ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ቀብር፡ ሥርዐት፥ ሐምሌ፡ 19፡ ቀን፡ 2000፡ ዓ.ም፣ ዐዲስ፡ አበባ፡ እመንበረ፡ ጸባኦት፡ ቅድስት፡ ሥላሴ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፣ ቤተ፡ ሰብ፡ ቤተ፡ ዘመድ፣ ወዳጅ፡ ወገን፣ ብዙ፡ ሕዝብ፡ በተገኘበት፣ ባርበኞች፡ ዐጀብ፣ በተዋሕዶ፡ ክርስቲያን፡ ሥርዐት፡ ተፈጽሟል።

ስም ከመቃብር በላይ ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
መጋቢት
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የደቡብ ኦሞን ዞን እምቅ የአትሌቲክስ አቅም ለመጠቀም የተከፈተው በር

**ይበል ካሳ**

ኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ እምቅ የአትሌቲክስ አቅም ያላት አገር ብትሆንም መጠቀም የቻለችው ውስን መሆኑን ባለሙያዎች ሲናገሩ ይደመጣል። በተለይም ኢትዮጵያ ከረጅምና መካከለኛ ርቀት ውድድሮች ውጪ በአጭር ርቀቶችና በሜዳ ተግባራት ውድድሮች በተለያዩ አካባቢዎች ያላትን እምቅ የአትሌቲክስ አቅም አውጥታ መጠቀም አልቻለችም። የረጅም ርቀት ውድድሮች በአለም ላይ እየተመናመኑ መምጣታቸውና ያሉትም ከፍተኛ ፉክክር የሚደረግባቸው በመሆኑ ኢትዮጵያ በውጤታማነቷ ለመቀጠል ፊቷን ወደ አጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ማዞር ያለባት ጊዜ አሁን እንደሆነ የፌዴሬሽኑም እምነት ነው።

ለዚህ ደግሞ ትልቅ እምቅ አቅም ካላቸው አካባቢዎች አንዱ የደቡብ ኦሞ ዞን ተጠቃሽ ነው። "ታላቁ ሩጫ በትንሿ ኢትዮጵያ ጂንካ" በሚል መሪ ሃሳብና "ለሠላም እሮጣለሁ" በሚል መፈክር" በፋን ኢትዮጵያና በደቡብ ኦሞ ዞን ትብብር በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በጂንካ ከተማ ሰሞኑን በተካሄደው የስምንት ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ላይም ዞኑ ከሃገር አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያን ሊያስጠሩ የሚችሉ ተተኪ አትሌቶችን ለማግኘት የሚያስችል የአትሌቲክስ እምቅ ኃይል እንዳለው ማስተዋል ተችሏል።

ሕዳር 25 ቀን 2015 ዓ.ም በተካሄደው የስምንት ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ በክብር እንግድነት የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ፣ የደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ የሆነ እምቅ የአትሌቲክስ አቅም ያለው መሆኑን መገንዘባቸውን ገልጸዋል፡፡የደቡብ ኦሞ ዞን በተፈጥሮና በባህል የታደለና ከፍተኛ የቱሪስት መስህብ ያለበት ከመሆኑም ባሻገር ከሃገር አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያን ሊያስጠሩ የሚችሉ ተተኪ አትሌቶችን ለማግኘት የሚያስችል የአትሌቲክስ እምቅ አቅም እንዳለው መገንዘባቸውን ጠቁመዋል፡፡ በመሆኑም መንግሥት በዞኑ ላለው የስፖርት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተለውና አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ ያመላከቱት አቶ ቀጄላ፤ የዞኑ ነዋሪዎችም የተጀመረውን የማሕበረሰብ ስፖርት ከዚህ በኋላም አጠናክረው እንዲያስቀጥሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የደቡብ ኦሞ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ንጋቱ ዳንሳ በበኩላቸው፤ ዞኑ በቱሪዝም ብሎም በአካባቢው ያሉትን ግዙፍ የስኳር ፋብሪካዎች ጨምሮ በግብርና ምርትም ከክልሉ አልፎ ለኢትዮጵያ ዋልታና ማገር የሚሆን ግዙፍ ሃብት ያለበት መሆኑን ጠቁመው፤ በስፖርት በተለይም በአትሌቲክሱ ትልቅ ደረጃ ሊደርስ የሚችል እምቅ ሃብት መኖሩን ተናግረዋል፡፡

የደቡብ ኦሞ ዞን በምስራቅ አፍሪካ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ርቀቶች በርካታ ስመ ጥር ተወዳዳሪዎች መፍለቂያ ከሆነው ሰሜን ኬኒያ ጋር የቅርብ ጎረቤት በመሆኑ "ትኩረት ሰጥተን ከሠራንበት በእኛም ሃገር በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ አያሌ አትሌቶችን ለማፍራት የሚያስችል ዕድል አለ" ብለዋል፡፡ ዞኑ በተለይም የሰሜን ኬኒያ አጎራባች ከሆኑት በእኛንጋቶም፣ ከዳሰነች፣ ከሐመር፣ ከቦዲ፣ ከሙርሲ በአጭርና በመካከለኛ ርቀት ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያስጠሩ የሚችሉ በርካታ አትሌቶችን ለማፍራት ትልቅ አቅም ያለው መሆኑንም ገልጸዋል፡፡


በጂንካ ከተማ በተካሄደው የ8ኪሎ ሜትር ውድድር ሰላሳ ሺ ህዝብ መሳተፉ ተገልጿል፣

በሩጫም ብቻ ሳይሆን በጦር ውርወራ፣ በውሃ ዋና፣ በእርምጃና በሌሎችም የስፖርት ዓይነቶች ጭምር ከፍተኛ እምቅ ሃብት የሚገኝበት መሆኑንም ዋና አስተዳዳሪው አመላክተዋል፡፡ በመሆኑም ከፋን ኢትዮጵያ ጋር ከተካሄደው ከዚህ ውድድር ጀምሮ የዞኑን ብሎም የሃገርን እምቅ የአትሌቲክስ ሃብት ለመጠቀም የሚያስችል ወርቃማ በር መከፈቱን ተናግረዋል፡፡ ለዚህም ከፍተኛ እምቅ ሃብት ባለበት የአትሌቲክስ ዘርፍም ሆነ በሌሎችም አትራፊ የሆኑ የዞኑ ሃብቶች ሁሉ ኢንቨስት ማድረግና ሃገርን መጥቀም የሚፈልግ ሃገር ወዳድ ባለ ሃብት ሁሉ ወደዞኑ በመምጣት ኢንቨስት እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ለዚህም ዞኑ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግና ኢንቨስት ማድረግ ከሚፈልጉ ባለሃብቶች በሙሉ ትብብር ለመሥራት በቁርጠኝነት ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ዋና አስተዳዳሪው ገልጸዋል፡፡

የፋን ኢትዮጵያ መሥራች አትሌት ፋንቱ ሚጌሶ በበኩሏ፤ ፋን ኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ተመሳሳይ የጎዳና ላይ ሩጫ ሲያካሂድ መቆየቱንና ታች ሕብረተሰቡ ድረስ ወርዶ በመሥራት በአጭር ጊዜ ውስጥ በዘርፉ እምቅ አቅም ላላቸው በርካታ ወጣቶች ዕድል መፍጠሩን ተናግራለች፡፡ አሁን ደግሞ ለሰባተኛ ጊዜ ከአስራ ስድስት በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ተፈቃቅረውና ተከባብረው በሰላም በሚኖሩባት የደቡብ አሞዋ ፈርጥ ትንሿ ኢትዮጵያ ጂንካ ከተማ ከሰላሳ ሺ በላይ የከተማዋንና የአካባቢዋን ነዋሪዎች በመሳተፍ በደማቅ ሁኔታ መካሄዱን ገልጻለች።

ሩጫው በዞኑ ያለውን እምቅ የአትሌቲክስ አቅም በመጠቀም እንደ ፈር ቀዳጁ ታላቅ አትሌት አበበ ቢቂላና ምሩጽ ይፍጠር፣ እንዲሁም ጥሩነሽ ዲባባ የመሳሰሉ ታላላቅ አትሌቶችን የማፍራት ዓላማ ያለው መሆኑን አትሌት ፋንቱ ጠቁማለች። ከዚህ በተጨማሪም በጂንካ ከተካሄደው ከዚህ የጎዳና ላይ ሩጫ ጀምሮ ውድድሩን ለሚያሸንፉና ጥሩ ሰዓት ለሚያስመዘግቡ አትሌቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ መሳተፍ የሚችሉበት ፍቃድና ዕድል የሚመቻችላቸው መሆኑንም አመላክታለች፡፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከአሁን በኋላ በቀጣይም በየአመቱ በተከታታይ ተመሳሳይ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮችን ለማካሄድና በዞኑ ያለውን እምቅ የአትሌቲክስ አቅም ለሃገር ጥቅም ለማዋል መታቀዱንም አትሌት ፋንቱ አስረድታለች፡፡

## ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

አዲስ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ን.ስ አ.ማ ከዚህ በታች በተመለከቱት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን በማወዳደር በቅጥር ለማሟላት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሰው የስራ መደብ ላይ መስፈርቱን የምታሟሉ አስፈላጊውን መረጃ በማሟላት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

| ተ.ቁ | ክፍት የስራ መደቡ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | ብዛት | ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ | ተጨማሪ ክህሎት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የህንጻ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር አማካሪ ባለሙያ | | በስምምነት | 1 | በአርክቴክቸር፣ ሲቪል መሀንዲስ፣ ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ቢ ኤስ ሲ /ኤም.ኤስ.ሲ 10/8 ዓመት የሥራ ልምድ በህንጻ ሲቪል መሀንዲስነት በህንጻ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያነት በህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት መሀንዲስነት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለውና ከዚሁ ውስጥ በፕሮጀክት አማካሪነት ከ3 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ማቅረብ የምትችል/የሚችል | መሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት ያለው/ያላት |
| 2 | የመዝገብ ቤት ሠራተኛ | V | 6,412 | 1 | በማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ ሙያ ዲፕሎማና 2 ዓመት የስራ ልምድ በሙያው አግባብ ያለው/ያላት | መሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት ያለው/ያላት |

**ማሳሰቢያ፡**

1. የቅጥር ሁኔታ የመዝገብ ቤት ሰራተኛ በቋሚነት የህንፃ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ በኮንትራት ሆኖ የስራ ቦታ አዲስ አበባ ነው::
2. የምዝገባ ጊዜ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት
3. አመልካቾች በትራንስክሪፕት የተደገፈ የትምህርት ማስረጃና ስርዝ ድልዝ ወይም ፍቀት የሌለው የስራ ልምድ ማስረጃቸውን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ከየግል ሁኔታ መግለጫ ቅጽ (Curriculum vittae) ጋር ማቅረብ አለባቸው::
4. የሚቀርበው የሥራ ልምድ ማስረጃ የስራ ልምድ የሥራ መደቡ መጠሪያ፤ ከመቼ እስከ መቼ እንደሰሩ፤ ቀን ፣ ወር እና ዓመተ ምህረት እንዲሁም የስንብቱን ምክንያት የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡
5. ከመንግስት መቤቶች ውጪ የሚቀርቡ የስራ ልምድ ማስረጃዎች በተጨማሪ የስራ ግብር ስለ መከፈሉ ከገቢዎች ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
6. በፋይናንስ ተቋማት የሰራ ቢሆን ይመረጣል፡፡
7. የመልካም ስነምግባር (Recommendation letter) የሚገልጽ ደብዳቤ ከሚሰሩበት መ/ቤት ማቅረብ የሚችል፡፡
8. የምዝገባ ቦታ ቸርችል ጎዳና ከቴዎድሮስ አደባባይ ከፍ ብሎ ሐሮን ታወር ፊት ለፊት አዲስ ብድርና ቁጠባ ህንፃ 5ኛ ፎቅ ቢ ቁጥር 503 በመምጣት መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን

**ስልክ ቁጥር- 0111263919**

## አዲስ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ን.ስ አ.ማ